# በኢትዮጵያ ፌ✍ደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የግብርና ሚኒስቴር

# ብሐ✍ራዊ የቡና ልማትና ጥራት ማሻሻያ ስትራቴጂ

**ታህሳስ 2007 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**<u>የአዘጋጅ ቡድን አባላት</u>**

1. ዶ/ር ተስፋዬ ሽምብር........................ ኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስትቲዩት
2. አቶ ብርሃኑ ⌨ጋዬ ............................. ግብርና ሚኒስቴር
3. አቶ ተፈሪ ኦልጅራ............................. ቡና ተክል ልማት ድርጅት
4. አቶ መኮንን 🕒/ሚካኤል ...................... ኢትዮ❛❛ያ ምርት ገበያ

**<u>አስተባባሪ</u>**

አቶ ፍቅሩ አመኑ.............................. ግብርና ሚኒስቴር

## ማውጫ

**መቅድም (EXECUTIVE SUMMARY) ..... IV**

**1. መግቢያ ..... 1**

**2. ራዕይ፤ ዓላማና ግቦች ..... 1**

2.1 ራዕይ ..... 1

2.2 ተልዕኮ ..... 1

2.3 ዓላማ ..... 2

2.4 ግቦች ..... 2

*2.4.1 ምርትና ምርታማነት ..... 2*

*2.4.2 ጥራት ..... 2*

**3.የቡና ዓለም አቀፋዊና ሃገራዊ ጠቀሜታ ..... 3**

**4.የባለድርሻና ተባባሪ አካላት ትንተና ..... 7**

4.1. አርሶ አደሮች ..... 7

4.2 ቡና አልሚ ባለሀብቶች ..... 8

4.3 ሕብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች ..... 8

4.4. ሌሎች ማህበራት ..... 9

4.5 ቡና አቅራቢዎች ..... 10

4.6 ቡና ላኪዎች ..... 11

4.7 አለም አቀፍ ቡና ገዢዎች ..... 12

4.8 መንግስት ..... 12

*4.8.1 ግብርና ሚኒስቴር ..... 12*

*4.8.2 የንግድ ሚኒስቴር ..... 14*

*4.8.3 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ..... 16*

*4.8.4 የኢትዮጵያ አዕምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ጽ/ቤት ..... 16*

4.9 ክልል ግብርና ቢሮዎች ..... 17

4.10 ክልል ግብይትና ህብረት ሥራ ቢሮ/ ኤጀንሲ ..... 17

4.11 የአገልግሎት ሰጪዎች ..... 18

*4.11.1 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ..... 18*

*4.11.2 ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ..... 19*

*4.11.3 የትራንስፖርትና የትራንዚት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ..... 19*

*4.11.4 የቡና ሰርቲፊኬት ሰጪ ድርጅቶች/ አካላት ..... 19*

4.12 ሌሎች ባለድርሻዎች ..... 20

**5.የቡና ዘርፍ ነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና ..... 20**

**6.የቡና ልማትና ጥራት ወሳኝ ተግዳሮቶች ..... 23**

*6.1.1 ለቡናው ንዑስ ዘርፍ የተሠጠው ትኩረት አናሳነት ..... 23*

*6.1.2 ከኋላቀር የአመራረት ዘይቤዎቹ የሚያላቅቅ ጠንካራ የድጋፍ ክትትልና ግብረ- መልስ ..... 23*

*ሥርዓት ያለመኖር ..... 23*

*6.1.3. አብዛኛው የቡና ተክል ያረጀና ተገቢውን እንክብካቤ የማያገኝ መሆን ..... 25*

*6.1.4 ሥነ-ምህዳርን ያማከሉ የቡና አመራረት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆን ..... 25*

*6.1.5 የቡና ልማትን ለማስፋፋት የመሬት አጠቃቀምና መረጃ ሥርዓት ያለመዘርጋት* ..... 26
*6.1.6 የግብአትና የብድር አቅርቦት ያለመኖር* ..... 26
*6.1.7 በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ያልተለመዱ ክስተቶች መበራከት* ..... 27
*6.1.8 የቡና ብዝሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ ፍትሐዊ ዘ ረ መል ልውውጥና አጠቃቀም ያለመጠናከር* ..... 28
*6.1.9. የዘርፉ አደረጃጀት ችግር* ..... 28
*6.1.10. የአቅም ግንባታ ድጋፍ በበቂ ሁኔታ ያለመመቻቸት* ..... 28
6.2 ጥራትና ግብይት ተግዳሮቶች ..... 29
*6.2.1 ሥነ ምህዳሩን ያማከሉ የተሻሻሉ የቡና ምርት አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣* ..... 29
*አጠቃቀምና ግንዘቤ ዝቅተኛነት* ..... 29
*6.2.2 እንደየአካባቢው ሥኑ-ምሕዳር ልዩ ባህርይና የጣዕም ይዘት ያላቸው ቡናዎች በጥናት* ..... 30
*ያለመለየት* ..... 30
*6.2.3 የአቅርቦትና የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራ ደረጃ ምደባ ተመጋጋቢ ያለመሆን* ..... 31
*6.2.4 ዘመናዊ የቡና ግብይት ስርዓት ተጠናክሮ ያለመተግበር* ..... 32
*6.2.5 የቡና ዋጋ አለመረጋጋትና ማካካሻ ሥርዓት ያለመኖር* ..... 32
*6.2.6 የኤክስፖርት ቡና ዝግጅት፣ ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን በክልሎች ያለመስፋፋት* ..... 33

**7. የቡና አምራች ሀገሮች ተሞክሮ (BENCHMARK) ..... 33**

7.1 ብርዚል ..... 34
7.2 ቬትናም ..... 35
7.3 ኮሎምቢያ ..... 36
7.4 ጓቲማላ ..... 37

**8. ስትራቴጂያዊ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት ..... 38**

8.1 ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል ..... 39
*8.1.1 ጠንካራ የኤክስቴንሽን ድጋፍና የመረጃ ሥርዓት መፍጠር* ..... 39
*8.1.2. የቡናን ምርትና ምርታማነት ለመጨመር የቡና እደሳ ስራዎችን በስፋት ማከናወን* ..... 40
*8.1.3 በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚ አካላትና ባለሙያዎች ለቡናው ዘርፍ የተለየ ትኩረት ሰጥተው* ..... 41
*እንዲሰሩ ማድረግ* ..... 41
*8.1.4 ለየስኑ-ምህዳሩ ተስማሚ የሆኑ የቡና አመራረት ቴክኖጂዎችን በቀጣይነትና ማፍለቅና* ..... 41
*ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ* ..... 41
*8.1.5 ለቡና ተስማሚ ሆኖ ያለማ መሬት በመለየት ዘመናዊ የቡና ልማትና ምርት ዝግጅት* ..... 42
*ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት* ..... 42
*8.1.6. ለቡና አምራቾችና የግብይቱ ተዋንያን የግብአት ብድር አቅርቦት ማሳደግ* ..... 43
*8.1.7 የአየር ንብረት ለውጥን መላመድና መቋቋም የሚያስችሉ የቡና ልማት ቴክኖሎጂዎችን* ..... 43
*ማስፋት* ..... 43
*8.1.8 የቡና በሽታና ተባይ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በስፋት መጠቀም* ..... 44
➢ ***የቡና ፍሬ በሽታ ቁጥጥር*** ..... 44
*8.1.9 የቡና ብዝሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ፍትሐዊ ልውውጥና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋትና* ..... 44
*ተግባራዊ ማድረግ* ..... 44
*8.1.10 ቅንጅታዊ አሰራርን የሚደግፍ የአደረጃጀት ለውጥ ማድረግ* ..... 45
*8.1.11 የባለሙያ እጥረትና አቅም ውስንነትን መቅረፍ* ..... 45
8.2 የቡና ምርት ዝግጅት ጥራትና ግብይት ስርዓትን ማሻሻል ..... 46
*8.2.1 ሥነ ምህዳሩን ያማከሉ የተሻሻሉ የቡና ምርት አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና* ..... 46

*አጠቃቀም ማሳደግ* ... 46
*8.2.2 የየአካባቢውን ሥኑ-ምሕዳር ልዩ ባህርይና የጣዕም ይዘት ያላቸው ቡናዎች አዘገጃጀት* ... 47
*ተግባራዊ ማድረግ* ... 47
*8.2.3 የአቅርቦትና የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራ ደረጃ ምደባ ማጠናከርና ተመጋጋቢ* ... 47
*ማድረግ* ... 47
***8.2.3.1 ጠንካራ የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብረ-መልስ ስርዓት መዘርጋት*** ... 47
*8.2.4 ልዩ ባህርይና ጣዕም ካላቸዉ የቡና አይነቶች የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ* ... 48
*8.2.5 ዘመናዊ የግብይት ስርዓትን የሚያጠናክር ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ግብረመልስ አሰራር* ... 48
*መፍጠር* ... 48
*8.2.6 የኤክስፖርት ቡና ዝግጅት፤ ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን በክልሎች ማስፋፋት* ... 49
**9. የስትራቴጂዎች አፈፃ▭ም የድርጊት መረሐ ግብር ... 50**
9.1 የቡና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ... 50
9.2. የቡና ምርት ዝግጅትና ጥራት ማሻሻያ መርሃ-ግብር ... 57

## መቅድም (Executive Summary)

ኢትዮጵያ በጣዕሙና ቃናዉ በዓለም ተወዳጅ የሆነዉ አረቢካ ቡና መገኛ እንደመሆኗ በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰፊ ተለያይነት ያላቸዉ ዝርያዎች በተለያዩ የአመራረት ሥርዓቶችና ሥነ-ምህዳራት ከጓሮ እስከ ጫካ በተፈጥሯዊ መንገድ የሚለሙባትና ከብራዚልና ኮሎምቢያ ቀጥላ ሦስተኛ ከፍተኛ አረቢካ ቡና አምራች ሀገር ነች፡፡ ከኤክስፖርት ገቢያችን ከ25% በላይ በመያዝ ቡና በሀገራችን ኢኮኖሚ የመሪነቱን ሚና ሲጫወት የነበረና አሁንም እየተጫወተ ያለ ሰብል ሲሆን 4.2 ሚሊዮን የሚሆኑትን ቡና አምራች አነስተኛ አርሶአደሮችን ጨምሮ ከዜጎቻችን ከሩቡ ለሚበልጡት የሥራ መስክ የከፈተና ኑሯቸዉን ደግፎ የያዘ ከመሆኑም በላይ በህብረተሰቡ ባሕልና ማሕበራዊ ኑሮ ዉስጥ ጉልህ ስፍራና ለረጅም ዘመናት የዘለቀ ታሪካዊ ቁርኝት አለዉ፡፡

ይሁንና ከዋና ዋና ቡና አምራች አገሮች አንጻር አነስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘዉ ምርቱ፤ ምርታማነቱና የጥራት ደረጃዉ እንዲሁም የኤክስፖርት ድርሻችን ይህን እምቅ የተፈጥሮ ፀጋ ወደ ላቀ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ለመለወጥ ብዙ ሥራዎች ይጠብቁናል፡፡ ስለሆነም መንግስት በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ወሳኝ የሆኑና በውጭ ምንዛሪ ምንጭነት ከፍተኛ ድርሻ ካለቸዉ የኤክስፖርት ምርቶች አንዱና ዋናው ለሆነዉ ቡና ልዩ ትኩረት በመስጠት ምርቱንና ምርታማነቱን በመጨመርና ጥራቱን በማሻሻል በአለም ገበያ ተፎካካሪነታችንን የበለጠ በማሳደግ ኤኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግሩን ዕዉን ለማድረግ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ለዘርፉ እድገትና መሻሻል የተለዩ ማነቆዎችን ለመቅረፍ ጠንካራ ድጋፍና ክትትል በማድረግና ህዝባዊ ንቅናቄ ፈጥሮ በሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት ዉስጥ የቡናን ምርትና ምርታማነት ዕድገት እና ጥራት ደረጃዉን በማሻሻል እመርታዊ ለዉጥ በማምጣት በዘርፉ ብርቱ ተፎካካሪ ሆኖ ለመገኘት መንግስት ባለዉ ጽኑ ፍላጎት ይህ የብሐ✍ራዊ ቡና ልማትና ጥራት ማሻሻያ ስትራቴጂ ተነድፏል፡፡ በዚህ ሰነድ በአገራችን ቡና ልማት፣ ምርት ዝግጅት፣ ጥራት፤ የቡና ምርምርና ኤክስቴንሽን ዉስጣዊና ዉጫዊ ሁኔታዎች በመተንተን ምርትን፤ ምርታማነትንና ጥራትን ለማሻሻል ሊተኮርባቸዉ የሚገቡ ማነቆዎች ተለይተዉ በስትራቴጂያዊ ጉዳይነት ተወስደዉ መፍትሄዎቻቸዉን ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

**ዋና ዋናዎቹም፡-**

- በየደረጃው ባሉ አስፈፃሚ አካላት ለንዑስ ዘርፉ የሚሠጠው ትኩረት አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከኋላቀር የአመራረት ዘይቤዎች የሚያላቅቅ የቡናንን ባህርይ ያገናዘበ ጠንካራ የኤክስቴንሽን ድጋፍ፣ ክትትልና ግብረ-መልስ ሥርዓት ያለመዳበር፣
- አብዛኛው የቡና ተክል ያረጀና ተገቢውን እንክብካቤ የማያገኝ መሆን
- ሥነ-ምህዳርን ያማከሉ የቡና አመራረት ቴክኖጂዎች አቅርቦትና አጠቃቀም ዝቅተኛነት
- የቡና ልማትን ለማስፋፋት የመሬት አጠቃቀምና መረጃ ሥርዓት ያለመዘርጋት

- የግብአትና የብድር አቅርቦት ያለመኖር
- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ያልተለመዱ ክስተቶች መበራከት
- የቡና ብዘሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ ፍትሐዊ ዘረ መል ልውውጥና አጠቃቀም ያለመጠናከር
- የንዑስ ዘርፉ አደረጃጀት ችግር
- ሥነ ምህዳሩን ያማከሉ የተሻሻሉ የቡና ምርት አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ አጠቃቀምና ግንዘቤ ዝቅተኛነት
- እንደየአካባቢው ሥነ-ምሕዳር ልዩ ባህርይና የጣዕም ይዘት ያላቸው ቡናዎች በጥናት ያለመለየት
- የአቅርቦትና የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራ ደረጃ ምደባ ተመጋጋቢ ያለመሆን
- ዘመናዊ የቡና ግብይት ስርዓት ተጠናክሮ ያለመተግበር
- የኤክስፖርት ቡና ዝግጅት፤ ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን በክልሎች ያለመስፋፋት
- የአቅም ግንባታ ድጋፍ በበቂ ሁኔታ ያለመሠጠት

ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በተለዩት ወሳ✂ ጉዳዮችና በአጠቃላይ በንዑስ ዘርፉ ባሉን ምቹ ሁኔታዎችና ሥጋች ባሉን ጥንካሬዎችና ድክመቶች ዙሪያ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻዎች ጋር ሰፊ ዉይይት ተካሂደዉ መግባበት ላይ ተደርሶ ሀገራዊ የቡና ልማትና ጥራት የተደራጀ የልማት ሠራዊት በመፍጠርና የተጠናከረ አቅም ግንባታና የግብዓት አቅርቦት ድጋፍ በየደረጃዉ በመስጠት የቡና ምርትንና አቅርቦት አፈጻጸምን አሁን ካለበት 486 ሺህና 224 ሺህ ቶን በቅደም ተከተል ወደ 2.32 እና 2 ሚሊዮን ቶን፣ የታጠበ እና ያልታጠበ ልዩ ቡና ድርሻን ከ10.7 ና 1 በመቶ ወደ 40 እና 30 በመቶ ማድረስ፣ መካከለኛ ደረጃ ቡና ድርሻን በቅደም ተከተል አሁን ካለበት 87 እና 53 በመቶ ወደ 60 እና 40 እንዲሁም ዝቅተኛ ደረጃ ቡናን ከ2.3 እና 46 ወደ 0.5 እና 40 በመቶ ዝቅ ለማድረግ የሚያስችል ጠቋሚ የድርጊት መረሐ-ግብር ተዘጋጅቶ የሰነዱ አካል ተደርጓል፡፡ ዝርዝር ዕቅዱ ከክልሎች ጋር በመወያየት በየደረጃዉ ካለዉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ከነአፈጻጸም ስልቱ በቀጣይ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

በዚህ ዕቅድ መሰረት ሀገራችንን በቡና ምርትና አቅርቦት ባጠረ ጊዜ ዉስጥ ከዓለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ በማድረስ መሠረቱ እየሰፋ በሚሄደዉ የኤክስፖርት ገቢያችን ዕድገት ዉስጥ የቡና ሚና በቀጣይነት የላቀ በማድረግ የአምራቹን፣ የንግዱን ህብረተሰብና በአጠቃላይ የሀገሪቱን ተጠቃሚነት ከፍ ወዳለ ደረጃ ማሻጋገር ስለሆነ የሁሉንም አካላት ያልተቆጠበ ጥረትና ከፍተኛ ትኩረት ይጠይቃል፡፡

# 1. መግቢያ

ቡና በአገራችን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት የመሪነቱን ሚና የሚጫወት ወሳኝ የግብርና ምርት ሲሆን ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና ለህዳሴ ጉዟችን መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ ግል💻 ነዉ፡፡ በመሆኑም መንግስት በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በውጭ ምንዛሪ ምንጭነት ከፍተኛ ድርሻ ካላቸዉ የኤክስፖርት ምርቶች አንዱና ዋነኛ ለሆነዉ ቡና ልዩ ትኩረት በመስጠት ምርቱንና ምርታማነቱን በመጨመርና ጥራቱን በማሻሻል በአለም ገበያ ተፎካካሪነታችንን ለማሳደግ ተስፋ ሰጪ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በሃገሪቱ ለቡና ልማት ተስማሚ የሆኑ ሰፊ ሥነ-ምህዳራት መኖራቸው፣ በባህርያቸው እጅግ ከፍተኛ ልዩነት ያላቸው የአረቢካ ቡና ብዝሀ-ሕይወት ክምችት ባለቤትነት፣ በጣዕማቸው በዓለም ገበያ ተወዳጅ የሆኑ በርካታ ታዋቂ የቡና ዓይነቶች መኖራቸዉ አገሪቱን ከለ✍ሎች የቡና አምራች አገሮች ይልቅ ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚያደርጋት አያጠራጥርም፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በሚታየዉ ኋላቀር እና ባህላዊ የቡና አመራረት ዘይቤ በዓለም ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከረረ በመጣዉ የገበያ ዉድድር በቀጣይነት ብርቱ ተፎካካሪና አዱናፊ ሆኖ ለመገኘት ፈታኝ መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህ የቡናን ልማት ለማስፋፋት፣ ምርትን፣ ምርታማነትንና ጥራትን ወደተ☆ለ ደረጃ ለማሳደግና ብሎም በዓለም ገበያ ቀጣይነት ባለው መልኩ ብርቱ ተፎካካሪ ሆኖ ለመቅረብ በአመራረትና ዝግጅት ሂደት የተ☆☆ሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ሊታለፍ የማይገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም በቡና ዘርፍ ያሉብንን የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት አቅርቦት እጥረቶችን በመቅረፍ እምርታዊ ለዉጥ ማስመዝገብ የሚያስችሉንን ወሳኝ ጉዳዮች በመለየት፣ በሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት ጊዜ ዉስጥ ሀገሪቷን በዓለም ቢያነስ ሁለተኛዋ ከፍተኛ የቡና አምራችና አቅራቢ ሃገር የማድረግ ራዕይ በመሰነቅና ይህንንም እዉን ለማድረግ ይህ የቡና ልማት፤ጥራትና ግብይት ማሻሻያ ስትራቴጂ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

# 2. ራዕይ፤ ዓላማና ግቦች

## 2.1 ራዕይ

ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት ውስጥ በዓለም ተወዳጅና ተመራጭ የሆነ ቡናን በብዛትና በጥራት በማምረትና በማቅረብ፤ ግምባር ቀደም ተጠቃሚ ከሆኑ ሁለት ሀገሮች አንዷ ሆና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ የማሻሻል ሚናዉ የበለጠ አድጎ ማየት፡፡

## 2.2 ተልዕኮ

በቡና ልማትና ግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉትን ዋነኛ ተግዳሮቶችን በመለየትና ስልቶችን በመንደፍ፤ ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት፤ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና፤ ግብዓቶችን በመጠቀምና ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት የቡናን ምርት፤ ምርታማነትንና ጥራትን በማሻሻል በዓለም የቡና ገበያ ቀጣይነት ባለው መልኩ ብቁ ተፎካካሪ በመሆን አገሪቱን በተለይም አምራቹንና የግብይቱን ተዋኒያን ከዘርፉ የላቀ ተጠቃሚ ማድረግ፡፡

## 2.3 ዓላማ

1. በአገሪቱ የቡና ልማት፣ጥራት፣ ምርምርና ኤክስቴንሽን ሥራዎች ዙሪያ ያሉትን ወሳኝ እጥረቶች በመለየት፣ የቡናን ምርትና ምርታማነት በእጥፍ የሚያሳድጉና ጥራቱን የሚያሻሽሉ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ለማድረግ

2. የኤክስፖርት ቡናን የአሰራር ሥርዓት ከገዢዎች ፍላጎት ጋር በማጣጣም የአምራቹንና የግብይቱን ተዋንያን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የውጭ ምንዛሪ ገቢ መጠንን ለማሳደግ

## *2.4 ግቦች*

### 2.4.1 ምርትና ምርታማነት

- ✓ 2.3 ሚሊዮን አርሶ አደሮች በሙሉ ፓኬጅ ቡና እንዲያለሙ መደገፍ
- ✓ ምርትን ከ552.3 ሺህ ቶን ወደ 2.32 ሚሊዮን ቶን ማሳደግ
- ✓ ምርታማነትን ከ7.1 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 12.5 ኩ/ል በሄ/ር ማሳደግ
- ✓ ምርት የሚሰጥ  የቡና መሬት ስፋት፡ ከ780.9 ሺህ ሄ/ር ወደ 1.85 ሚሊዮን ሄ/ር ማድረስ
- ✓ 396.82 ሺህሄ/ር ያረጀ እናት ቡና እድሳትና ስግሰጋ ማካሄድ
- ✓ 190.3 ሺህ ሄ/ር ያረጀ እናት ቡና ነቅሎ በምርታማ ዝርያዎች መተካት
- ✓ 1.9 ሚሊዮን ሄ/ር አዲስ መሬት በምርታማ ዝርያዎች መትከል
- ✓ ለማዕከላዊ ገበያ አቅርቦት ቡና፡ ከ224 ሺህ ቶን ወደ 2 ሚሊዮን ቶን ማድረስ

### 2.4.2 ጥራት

- ✓ የታጠበ  ልዩ ቡና አቅርቦት ከ11 በመቶ ወደ 40 በመቶ ማሳደግ
- ✓ የታጠበ መካከለኛ የጥራት ደረጃ ያለው ቡና አቅርቦት ከ87 በመቶ 60 በመቶ ማድረስ
- ✓ ያልታጠበ አቅርቦት ልዩ ቡና ከ1 በመቶ ወደ 30 በመቶ ማሳደግ
- ✓ ያልታጠበ መካከለኛ የጥራት ደረጃ ያለው  ቡና አቅርቦት ከ53 በመቶ ወደ 40 በመቶ ዝቅ ማድረግ
- ✓ ያልታጠበ ዝቅተኛ ደረጃ ያለው  አቅርቦት ቡና  ከ46 በመቶ ወደ 30 በመቶ መቀነስ

## 3.የቡና ዓለም አቀፋዊና ሃገራዊ ጠቀሜታ

ቡና በዓለም ገበያ ከነዳጅ ዘይት ቀጥሎ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ የሐሩራማ /ትሮፒካል/ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ የግብርና ምርት ሲሆን ሰባ የሚሆኑ ሀገሮች የሚያመርቱትና ዓለም አቀፍ የንግድ ማዕከል ባወጣዉ መረጃ ከሀገራችን ጭምር በርካታ ታዳጊ ሃገሮች ከ20% በላይ የሚሆነውን የውጪ ምንዛሪያቸውን የሚያገኙት ከዚህ ሰብል ነው፡፡ ከ13ኛዉ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከኢትዮጵያ ዉጭ በመከከለኛዉ ምሥራቅና በሰሜናዊ አፍሪካ በሚገኙ የአረብ ሀገራት ዘንድ ተወዳጅ አልኮል አልባ መጠጥ ሆኖ በማገልገል ቀይቶ ቀስ በቀስ በቱርክና ጣሊያን በኩል ከ15ኛው - 17ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ወደ አዉሮፓና አሜሪካ ዘልቆ በአሁኑ ጊዜ 2.5 ቢሊዮን ሲኒ የሚሆን ቡና በዓለማችን በቀን የሚጠጣበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡

በሠንጠረዥ 1 ላይ እንደሚታየዉ ቡናን በማምረት በዓለም ትልቁን ሥፍራ (86.6%) የሚይዙት 11 ሀገሮች ሲሆኑ ከአፍሪካ ኢትዮጵያና ዩጋንዳ (7.5%)፤ ከደቡባዊና ማእከላዊ አሜሪካ ብራዚል፣ ኮሎምቢያ፣ ሜክሲኮ፣ ጓቲማላ፣ ፔሩና ሁንዱራስ (52.5%)፤እና ከኤስያ፣ ቬትናም፣ ኢንዶኔዥያና ህንድ (26.6%) ናቸዉ፡፡ አራት ሀገሮች (ብራዚል፣ቬትናም፣ ኢንዶኔዥያና ኮሎምቢያ) ብቻቸዉን 60% የሚሆን ድርሻ አላቸዉ፡፡ በዓለም ከሚመረተዉ ቡና 77% የሚደርሰዉ ኤክስፖርት የሚደረግ ሲሆን አዉሮፓ ህብረት 50% (ከዚያ ዉስጥ ጀርመን 14.5%፣ጣሊያን 6%፣ ፈረንሳይ 5.5%፣ ስፔን 3.7%፣ ቤልጂየም 3.6%፣ ታላቋ ብሪታኒያ 2.9%)፤ ዩ.ኤስ. አሜሪካ 19.5%፤ እና ጃፓን 5.9% ኢምፖርት ያደርጋሉ፡፡

ቡና ባለዉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዉ ምክንያት በተለያዩ አገሮች 12 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት ላይ የሚለማ ሲሆን ግብይቱ በሁሉም ሀገራት እየተስፋፋ በመምጣቱ በዓለም ገበያ ላይ ምርቱ በተለያየ መልክና የጥራት ደረጃ በብዛት እየቀረበ ለገዥዎች ብዙ አማራጮችን በመፍጠሩ ምክንያት ዋጋዉ እየወረደ በአምራች ሃገሮች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ነዉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በአምራች አገሮች መካከል ያለዉን የዓለም የቡና ገበያ ፉክክር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከረረ እንዲመጣ አድርጎታል፡፡

ሃገራችን በቡና ምርት ከዓለም አምስተኛ ከአፍሪካ አንደኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ቢሆንም ከዓለም ቡና ጠቅላላ ምርት ከ5% እንዲሁም ከአረቢካ ቡና ምርት ከ9% የማይበልጠዉን ድርሻዋን ባላት ምቹ እና ሰፊ ሥነ-ምህዳር በመጠቀም ደረጃዋን ለማሻሻል ከፍተኛ ዕድል አላት፡፡ በ2005/06 ምርት ዘመን በግብርና ሚ/ር መረጃ መሰረት ለሰብል ልማት ከዋለው መሬት ውስጥ ምርት በሚሰጥ ቡና የተሸፈነዉ 758 ሺህ ሄክታር ወይም በጠቅላላው ለሰብል ልማት ከዋለዉ 5% ያልበለጠ ሲሆን ከአጠቃላይ የኤክስፖርት ገቢ 26% ያህሉን ድርሻ ይይዛል፡፡በዓለም አቀፍ ገበያ የቡና አቅርቦት፣ ፍላጎትና ኤክስፖርት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን ሠንጠረዥ 2 ላይ እንደቀረበዉ የሀገራችን እውነታም ተመሳሳይነት ያለዉ ቢሆንም የአቅርቦትና ኤክፖርት ዕድገት በአማካይ ከምርት ዕድገቱ ያነሰ መሆኑ በጥራት አጠባበቅና በወጪ ንግድ ማስፋፊያ አፈጻጸማችንን የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ የበለጠ ማሻሻል እንደሚኖርብን ያመላክታል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡ በዋና ዋና ቡና አምራች ሀገሮች ዓመታዊ ቡና ምርትና ኤክስፖርት (እ.አ.አ 2008 - 2012)**

| ተ.ቁ | ሀገር | ምርት | | | | | | ድርሻ (%) | ኤክስፖርት (በሚሊዮን 60 ኪ.ግ ከረጢት) | | | | | | ኤክስፖርት/ ምርት | አማካይ ኤስፖርት ድርሻ (%) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | አማካይ | | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | አማካይ | | |
| 1 | ብራዚል | 45.99 | 34.47 | 48.09 | 43.48 | 50.83 | 44.57 | 33.58 | 29.10 | 30.35 | 33.03 | 33.51 | 28.33 | 30.86 | 0.69 | 30.33 |
| 2 | ቬትናም | 18.44 | 17.82 | 19.47 | 24.06 | 22.00 | 20.36 | 15.34 | 16.10 | 17.05 | 14.23 | 17.67 | 25.48 | 18.11 | 0.89 | 17.80 |
| 3 | ኢንዶኔሽያ | 9.61 | 11.38 | 9.13 | 7.29 | 12.73 | 10.03 | 7.56 | 5.74 | 7.91 | 5.49 | 6.16 | 10.61 | 7.18 | 0.72 | 7.06 |
| 4 | ኮሎምቢያ | 8.66 | 8.10 | 8.52 | 7.65 | 9.50 | 8.49 | 6.40 | 11.08 | 7.89 | 7.82 | 7.73 | 7.17 | 8.34 | 0.98 | 8.20 |
| 5 | ኢትዮጵያ | 4.95 | 6.93 | 7.50 | 6.80 | 8.10 | 6.86 | 5.17 | 2.85 | 3.29 | 3.32 | 2.68 | 3.20 | 3.07 | 0.41 | 3.02 |
| 6 | ህንድ | 3.95 | 4.79 | 5.03 | 5.23 | 5.23 | 4.86 | 3.66 | 3.38 | 3.01 | 4.63 | 5.84 | 5.29 | 4.43 | 0.91 | 4.35 |
| 7 | ሜክሲኮ | 3.45 | 3.60 | 4.33 | 5.90 | 4.90 | 4.44 | 3.34 | 2.45 | 2.84 | 2.50 | 2.91 | 3.56 | 2.85 | 0.64 | 2.80 |
| 8 | ጓትማላ | 4.65 | 4.11 | 4.00 | 4.56 | 3.90 | 4.24 | 3.19 | 3.78 | 3.49 | 3.47 | 3.70 | 3.75 | 3.64 | 0.86 | 3.58 |
| 9 | ፔሩ | 3.87 | 3.29 | 4.07 | 5.37 | 4.1 | 4.14 | 3.12 | 3.73 | 3.07 | 3.82 | 4.70 | 4.31 | 3.93 | 0.95 | 3.86 |
| 10 | ሁንዱራስ | 3.45 | 3.60 | 4.33 | 5.90 | 4.90 | 3.97 | 2.99 | 3.26 | 3.08 | 3.35 | 3.95 | 5.51 | 3.83 | 0.96 | 3.76 |
| 11 | ኡጋንዳ | 3.29 | 2.85 | 3.20 | 2.82 | 3.20 | 3.07 | 2.31 | 3.31 | 3.01 | 2.66 | 3.14 | 2.69 | 2.96 | 0.96 | 2.91 |
| | ን/ድምር | 118.31 | 109.94 | 127.67 | 130.06 | 141.39 | 115.03 | 86.66 | 92.78 | 92.55 | 94.32 | 102.99 | 111.9 | 98.79 | 0.77 | 87.38 |
| | ሌሎች | 10.29 | 12.96 | 5.73 | 4.08 | 3.22 | 17.71 | 13.34 | 12.61 | 11.75 | 12.73 | 12.47 | 13.33 | 12.58 | 0.6 6 | 12.36 |
| | **ጠ/ድምር** | **128.6** | **122.9** | **133.4** | **134.14** | **144.61** | **132.74** | **100** | **105.39** | **104.3** | **107.05** | **115.46** | **125.2** | **111.37** | **0.77** | **100** |
| | **%** | **92** | **89.45** | **95.7** | **96.96** | **97.78** | **86.67** | | **88.03** | **88.73** | **88.11** | **89.2** | **89.38** | **88.7** | | |

**ምንጭ፡ ዓለም ቡና ድርጅት 2012**

**ሠንጠረዥ 2: ዓመታዊ የሃገራችን ቡና ምርትና ኤክስፖርት**

| ዓመት (እ.አ.አ) | ምርት (ሺህ ቶን) | ኤክስፖርት (ሺህ ቶን) | መቶኛ | ኤክስፖርት ዋጋ (ሚሊዮን ዩ.ኤስ.ዶ) |
|---|---|---|---|---|
| 2005/06 | 286.64 | 153.16 | 53.43 | 365.83 |
| 2006/07 | 333.06 | 176.39 | 52.96 | 424.14 |
| 2007/08 | 358.02 | 170.89 | 47.73 | 525.12 |
| 2008/09 | 296.94 | 153.16 | 51.58 | 375.84 |
| 2009/10 | 415.86 | 172.21 | 41.41 | 528.16 |
| 2010/11 | 450.00 | 196.12 | 43.58 | 841.65 |
| 2011/12 | 407.88 | 169.39 | 41.53 | 832.91 |
| 2012/13 | 486.00 | 199.10 | 40.97 | 746.42 |
| አማካይ | 379.30 | 173.8 | - | 580.0 |

ምንጭ፡ ዓለም ቡና ድርጅት 2012

**ሠንጠረዥ 3፡ የሃገራችን ቡና ምርት፣ አቅርቦትና ኤክስፖርት ዕድገት (ሺህ ቶን)**

| ዝርዝር | 2009/10 | 2010/11 | 2011/12 | 2012/13 | አማካይ | አማካይ ዓመታዊ ዕድገት (%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ምርት[1] | 415.86 | 450.0 | 407.88 | 486.0 | 439.74 | 5.62 |
| አቅርቦት[2] | 216.98 | 228.47 | 237.45 | 224.38 | 226.82 | 1.14 |
| ኤክስፖርት[2] | 172.22 | 196.14 | 169.41 | 199.10 | 184.22 | 3.9 |


*ምን*

*ጭ፡[1] ዓለም ቡና ድርጅት 2012/13 [2] የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን*

በሀገራችን ከ93 - 95% የሚሆነዉ ቡና በአነስተኛ አርሶአደሮች እንዲሁም 5 - 7 % በግል ባለሀብቶች ይመረታል፡፡ ከአርሶ አደሩ ዓመታዊ ገቢ ዉስጥ ቡና ከግማሽ በላይ ድርሻ የሚይዝባቸዉ አምራች አከባቢዎች በዋናነት በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና በደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ባሉ 125 ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ እና ትግራይ በተወሰኑ ወረዳዎች እንዲሁም በሀረሪና ድሬዳዋ በጥቂቱ እየተመረተ ያለዉ ቡና ለጊዜዉ የአካባቢ ፍጆታንም ሊያሟላ የቻለ ባለመሆኑ ለማዕከላዊና ኤክስፖርት ገበያ የሚቀርበዉ ቡና በዋናነት በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብ/ብ/ህ እና በጋምቤላ

ክልሎች ዉስጥ የሚመረት ነዉ:: ኢትዮጵያ ለውጪ ገበያ ከምታቀርባቸው የግብርና ምርት ውጤቶች ቡና ቀዳሚውን ቦታ የሚይዝ ከመሆኑም ባሻገር በዓለም ገበያ ከ60% በላይ የገበያ ድርሻ ያለው የአረቢካ ቡና የተለያዩ ዝርያዎች በአገሪ• መኖር ከሌሎች ቡና አምራች ሀገሮች የተለየች የሚያደርጋት በመሆኑ ይህንንም መልካም አጋጣሚ በመጠቀም አገራችን የተለያዩ ተፈላጊነት ያላቸውን የቡና ዓይነቶች በ58 ሀገሮች ለገበያ ስታርብ በዋናነት በ15 ሀገራት ትሸጣለች::

**ምስል 1፡ ለቡና ልማት በአመቺነት ደረጃ የተለዩ አከባቢዎች**




**ሠንጠረዥ 4፡ ለቡና ከፍተኛና መካከለኛ ተሰማሚ መሬት በሺህ ሄ/ር**

| ክልል | ከፍተኛ | መካከለኛ | ድምር |
|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | 3,556 | 6,442 | 9,998 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 836 | 3,502 | 4,338 |
| አማራ | 361 | 5,191 | 6,552 |
| ቤ/ጉሙዝ | 619 | 1,760 | 2,379 |
| ጋምቤላ | 105 | 105 | 210 |
| ትግራይ | - | 627 | 627 |
| **ድምር** | **5,477** | **17,629** | **23,105** |

*ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት*

በዚህም ረገድ አገራችን የአረቢካ ቡና መገኛ፤ የብዝሀ-ሕይወት ምንጭ፤ የተለያዩ በዓለም ተወዳጅና ልዩ ጣዕም ያላቸዉ ቡናዎች ባለቤትና ለልማቱ መስፋፋት አመች የሆኑ የተፈጥሮ ሁኔታዎችና መልካም አጋጣሚዎች ያላት ብትሆንም የሰብሉ ምርት፤ ምርታማነትና ጥራት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ያህል ጥቅም እያገኘች አይደለም፡፡ ቡና የሀገራችንን የውጭ ምንዛሪ ገቢ ምሰሶ በመሆን ለረዥም ዓመታት በመዝለቅ በብሄራዊ ኤኮኖሚ ልማታችን ወሳኝ በመሆን፤ ከባሕላዊና ማሕበራዊ እሴትነቱ በተጓዳኝ የአምራቹን አርሶአደር የኑሮ ሁኔታ በማሻሻልና ለ25% ያህል የአገሪቱ ዜጎች በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሥራ እድል በመፍጠር የሚጫወተዉ ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ በመሆኑም ከቡና የሚገኘውን የውጪ ምንዛሪ በላቀ ደረጃ በማሳደግ የአምራቹንና ግብይቱን ተዋንያን ተጠቃሚነት በቀጣይነት ለማረጋገጥ በየዓመቱ የምናመርተውን የቡና መጠን ከማሳደግ በተጨማሪ በዓለም ገበያ ላይ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ምርት በማቅረብ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነን መገኘት ይጠበቅብናል፡፡

በልዩ (ስፔሻሊቲ) ቡናዎች ላይ በማተኮር ልማቱን ከማስፋፋት ጎን ለጎን በድህረ ምርት አያያዝ፣ የምርት ዝግጅትና ቅንብር ላይ በመስራት እሴትን መጨመርና ምርቱን በጥሬና በተፈጨ መልክ በማዘጋጀት በተለያዩ ነባርና አዳዲስ የዓለም ገበያዎች በማስተዋወቅ ከዘርፉ ዘላቂ የሆነ ጥቅም ለማግኘት የተሻለ ሁኔታ እንዳለን እሙን ነዉ፡፡ በዚህም ረገድ በ5 ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ ዓመት ላይ ለማሳካት ያስቀመጥነው ከ601 ሺህ ቶን የሚጠጋ ቡና ኤክስፖርት የማድረግ ግብ እውን ሊሆን የሚችልበት ስትራቴጂ ተቀርፆ በተለይ እምርታዊ ለዉጥ ለማምጣት የተሻለ አቅም ባለቸዉ አካባቢዎች የተለየ ርብርብ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን ከእጥፍ በላይ ማሻሻል እንደሚቻል እምነት ተይዞ በቁርጠኝነት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ሀገራችንን በቀጣይ ሰባት ዓመታት ውስጥ በዓለም ቡና አምራችነት እና አቅራቢነት ሁለተኛ ደረጃ ላይ ደርሳ ለመገኘት አሁን ባሉን ዋና ዋና ቡና አምራች ወረዳዎችና እምቅ አቅማቸዉ በቀጣይ ጥናት በሚለዩ የሁሉም ክልሎች ተጨማሪ ወረዳዎች የተለየ ትኩረትና የተሟላ ድጋፍ በመስጠት ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን በላቀ ደረጃ የሚያሻሻሉ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎችን ምክረ-ሀሳብና ምርጥ ተሞክሮን ያካተተ ሙሉ ፓኬጅ በእያንዳንዱ አርሶ አደር ማሳና በቡና አልሚ ባለሀብቶች እርሻዎች መተግበር ይኖርብናል፡፡

## 4.የባለድርሻና ተባባሪ አካላት ትንተና

### 4.1. አርሶ አደሮች

በሀገራችን ከ93 - 95% የሚሆነዉ ቡና በአነስተኛ አርሶአደሮች ይዞታ ሥር የሚገኝ ሲሆን የአመራረት ዘይቤውም የጫካ፤ ከፊል ጫካ እና የጓሮ ቡና መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ምርትና ምርታማነቱ ብሎም የጥራት ደረጃው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለሚገኝ አርሶ አደሩ ከቡናው ምርት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ሳያገኝ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ቡናን በሚፈለገው መጠንና ጥራት አምርቶ ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ በተከታታይ ለመጀመሪያ ደረጃ ገበያ የማቅረብ ኃላፊነትን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አኳያ ከጊዜ ወደ ጊዜ በልማት ሠራዊት በመደራጀት ኮምፖስትና የተሻሻሉ ዝርያዎችን የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የምርታማነት፣ ምርት አሰባሰብ፣ አዘገጃጀትና አቅርቦት ሁኔታ ዕድገት አሳይቷል፡፡ እንዲሁም የቡና ምርት ጥራት አጠባበቅ ልምድ በየጊዜው ማሳደግ መቻሉና በቡና ዘመናዊ ግብይት ስርዓት ተወዳዳሪና ግልጽ በሆነ ዋጋ በአቅራቢያዉ በተቋቋመው የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት መሸጥ ላይ እምነት እየያዘ መሆኑ በመልካም ጎን የሚጠቀሱ ተግባሮች ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ አርሶ አደሩ በገቢ ተጠቃሚነቱ እያደገ የመጣ ቢሆንም ወደ ላቀ ደረጃ ከማድረስ አንጻር የሚቀሩ በርካታ ክፍተቶች አሁንም ይታያሉ፡፡

ለማሳያነትም በግብርና ኤክስቴንሽን እየቀረቡለት ያሉትን የተሻሻሉ የግብርና አሠራሮችን አሟልቶ ስለማይተገብር አመካይ ምርታማነቱ ከግንባር ቀደም አርሶአደር ቢያንስ በእጥፍ አንሶ ይታያል፡፡ የቡና ተክል እንክብካቤ ጉድለት፣ የተሻሻሉ

ዝርያዎችን ያለመጠቀም፤ ያረጁ ቡና ዛፎችን ያለመጎንደል ወይም ነቅሎ በአዲስ ያለመተካት፣ የቡና ጥላ መጠን ያለመስተካከል፣ የቡና በሽታና ተባዮችን በተገቢው መንገድ አለመከላከል፣ በወቅቱ ቀይ ቀዩን ቡና በመልቀም ምርቱን በወቅቱ በመሰብሰብ እርሸቱን ለገበያ ያለማቅረብ፣ በጥራት በተዘጋጀ አልጋ ወይም አውድማ ላይ ያለማድረቅ እና የደረቀዉን በተስማሚ መጋዘን በንጹህ ዕቃ/ጆንያ ያለማቆየት፤ በቡና ምርት፣ ምርታማነትና ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩ ያሉ አብይ ክፍተቶች ናቸው፡፡

ከግብይት አንፃርም አንዳንድ አርሶአደሮች የቡናን ምርት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት አቅርበው ምርቱን በወቅቱ ከመሸጥ በእጃቸው የጀንፈል ቡና ከምችት በማቆየት በአቅርቦት ፍሰትና ጥራት ላይ ክፍተት እንዲፈጠር ማድረጋቸው፣ የቡናውን ጥራት ጠብቆ ገበያ ለማድረስ ደረጃውን የጠበቀ የምርት መያዣ ጆንያና ተስማሚ ማጓጓዣ አለመጠቀም፣ የተዘረጋውን ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት በማጠናከር የሕገ-ወጥ ቡና ግብይትን መከላከል በዋናነት የሚጠቅመው አርሶ አደሩን  እና የቡና ዋጋ በዓለም ገበያ ላይ ተመስርቶ በከፍተኛ ሁኔታ የሚዋዥቅ መሆኑን በመገንዘብ ከመወሰን አንፃር እንዲሁም በጥሩ ዋጋ በሚሸጥበት ጊዜ የተገኘዉን ገንዘብ በቁጠባ የመጠቀምና በሌላ አዋጭ ብዝነስ በማዋል ችግሩን ለመቋቋም ሰፊ ክፍተቶች ይስተዋላሉ፡፡

## 4.2 ቡና አልሚ ባለሀብቶች

በሀገራችን ከ5-7 በመቶ የሚሸፍነው የቡና ይዞታ በአልሚ ባለሀብቶች  ይዞታ ስር  የሚገኝ  ነው፡፡ በዚህም መሰረትካለፉት ሃያ ዓመታት ጀምሮ ወደ ሥራ የገቡት ባለሀብቶችና ወደ ግል ይዞታነት የተዛወሩት የመንግስት ቡና እርሻዎች በጥቅሉ 150 በሚደርሱ ባለሀብቶች ከ30 ሄ/ር እስከ 7000 ሄ/ር ላይ ቡና በማልማት ለማዕከላዊ ገበያ ወይም ወደ ውጭ በመላክ የተሰማሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ዘመናዊ የቡና እርሻዎች  በተሻሻለ አሰራርና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ልማቱን በሚያበረታታ ሂደት ላይ ያሉና  በአካባቢያቸው ላሉ አርሶ አደሮች የቡና ምርጥ ዘር በማቅረብና እንዲሁም ዘመናዊ የምርት ዝግጅት ስራዎችን በመተግበርና ድጋፍ በመስጠት በአቅራቢያቸዉ ከሚገኙ የግብርና መዋቅሮች ጋር በመተባበር የሚሰሩ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ቡና አልሚ ባለሀብቶች በሚፈለገው መጠን ያልተጠናከሩና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በተሟላ መልኩ እየተጠቀሙ ያለመሆናቸውና በሰለጠነ ባለሙያ  ስለማይጠቀሙ  ምርታማነታቸዉንና ትርፋማነታቸዉን ከፍ በማድረግ በመሆን ለዘርፉና ሀገራችን ኤኮኖሚ ዕድገትም እንደዚሁም በአካባቢያቸው ለሚገኙ አርሶአደሮች የተሻሻሉ አሰራሮችን በማስተላለፍ እያበረከቱ ያለው አስተዋፅኦ ውሱን ነው፡፡ ስለዚህ ቴክኖሎጂዎችን በተሟላ መልኩ በመጠቀም እና ብቃት ያላቸዉን ባለሙያዎች በመቅጠር በምርትና ምርታማነት ዕድገትና ጥራት መሻሻል እንዲሁም ከአርሶ አደሩ ጋር ጠንካራ ቅንጅት በመፍጠር ኢንዱስትሪዉን በማሳደግ በገበያው ብርቱ ተፎካካሪ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ በመንግሥት የተሰጣቸዉን በቀጥታ ምርታቸዉን ወደ ዉጭ የመላክ መብትን በመጠቀም ከአርሶአደሩና አቅራቢዉ በህገወጥ መንገድ ቡናን በመሰብሰብ ቀላቅለዉ ኤክስፖርት በማድረግ ግብይቱን የሚያዛቡበት ሁኔታ በተወሰኑት ላይ ይታያል፡፡

## 4.3 ሕብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች

በየደረጃው የተደራጁት የህብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች የቡና አምራቹን አርሶአደር በማደራጀት ምርቱን በተሻለ ዋጋ ለማዕከላዊ ገበያ ወይም በቀጥታ ወደ ውጭ በመላክ የሚሸጥበትን ሁኔታ በማመቻቸት አርሶአደሩ ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚረዱ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት አርሶ አደሩን ለምርታማነት ዕድገትና ምርት ጥራት የሚዉሉ ግብዓቶችና የፋይናንስ አቅርቦት በማመቻቸት፣ በዘመናዊ ግብይት ሥርዓት እንዲጠቀም አቅም በመገንባት፣

ወቅታዊ የገበያ መረጃ በመቀበል እና በቂና ተስማሚ ማዘጋጃና ማከማቻዎችን በመገንባት በወቅቱ ምርቱን ፍትሃዊና ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ በመረከብ በአጠቃላይ ተጠቃሚነቱን ከማረጋገጥ አንጻር በርካታ ተግባራትን በማከናወን የአባላት ቁጥርን ለማሳደግ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ጥቂት የሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ህብረት ሥራ ማህበራትና አብዛኞቹ ዩኒየኖች በዚህ ረገድ የተወሰነ ጥረት በማድረግ ላይ ሲሆኑ ብዙዎቹ ዩኒየኖች ለዓለም ገበያ የቡና ምርት ማቅረብ የጀመሩ ቢሆንም የተሠሩት ሥራዎች በቂ በሚባል ደረጃ ላይ የሚገኙ አይደሉም፡፡

ማህበራቱ አልፎ እልፎ በሚታየዉ የአመራሮቻቸዉ ብቃት ማነስና ኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ምክንያት የአባሎቻቸዉን ምርት በሚፈለገው ደረጃ በመረከብና በማዘጋጀት በተስማሚ መጋዘን አቆይተዉ የተሻለ ለዋጋ ለመሸጥ ባለመቻላቸውና በየእርከኑ ያለው ግንኙነትና መደጋገፍ ባለመጠናከሩ አርሶአደሩ ከመሠረታዊ ማህበራት ይልቅ እንዲሁም መሠረታዊ ማህበራትም ከዩኒዬኖቻቸው ይልቅ አብዛኛዉን ምርታቸውን ለግል ነጋዴዎች አልፎም ለህገ-ወጥ ሰብሳቢዎች በየመንደሩ ለመሸጥ መምረጣቸው፣ ተሰማሚ የምርት ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘኖችና በቂ የፋይናንስ አቅም የሌላቸው በመሆኑ በቂ ምርት ገዝቶ ማዘጋጀትና መያዝ አለመቻል፤ ፣ የማህበራቱን ገንዘብና ንብረት አያያዝና አጠባበቅ በየጊዜዉ ኦዲት አለማድረግና በአጥፊዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ በአግባቡ ያለመወሰድ፣ በዉጭዉ ዓለም ካሉት ህብረት ሥራ ማህበራት በልማቱና ግብይቱ መልካም ተሞክሮዎችን በመቅሰም የጥራት ማሻሻያ፣ ገበያ ማስፋፊያና ትስስር ሥራዎችን በበቂ ያለመሥራት፣ ፈጣን የገበያ ውሳኔ መስጠት አለመቻልና የዓለም ገበያ ዋጋን ተከትሎ ምርት ያለመግዛትና ያለመሸጥ፣ ለግብይት ሥርዓቱ ተግባራዊነት የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት ያለመቻላቸው፣ ወደ ኤክስፖርት የገቡት ሕብረት ሥራ ማህበራት/ዩኒየኖችም ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎችን እያሳዩ ቢሆንም በአዳዲስ ገበያዎች ሰብሮ በመግባት የተሻለ ምርት በማቅረብ በየዓመቱ ወደ ዉጭ የሚልኩት ምርት አድገት ትርጉም ያለው ደረጃ ላይ አለመድረሱ በዋናነት የሚታዩባቸዉ ችግሮች ናቸው፡፡

## 4.4. ሌሎች ማህበራት

- **የኢትዮጵያ ቡና አልሚዎችና ላኪዎች ማህበር**

ማህበሩ መንግስት በፈጠረው ምቹ የግብርና ፖሊሲና ስትራተጂ በመጠቀም ቁጥራቸው ከ60 በላይ በሆኑ ባለሀብቶች የተመሰረተ ማህበር ነው፡፡ የማህበሩ ዋና አላማ እነዚህ በሰፋፊ የቡና ልማትና ኤክስፖርት ላይ የተሰማሩትን ባለሀብቶች በማስተባበር ጥራቱን የጠበቀ ልዩ ቡና በማምረትና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አባላቱ ብሎም ሀገሪቱ በዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ብዛት ያለው የስራ ዕድል በመፍጠር የሀገሪቱን ቡና ተወዳዳሪነት በማጎልበትና የተሻለ ተጠቃሚ በማድረግ እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ የሚያበረታታ ነው፡፡ የማህበሩ አባላት ቡና በሚያለሙበት አጎራባች የሆኑ ቡና አምራች አርሶአደሮችን የቡና ዘር በማቅረብና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ እያደረጉለት ያለው አስተዋፅኦ የሚያበረታታና በቀጣይ እያደገ መሄድ ያለበት ነው፡፡ ማህበሩ የዓለም የቡና ኢንዱስትሪ የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ በተሻለ የመከታተልና የማየት አጋጣሚዎችን ተጠቅሞ ለአርሶ አደሮች፣ ለአባላቱና በየደረጃዉ ላሉ ባለሙያዎችና አመራሮች ስለተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች ጠቀሜታ ማሳወቅ ተግቶ መሥራት ይኖርበታል፡፡

- **የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማህበር**

ይህ ማህበር የቡናው ዘርፍ በመንግሥት አወቃቀር መደራጀት ከጀመረበት ወቅት ጀምሮ በጥቂት ቡና ላኪ ኩባኒያዎች ተመስርቶ በዘርፉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ የሚገኝ ግንባር ቀደም ማህበር ነው፡፡ ማህበሩ የቡናው ክፍለ ኤኮኖሚ ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ ፖሊሲዎች፤ መመሪያዎችና ደንቦች በመሆን እንዲቀረፁና ሥራ ላይ እንዲውሉ ከመንግስት ጋር ተባብሮ በመሥራት አስተዋፅአዉን በማበርከት ላይ ሲሆን ከሌሎች ተመሳሳይ የቡና አምራችና ገዢ ሀገራት አቻዎቹ ጋር ዓለማቀፋዊ ግንኙነት በመፍጠርና የልምድ ልውውጥ በማድረግ አባላቱን ብሎም ሀገሪቱን የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ

ማስቻል ነው፡፡ ይህ ማህበር በአሁኑ ወቅት በየዓመቱ ዓለም አቀፍ የቡና ኮንፈረንስ በሀገሪቱ እንዲካሄድ በማድረግ የሀገሪቱን ቡና በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል፡፡

ይሁንና አመራረቱን ዘመናዊ በማድረግና ግብይቱን ፍትሃዊነት በማላበስ በኩል ከመንግሥት ጎን ሆኖ ክፍተቶቹን በማረምና አባላቱን በመግራት ለዘርፉ ዘላቂ ዕድገት ሊጫወት የሚገበዉን ሚና ባግባቡ መወጣት ላይ ጠንክሮ መስራት ይጠቅበታል፡፡ ለአብነትም አባላቱ ከምርት ገበያ የሚገዙትን ቡና በኮንትራታቸዉ መሠረት አዘጋጅተዉ ቶሎ ኤክስፖርት ባለማድረግ ዉል ማፍረስ፣ በመጋዘን ያለዉን ክምችት መረጃ በትክክል ያለመያዝ ረገድ፣ ከብሔራዊ ባንክ ከተገኘዉ ኤክስፖርት ፈቃድ ጋር ያልተመጣጠነ ቡና ማስወጣት የመሳሰሉት ህገወጥ አሰራሮችን ከአስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር በቆራጥት መታገል ይኖርበታል፡፡

- ***የኢትዮጵያ ቡና ቆይዎች ማህበር***

ማህበሩ በምርት ገበያው ከሚቀርበው አቅርቦት ቡና ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውለውን ቡና ከኢትዮጰያ ምርት ገበያ በመግዛት ቆልተው ፈጭተውና አሽገው ለተለያዩ የንግድ ድርጅቶች በሚያከፋፍሉ የንግድ ድርጅቶች የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡ ማህበሩ ከ30 በላይ አባላት ያሉት ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ አሰራራቸውን በማዳበር እና የቡናውን ኢንዱስትሪ ለማሳደግ የበኩሉን አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ ዘርፉ በተሻሻለ ቴክኖሎጂና አቅም የቡናን ምርት እሴት በመጨመር ሃገሪቷ ከዘርፉ የላቀ ተጠቃሚ እንድትሆን ያሉበትን ተግዳሮቶች ለይቶና ተጠናክሮ በመስራት እሴት የተጨመረበት ቡናችንን ለዓለም ይበልጥ ማስተዋወቅ አለበት፡፡

ከሌሎች ቡና አምራችና ላኪ ሃገሮች በጎ ልምድ በመቅሰም የተቆላና የተፈጨ ቡና ዓለምአቀፍ የጥራት ደራጀዉን በጠበቀ መልኩ በማምረትና ለገበያ በማቅረብ ለዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል የመፍጠርና ከጥሬ ቡና ኤክስፖርት ጥገኝነት በሂደት የመላቀቅን አቅጣጫ መከተል ያስፈልገዋል፡፡

## 4.5 ቡና አቅራቢዎች

የቡና አቅራቢዎች ከአርሶአደሩ የሚቀርብን ቡና ከመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት ቡናን በመግዛትና በማዘጋጀት ለማዕከላዊ ገበያ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት እያንዳንዱ አቅራቢ በመስፈርቱ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በማውጣትና በየዓመቱም በማደስ የሚሰሩና ቡናን ገዝተው በአግባቡ መዝግበው፣ በተሻለ ጥራት አዘጋጅተውና በንፁህ የቃጫ ጆንያ አከማችተው በወቅቱ የተዘጋጀውን ቡና ጥራቱና መጠኑ ተረጋግጦለት ወደ ምርት ገበያ በሕጋዊ ሰነድ በማጓጓዝ እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የቡና ጥራት ደረጃን በማሳደግ፤ የአቅርቦት ሂደትን ሳይቆራረጥ በማስኬድ የቡና ግብይት በሚፈለገው ደረጃ እንዲሳለጥ በሚደረገው ጥረት ክፍተቶች ይታያሉ፡፡

በዘርፉ ከሚስተዋሉ ችግሮች ውስጥ ለአብነት ብንወስድ ቡናን በሕገ-ወጥ መንገድ ለሀገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ፣ በትክክለኛ የዓለም ቡና ዋጋ መረጃ ላይ ባልተመሠረተ ዋጋና ባልተገባ ዉድድር መግዛት፤ አላስፈላጊ ክምችት በመያዝ በቡና አቅርቦት ላይ እጥረት እንዲፈጠር ማድረግ፤ በአቋራጭ ለመበልጸግ ባዕድ ነገር ቀላቅሎ ማቅረብ፣ ደረጃውን ባልጠበቀ ምርት የተሻላ ዋጋ ለማግኘት ማጭበርበር፤ ደረጃውን ባልጠበቀ ጆንያ ማቅረብ፤ እርስ በርስ ተመሳጥሮ ዋጋ ወስኖ መግዛት፣ የመሳሰሉት በአቅራቢዎች በኩል የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ ችግሮች ናቸዉ፡፡

በአንፃሩ በግብይት ሂደት ውስጥ አባላትና ወኪሎች አልፎ አልፎ በአቅራቢዎች ላይ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ውስጥ ለመጥቀስ ያክል - በመመሳጠር የምርት ገበያውን ዕለታዊ ዋጋ ለማውጣትና ለማውረድ መስራት፣ የአክስዮን ማሕበርን እንደ ሽፋን በመጠቀምና እንደ መድረክ ወኪል ሆኖ በመግባት የየግል ግብይት ማካሄድ፣ አንዳንድ አገናኝ አባላት የሸጡበትን የምርት ዋጋና ሌሎች መረጃዎችን በአግባቡና በወቅቱ ለደንበኞቻቸው አለማድረስ፤ በዚህም ምክንያት አቅራቢዎች ለገበያ ያቀረቡትን ምርት እንዲሸጥ የሰጡት ውሳኔ ወቅታዊነትን ያልተከተለና በገበያ ሂደትም ችግሮችን የሚያባብስ መሆን፤ አንዳንድ አገናኞች ደንበኞቻቸው ሽጡ ባሉት ቀንና ዋጋ ያለመሸጥ እና ከላኪዎች ጋር በመመሳጠር ዋጋ ዝቅ ባለ ወቅት በመሸጥ ወካዮቻቸዉን ማጭበርበር የመሳሰሉት ሲሆኑ በግብይቱ ሂደት ችግሮቹ ተለይተው ሊስተካከሉ የሚገባቸው ናቸው፡፡

## 4.6 ቡና ላኪዎች

የቡና ላኪዎች ቡናን ከምርት ገበያ በመግዛትና በማቀነባበር ለኤክስፖርት ወደ ውጭ በመላክ ተረፈ-ምርታቸውንም ለሀገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ በዘርፉ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት እያንዳንዱ ቡና ላኪ በመስፈርቱ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በማውጣትና በየዓመቱም በማደስ የሚሰሩና ቡናን ገዝተው በአግባቡ መዝግበው፣ በተሻለ ጥራት አዘጋጅተውና በገቡት የኮንትራት ውል መሰረት ቡናን በወቅቱ አዘጋጅተው በህጋዊ አካል ጥራቱና መጠኑ ተረጋግጦለት ወደ ውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቡናን ለዓለም በማስተዋወቅና ገበያን በማፈላለግ ዘርፉ የበለጠ እንዲስፋፋና እንዲያድግ የላቀ ድርሻ እንዲጫወቱ እና ለቡና በተሻለ ዋጋ ኮንትራት በመግባት የአገሪቱ ምርት በቀጣይ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ ማስቻል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም እንዲረዳቸው ከተፎካካሪ ሀገራት በተሻለ ሁኔታ የቡና ገዢዎቻችንን ፍላጎት ለማርካት ምርትን በጥራትና በደንበኞች ፍላጎት ማዘጋጀት፤ዘመናዊ የገበያ ስርዓትን መዘርጋት፤ብቁ የሰው ሃይልና የተደራጀ አሰራር መከተል፤ ዘመናዊ የቡና ኮንትራት አገባብና አፈፃጸም እንዲኖር ማስቻል፤ የአገሪቷን የቡና አይነቶች ልዩ ባህሪያቸውን ጠብቆ መላክና የመሳሰሉት ተግባራትን በማከናወን የቡናው ኢንዱስትሪ ተአማኒነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያድግ ማድረግና በዘርፉ ለታቀደው ግብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለአብነትም አንዳንድ የቡና ላኪዎች በምርት አስተሻሸግ፣ በአዳዲስ ገበያዎች ቡናን በማስተዋወቅ፤ በአዳዲስ ገበያዎች ዘልቆ በመግባትና ነባር ገበያዎች ላይ የገበያ ድርሻ ከማሳደግ አንጻር እየሰሩ ያሉት ተግባራት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለተመዘገበዉ የቡና ኤክስፖርት መጠንና ገቢ እድገት የማይናቅ አስተዋፅዖ ማበርከቱ ግልጽ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ምንም እንኳን መሻሻሎች ቢኖሩም ዘመናዊ የግብይት ሥርዓቱን በሚገባ ተገንዝቦ በዓለም ገበያ ፍላጎት ላይ በተመሠረተ ምርቶችን በጥራት አዘጋጅቶ ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ረገድ አሁንም በከፍተኛ ሁኔታ በአንዳንድ ላኪዎች ዘንድ የሚስተዋሉ ክፍተቶች ሲሆኑ ለአብነትም ቀድመዉ ዋጋ ተደራድረዉ ወደ ምርት ገበያ በመግባት የሀገር ውስጥ ገበያ የዓለም ገበያ ዋጋን ተከትሎ እንዳይራመድ እንቅፋት መሆን፤ የእህት ኩባንያ ያቀረበውን አቅርቦት ቡና ወይም ቀድመው ተነጋግረው የገቡትን ቡና ከምርት ገበያው መጋዘን ለይቶ በማውጣት የግብይት ሥርዓት አካሄድ ላይ ችግር መፍጠር፤ ከአቅም በላይ የሆነ ኮንትራት በመግባትና ባለመፈጸም የቡና ገዢ ደንበኞችን ዕምነት መሸርሸር፤ የዓለም ገበያ ሁኔታን ሳያገናዝቡ በከፍተኛ ዋጋ አስቀድሞ ምርት በመግዛት ኪሳራ ላይ መውደቅ፤ ለውጭ ገበያ ገዢዎች የተሳሳተ አሉታዊ መረጃ በማቃበል የገበያ ድርሻችንን እንድናጣ ማድረግ፣ የተለያዩ ቡና ኦሪጅን ማደባለቅ፣ ኮንትራት ከተገባው ጥራት ደረጃ ጋር የማይመጥን ምርት መላክ፣ ከመግዣ ዋጋ በታች ኮንትራት በመግባት ዝቅተኛ ጥራት ያለው ቡና በመላክ ኪሳራን ለማካከስ መሞከር፣ ጠንካራ ማህበር በመፍጠር ከመንግሥት ጎን በመቆም በዓለም ገበያ ያለንን የተወዳዳሪነት አቅምን ለማሳደግ በቂ ጥረት ያለመደረጉ፤ በጥሩ ቢዝነስ ስነምግባር ታንጾ ያለመስራት፤ በገበያ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ የገበያ ማስፋፊያ ሥራ በራስ ተነሳሽነት የማካሄድ ውሱንነት፣ ጥቂት ላኪዎች መንግስት ለዘርፉ ማደግ የሚዘረጋቸውን አሠራሮች በተገቢውና አዎንታዊ መልኩ ሳይገነዘቡ አልያም በሕገ-ወጥ መንገድ የሚያገኙት ጥቅም እንዳይቀርባቸዉ በመስጋት በደፈናዉ

ከመቃወምም አልፈዉ አደናቃፊ መሆን የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ለዘርፉ ማደግ የላቀ ሚና እንዲጫወቱ ያስችላቸዋል፡፡

## 4.7 አለም አቀፍ ቡና ገዢዎች

አለም አቀፍ ቡና ገዢዎች ከተለያዩ ቡና አምራችና ሻጭ ሀገሮች ቡናን በመግዛት ለተጠቃሚው የሚያቀርቡ አካላት ናቸው፡፡ ከገዢዎች ተወካዮች ጋር ባለፉት ዓመታት የተጀመሩ መድረኮችና የተፈጠሩ መቀራረቦችና በሂደትም ኤክስፖርት አፈጻጸምን በቡና ገዢዎች አንጻር በመገምገም በንግድ ሂደቱ የግዢ መሻሻሎች ታይተዋል፡፡ ቢሆንም በጥራት፣ በተወዳዳሪ ዋጋ፣ በተከታታይነት የሚፈልገውን ምርት እንደያገኝ የሚያስችለው መሆኑን በተገቢው ተረድቶ ፈጥኖ በመቀበል ወደ ሥርዓቱ በደጋፊነት እንዲገባ የተሠሩ ሥራዎች በቂ የሚባሉ አይደሉም፡፡

አንዳንድ በተለይ በኤሺያ ሀገራት የሚገኙ ገዢዎች ቡና ኮንትራት ከገቡ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ኮንትራቶችን መሰረዝ፣ አንዳንዴም ምርቱ መግቢያ ወደብ ከደረሰ በኋላም ለመረከብ ፈቃደኛ አለመሆን፣ የገቡትን ኮንትራት ናሙና በማመላለስ በወቅቱ አለመረከብ፣ የዓለም ገበያ ዋጋ በልተጠበቀ ሁኔታ ሲያድግ አስቀድሞ ለተገባ ኮንትራት እንደመልካም ደንበኛ ተደራድረው የዋጋ ማሻሻያዎችን ማድረግ ሲችሉ በነበረው ሁኔታ የኮንትራት ውል መሠረት እንዲያሟሉ ተፅዕኖ መፍጠር፣ ሀገሪቱ ካላት ተጨባጭ ሁኔታ የምታወጣቸውን የግብይት አሠራሮች፣ መመሪያዎችና ህጎች ፈጥኖ አምኖ ወደ ሥራ አለመግባት በዋናነት የሚጠቀሱ ጉድለቶች ናቸው፡፡

## 4.8 መንግስት

ከቡናው ዘርፍ ጋር ግንኙነት ያላቸው የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት በተለያየ አደረጃጀት ውስጥ ተዋቅረው ልማቱን፤ጥራትና ግብይቱን በማስተባበርና በመምራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሰረት የሚያከናውኗቸውንና የሚጠበቅባቸውን ተግባራት በምን አግባብ እየተወጡ እንደሆነ ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 4.8.1 ግብርና ሚኒስቴር

የግብርና ሚኒስቴር ከመንግሥት በተሰጠዉ ኃላፊነት በመነሳት ሃገራችን በገጠር ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶች ባስቀመጠቻቸዉ አቅጣጫዎች መሠረት ሀገራዊ የቡና ብዘሃ ህይወት ጥበቃ፣ ምርምር፣ ልማትና ጥራት ትርጉም ባለው መልኩ እንዲካሄድ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት ድጋፍና ክትትል በማድረግ ዘርፉ ለግብርና ክፍለኤኮኖሚ ብሎም አጠቃላይ ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት የሚያበረክተዉ አስተዋፆዉ በቀጣይ እንዲያድግ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም የቡና ዘርፍ ከፍተኛ የሆነዉን ሀገርን የማልማት ሚናዉን ባግባቡ እንዲወጣ ለማስቻል በምርምር የተገኙ በሽታን የሚቋቋሙና በየስነ-ምህዳሩ የተመረጡ ልዩ የቡና ዝርያዎችና የተሻሻሉ የአመራረትና አዘገጃጀት ዘዴዎች ለአርሶ አደሩና ለቡና አልሚ ባለሀብቶች እንዲደርሱ፣ በክልሎችና በሌሎች ሀገራት በቡናዉ ዘርፍ የተመዘገቡ መልካም ተሞክሮዎች ተቀምረዉ በአምራቹ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲዉሉ በማድረግ የተከናወኑት ተግባራትና የተገኙት ዉጤቶች የሚያበረታቱ ናቸዉ፡፡ በተንጠባጠበ መልኩም ቢሆን የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር በዘርፉ ዕድገት ላይ አሉታዊ ጫና የሚያሳድሩ ተግዳሮቶችን ተባብሮ ለመፍታት ጅምር ሥራዎች ዉጤት እያስገኙ ናቸዉ፡፡ ሆኖም የምርምርና ኤስቴንሽን ቅንጅቱ እንዲሁም የምክርና ሥልጠና አገልግሎቱ የቡናን ቋሚ ሰብልነትና ኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባገናዘበ ደረጃ ላይ ደርሶ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሊያደርገን በሚያስችል ቁመና ላይ አይደሉም፡፡

በቡና ኤክሰቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ በኩል በምርምር የተገኙ ስፔሻሊቲና የቡና ፍሬ በሽታን የሚቋቋሙ የቡና ዝርያዎችና የተሻሻሉ የአመራረትና አዘገጃጀት ዘዴዎች ለአርሶ አደሩና አልሚ ባለሀብቶች እንዲደርሱ፣ መልካም ተሞክሮዎች ተቀምረዉ በአርሶአደሩ እንዲተገበሩ የተከናወኑት ተግባራትና የተሰጠዉ ድጋፍና የተደረገዉ ክትትል፤ በየክልሉ በሚደረገው የሥራ አፈጻጸም ግምገማ በቡና ጥራትና አቅርቦት የሚታዩ ወቅታዊ ችግሮች እንዲፈቱ ጥረት መደረጉ፣ በመስክ በመገኘት የባለሙያ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለችግሮች መፍትሔ የማስገኘትና የአቅም ክፍተቶችን በስልጠና የማብቃት ጥረቶች መደረጋቸው በዋናነት በጥንካሬ የሚወሰዱ ተግባራት ናቸው፡፡ በሌላ መልኩ የቡና አምራቹ በዘመናዊ አመራረትና ምርት አያያዝ ላይ ያለውን ክህሎት እንዲያሳደግና በቡና ምርታማነትና ጥራት ላይ ለውጥ እንዲያመጣ በቂ ድጋፍ እየተሠጠዉ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የዘመናዊ ምርት ግብይት ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ በኩል የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ አስፈጻሚ አካላትን በመደገፍና አፈጻጸማቸውን ከሚመለከታቸዉ ጋር ተቀናጅቶ በመከታተል፣ ደረጃቸዉን የጠበቁ የምርት ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘኖች በግል ባለሀብቶች እንዲገነቡ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፤ ወጥነት ያለው ከክልል እስከ ቀበሌ የሚደርስ የቡና ልማትና ግብይት መዋቅር እንዲዘረጋ በማድረግና በበጀት በመደገፍ በኩል የሚታዩ በርካታ ውስንነቶች ተለይተው ሊስተካከሉ የሚገባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም የተሻሻሉ የአመራረት ቴክኖሎጂዎቸን በማስፋት ረገድ ያሉበትን ጉድለቶች በትክክል ለይቶ በመፍታት የላቀ ዉጤት ለማስመዝገብ በወሳኝ መልኩ ገና ብዙ መስራት እንዳለበት አያጠያይቅም፡፡

#### 4.8.1.1 የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ማዕከል

ይህ ማዕከል በሚኒስቴሩ የእጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር የስራ ሂደት ተጠሪ ሆኖ ሀገሪቱ ለውጭ ገበያ የምትልከውን የኤክስፖርት ቡና ጥራትና ፍተሸ ማካሄድና የጥራት ሰርቲፊኬት በመስጠት ቡናን አሸጎ በመመሪያው መሰረት ይልካል፡፡ በተጨማሪም ከቡና ጥራት ጋር በተያያዙ በዘርፉ ለተሰማሩ ድርጅቶች የጥራትና ጣዕም ባለሙያ ስልጠና በመስጠትና የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ይከታተላል፡፡ ይሁን እንጂ የአቅርቦትና ኤክስፖርት ቡና ደረጃ ምደባ አለመጣጣም፤ ዘርፉ በሰው ሃይልና ቴክኖሎጂ ከወቅቱ የገበያ ፍላጎትና ገዢዎች አንፃር በሚፈለገው መጠን ተደራጅቶና ተጠናክሮ አለመገኘቱ ከዘርፉ ተገልጋዮች የሚጠብቁትን ቀልጣፋ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ መስጠት ያለማቻሉ፣ የቡና ጥራት ግንዛቤ በአምራቹና ንግዱ ህብረተሰብ እንዲሰርጽ ተገቢ ድገፍ ያለመስጠቱ ዋና ዋና ተግዳሮቶቹን በትክክል ለየቶ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

#### 4.8.1.2 የኢትዮጰያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

በብሔራዊ ግብርና ምርምር ሥርዓታችን ለሚካሄደዉ የቡና ምርምር ከፍተኛዉ ኃላፊነት የተሰጠዉ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ለጅማ ግብርና ምርምር ማእከል ነው፡፡ ማዕከሉ ስፔሻሊቲ ቡናዎችን ጨምሮ ቀደም ሲል ካወጣቸው የቡና ዝርያዎች ባሻገር ለተለያዩ ቡና አብቃይ አካባቢዎች የተሻሻሉ ዝርያዎችን የማፍለቅ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ ለእያንዳንዱ የቡና አብቃይ ሥነ-ምህዳር የሚስማሙ ችግር ፈቺ የሆኑ የቡና ቴክኖሎጂዎች በማቅረብ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት በማርካት የዘርፉን ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስተዋጽዖ በቀጣይነት ለማጎልበት የሚያስችል የምርምርና ኤክስቴንሽን አቅጣጫ ላይ በበቂ ትኩረት በመሥራት በኩል በርካታ እጥረቶች አሉበት፡፡ የዲቃላ ቡና ዝርያዎችን በቲሹ ካልቸርና በግንድ ቁርጥራጭ በማባዛትና ሌሎች ልዩ ልዩ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በሚፈለገዉ ብዛትና ጥራት በማፍለቅና በማስተዋወቅ በኤክስቴንሽን በኩል ለተጠቃሚዉ በፍጥነትና በብዛት ደርሶ የቡናን ምርት፣ ምርታማነትና ጥራት ትርጉም ባለዉ መልኩ ሊያሳድግ የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር በተጠናከረ ደረጃ ላይ አይደለም፡፡ ለዚህም ድክመት

በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ዋነኞች ምርምሩና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱ አደረጃጀት ውስንነት፣ የትሥሥሩ ጠንካራ አለመሆን፣ በቂ በጀትና የሰለጠነ የሰዉ ኃይል አለመመደብ½ ከዓለም አቀፍ የምርምርና ኤክስቴንሽን ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት እጅግ የላላ መሆንና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በመናበብ በበቂ ሁኔታ ለመስራት አለመቻሉና የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ለዘርፉ ማደግ የላቀ ሚና እንዲጫወት፤ የተሻሻሉ የአመራረት ቴክኖሎጂዎቸን በማፍለቅና በማሰራጨት ረገድ ያሉትን ጉድለቶች በትክክል ለይቶ በመፍታት የላቀ ዉጤት ለማስመዝገብ ገና ብዙ መሰራት እንደሚኖርበት ይታመናል፡፡

### 4.8.1.3 የኢትዮጲያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት

ሃገራችን የአረቢካ ቡና ዘረ-መል ምንጭ እንደመሆኗ መጠን፤ ለሰብሉ የተጠናከረ ጥበቃ   በማድረግ ከጥፋት መታደግ ያስፈልጋል፡፡ በቡና መገኛነትና ብዝሀ-ህይወት ምንጭ መሆኑ የሚታወቀው የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ደን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ ይገኛል፡፡ የቡናችንን ምርታማነትና ጥራት ለማሻሻል እና የብዘሃ- ህይወት ጥበቃ በምናደርገዉ ጥረት የዘረ-መል መመናመንን በመከላከልና ጥበቃ በማድረግ ረገድ ትኩረት በመስጠት በተፈጥሮ ደን ውስጥ የሚገኘውንና በአርሶአደሩ እጅ ያሉ የቡና ዝርያዎችን መጠበቅና መንከባከብ፤ ለመላው ዓለም ሁሉ የአረቢካ ዘረ-መል ምንጭ እንዳይጠፋ ማድረግ ሃገራችን ላይ የተጣለ ሃላፊነትና ግዴታ ነው፡፡  በመሆኑም  በተፈጥሮ ደን ውስጥ የሚገኘውን የጫካ ቡና እና በአርሶአደሩ እጅ ያሉ ነባር የቡና ዝርያዎችን በመጠበቅና በመንከባከብ እንዲሁም የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ዘላቂነት ያለው የብዝሀ-ህይወት ጥበቃና የዘረ መል ልዉዉጥ ሥርዓት በመዘርጋት ዉድ ሀብታችንን ከጥፋት መከላከል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ተግባር ነው፡፡

በመንግስት በኩል የተፈጥሮ ቡናን ዘረ-መል ጥበቃ እና እንክብካቤ ማድረግ አስፋላጊነቱ ቢታመንበትም በቡና ጫካዎች ዙሪያ የሚኖረዉን ህብረተሰብ  ተሳትፎና ተጠቃሚትን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ማድረግ የሚቻልበት ደረጃ  ላይ ገና አልተደረሰም፡፡ ለዚህም በዋና ዋና ምክንያትነት ከሚጠቀሱት ተግዳሮቶች ውስጥ- የደን መጨፍጨፍና ለዓመታዊ ሰብል ልማት መዋል፤ የቡና ብዘሀ-ሕይወት ጥበቃ የግንዛቤ እጥረትና፣ ፍትሐዊ የዘረ-መል  ልውውጥና አጠቃቀም እንዲሁም የቁጥጥር ሥርዓትና ቅንጅታዊ አሰራር ያለመኖር ናቸው፡፡

bt=¥¶M yx!T×ùÃ Bz¦ HYwT _b” x!n!StE$T†T ytÈlbTN `§ðnT lmwÈT kምርምርና ኤክስቴንሽን ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት የላለ መሆንና ባለድርሻ አካላትና ለጋሾች ጋር በቅንጅትና በመናበብ በበቂ ሁኔታ መስራት ላይ ያሉበትን ክፍተቶች አለመሙለቱ አብይ ችግሮች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም በዘርፉ  ያሉትን ጉድለቶች ለይቶ በመፍታት  ኢንስቲትዩቱ ከተፈጥሮ ሀብታችንን አንዱ የሆነውን ቡናችንን ከጥፋት እንዲታደግ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

### 4.8.2 የንግድ ሚኒስቴር

የንግድ ሚኒስቴር በሀገሪቱ የሚካሄደውን የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ ስራ እንቅስቃሴ በመምራት፤ በመደገፍና በመከታተል የተጣለበትን ሃላፊነት በመወጣት ላይ የሚገኝ መንግስታዊ ድርጅት ሲሆን፤ ኢትዮጵያ መደ ውጭ ከምትልካቸው ዋና ዋና የግብርና ውጤቶች አንዱ የሆነውን የቡና ጥራት ቁጥጥርና የግብይት ሥርዓት ዝርጋታ በማጠናከርና በማስፋፋት ከፌዴራልና ክልል ባለድሻ አካለት ጋር በቅንጅት በመስራት የቡና ግብይት ሥርዓቱ ዘመናዊነትን ይዞ ወደፊት እንዲራመድ  ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም በየክልሉ በተከታታይ በሚደረገው የሥራ አፈጻጸም ግምገማ በቡና ጥራትና አቅርቦት የነበሩ ወቅታዊ ችግሮች እንዲፈቱ ጥረት መደረጉ፣ የግብይት ተዋንያኖችን በማስተባበር

በዘርፉ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለመፍታት ያለዉ ቁርጠኝነት፣ ላኪ ድርጅቶች በቢዝነስ ፕላን ላይ በመመስረት የአፈጻጸም ደረጃቸውን በየጊዜው በመገመገም የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መደረጉ፣ የገበያ ማስፋፊያና ትስስር ሥራዎችን የግብይት ተዋንያን አስተባብሮ በማዘጋጀትና በማሳተፍ የቡና ኤክስፖርት እንዲሻሻል መደረጉ በአዎንታዊነት ጎን የሚወሰዱ ናቸዉ፡፡

በአንፃሩ በቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አተገባበር ላይ በየወቅቱ የሚታዩና ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለይቶ በማዉጣት ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት ፈጣን የማስተካከያ እርምጃዎች በመውሰድ ሥርዓቱ ወጥ ሆኖ እንዲገነባ ያለማድረግ፤ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ውስንነቶችን በወቅቱ አለመቅረፍ፤ የቁጥጥር ሥርዓትን በማጠናከር በሕገ-ወጥ መንገድ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሰውን የህገ-ወጥ ቡና ንግድ እንቅስቃሴ በሚፈለገው መልኩ መቆጣጠር ያለመቻሉ፤ ላኪዎች በቢዝነስ ፕላናቸው መሠረት ምርቱን በወቅቱ ገዝተው፣ አዘጋጅተውና በኮንትራታቸዉ መሠረት ህጋዊ አግባብን ተከትለዉ እንዲልኩ፣ በመጋዘኖቻቸዉ ያለዉን ክምችት ተከታትሎ ቆጠራ ያለማካሄድ፣ ከደንብና መመሪያ ዉጭ የሚንቀሳቀሱትን የግብይት ተዋንያን ተከታትሎ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ በማድረግ፣ በማዘጋጃና በማከማቻ አቅም፣ በብደርና በትራንስፖርት አቅርቦት፣ በገበያ ማስፋፊያና ትስስር፣ በምርት ገበያ አገልግሎት አሰጣጥ፣ በወደብ አገልግሎት ያሉ እጥረቶችን በፍጥነት አለመፍታት፤ መረጃዎችን ለተጠቃሚው በወቅቱ አለማድረስ እንዲሁም የግብይት ክህሎት ያለመዳበር ውሱንነቶች በዋናነት የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በቡና ግብይት ሂደቱ ላይ ያሉትን ጉድለቶች ለይቶ በመፍታት ሀገሪቱ ከዘርፉ የምትገኘውን ገቢ እንዲያድግ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

### 4.8.2.1 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን በማዕከላዊ ገበያ የምርት ግብይት ሥርዓትን የሚቆጣጠር ተቋም ነው፡፡ በዚህም መሠረት ባለስልጣኑ ውጤታማና ዘመናዊ መገበያያ ሥርዓት መገንባቱን በማረጋገጥ፡፡ ምርት ገበያው አስተማማኝ፣ ግልጽና የተረጋጋ አሰራር እንዲኖረው የሚቆጣጠር ሲሆን በገበያ የሚሳተፉትንም ሆነ አጠቃላይ የህብረተሰቡ ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡ ለዚህም እንዲረዳው ግልጽ አሠራርና ሥርዓትን ዘርግቶ ዘመናዊ ገበያ ሥርዓት ባለው መንገድ እንዲከናወን የሚሠራ ተቋም ነው፡፡ ይሁንና የሥርዓቱን አደስነት ተከትሎ አቅራቢዎችና ላኪዎች በሚጠብቁት ፍጥነት፣ ጥራትና ግልጸኝነት አገልግሎቱን መስጠት ላይ ክፍተቶች እንዳሉ በየጊዜዉ ይነሳሉ፡፡ ቡና አቅራቢዎችና ላኪዎች በመመሳጠር ዋጋዉን ያላገባብ ከፍና ዝቅ በማድረግ ገበያዉን እንዳያዛቡ በንቃት መከታተልና እርምጃ መዉሰድ ያለመቻልጉዳይ በስፋት የሚነሱ ችግሮች ናቸዉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የተቋቋመ የመሆኑን ያህል የግብይት ሥርዓቱን ማስጠበቅ ላይ በቂ ሥራ እየሰራ አለመሆኑን የመደረኩ ተገልጋዮች ሁሌ ይጠቅሳሉ፡፡

### 4.8.2.2 ኢትዮጵያ ምርት ገበያ

ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወጥ ሆነው በተዘጋጁና ምርት ነክ ውሎችን ህጋዊ መሰፈርቶችን አሟልተው በተመዘገቡ አባላት ግብይት የሚፈጸሙበት ገበያ ነው፡፡ ይህ ገበያ ቀልጣፋ፤ ግልጽና ስርዓት ባለው መንገድ የሀገራችንን የግብርና ምርቶች በዘመናዊ መንገድ ያገበያያል፡፡ ለዚህም እንዲረዳው በግልጽ የተዘረዘሩ አሠራሮችና ተግባራቶት ሲኖሩት እነዚህም የአባላት ሥራ አመራር ግብይትና የግብር ሥርዓት፣ የገበያ መረጃ መስጠትና የምርት ግብይት ውሎችን የደረጃ ማውጣትና የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ መስጠት፣ ክፍያና ግዱታ አፈጻጸም፣ የገበያ ክትትልን፣ የአደጋ ቁጥጥር፣ ዋስትናና ክርክር አፈታት ሂደትን በግልጽ በመዘርዘር ለአባላቱ ምቹና ዘመናዊ ገበያ ፈጥሮ የሚሰራ ተቋም ነው፡፡

በዚህም መሠረት በሻጭ ወገን የተመዘቡ አባላቱ የምርት መጠንና ጥራት አረጋግጦ በመረከብ በገዢ ወገን ያሉ አባላቱ ለግብይት የሚሆን በቂ የባንክ ሂሳብ መኖሩን በማረጋገጥ በግልጽ ግብይት ወቅት በሚፈጸሙት ህጋዊ ውል መሠረት ምርትና ገንዘብን ለገዢና ሻጭ በወበቅቱ በማስተላለፍ የሚሰራ ገበያ ነው፡፡ ሆኖም ዘመናዊ ምርት ግብይት እንቅስቃሴ በማስፋፋትና በማጠናከር በኩል ያሉ ውስንነቶችና ተግዳሮቶችን ለይቶ ጠነክሮ መስራት ይጠበቃል፡፡

ከቡና አቅራቢዎችና ላኪዎች ድርጅቱ ላይ ከሚቀርቡ ስሞታዎች ዉስጥ ዋነኞቹ ያንዳንድ ቀማሾች ሥነምግባር ጉድለት በጥራት ደረጃ አሰጣጥን ማዛባቱ፣ ናሙና ለመዉሰድ ብዙ ቀናት ማስጠበቁ፣ ከመድረኩ የተገዛዉ ቡና በርክክብ ወቅት በጥራትም ሆነ በመጠን ቀንሶ መገኘቱ፣ የተለያዩ ባህርይ ያላቸዉ ቡናዎች የመቀላቀል ችግር አስቸኳይ መፍተሔ የሚሹ ናቸዉ፡፡

#### 4.8.3 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

በቡና ንግድ ዘርፍ እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ የጎላ ሲሆን፤ በዋናነትም ከብሄራዊ ባንክ በሚደርሰው መረጃ መሰረት ቡና ላኪዎች የገቡትን ውል መመዝገብ፤የተላከውን ቡና በመጠንና በውጭ ምንዛሪ መጠን በየኤክስፖረተሩ ለይቶ በመመዝገብና የተገኘውን የውጭ ምንዛሪ በማስላት ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ ማሰራጨት ነው፡፡ መስሪያ ቤቱ ለውጭ ገበያ የሚላከውን ቡና አስፈላጊው የጥራትና ተጓዳኝ መስፈርቶች መሟላታቸው ካረጋገጠ በኋላ በፐሎመፐ በማሸግና የታሸጉትንም ተሸከርካሪዎች ወደ ወደብ በፍጥነት እንዲንቀሳቀሱ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡ የሀገሪቱ የቡና ግብይት ስርዓት እስከ ወደብ ብቻ (Free on Board) እንደ መሆኑ መጠን ቡናዎቹን በመረከብ እስኪጫኑ ድረስ ያለው ሂደት የመከታተል ሃላፊነት አለበት፡፡

#### 4.8.4 የኢትዮጵያ አዕምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ጽ/ቤት

ሃገራችን የኢትዮጵያ የአረቢካ ቡና ዘረ-መል ምንጭ እንደመሆኗ መጠን ታዋቂ ልዩ ቡናዎቻችንን በመላው ዓለም ጥበቃ እንዲያገኙ በማድረግ ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ ይገባል፡፡ በልዩ ጣዕማቸው የሚታወቁት አምስቱ ታዋቂ ልዩ ቡናዎች መጠሪያ ስያሜ እንዲያገኙ በተለያዩ ሃገራት በንግድ ምልክትነት ማስመዝገብ እና በተመሳሳይ ሌሎች ሀገራት እንዳይጠቀሙ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ለማስቻል፣ በንግድ ምልክት በማስመዝገብ ቡናችንን በመላው ዓለም በማስተዋወቅ ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ አምስቱ ታዋቂ ልዩ ቡናዎች ሐረር፣ሲዳማ፣ ይርጋጨፌ፣ሊሙ እና ነቀምት የንግድ ምልክቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ፣የተደረጉ ጥረቶች ያሉ ቢሆንም የሐረር፣ሲዳማና ይርጋጨፌ ቡና በውጭ ሃገር የተመዘገቡና እውቅና የተሰጣቸው ይሁን እንጂ የንግድ ምልክቶቹ የባለቤትነት መብት ተጠብቆ ሀገሪቱ እና አምራቹ ህብረተሰብ ከዘርፉ ሊያገኙ የሚገባቸው ተጠቃሚነት ገና ያልተረጋገጠበት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በንግድ ምልክትነት ያልተመዘገቡ ሊሙና ነቀምት ልዩ ቡናዎች እንዲመዘገቡ ለማድረግ የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም አሰስካሁን አውቅናው አልተሰጣቸዉም፡፡

በመሆኑም በዘርፉ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለመፍታትና ጥበቃ ያገኙትን የልዩ ቡናዎች ንግድ ምልክቶች የተወሰነ ግዴታዎችን በመግባትና በፈቃድ ውል ስምምነት /Lisensing/ አማካኝነት እንዲጠቀሙ ለማድረግ ዉስን ያሉ ጥረቶች ቢኖሩም በዘላቂነት ለቀጥል አልቻለም፡፡ ለዚህም ድክመት በዋና ዋና ምክንያትነት ከሚጠቀሱት ተግዳሮቶች ውስጥ፤ በውጭ ሃገራት ሊጠበቁ የሚችሉ የኢትዮጵያ ልዩ ቡናዎች ንግድ ምልክቶችን በውጭ ሃገራት አዕምሯዊ

ንብረት ጽ/ቤቶች በተሟላ መልኩ ያለማስመዝገብ፤የተመዘገቡ ንግድ ምልክቶችን ቡና ገዥዎች የፈቃድ ውል በመፈረም እንዲጠቀሙ ቡናችንን የሚገዙ የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር ድርጅቶች ፈቃድ ውል እንዲፈርሙ ማድረግ፣ በቡና ንግድ ምልክቶቻችን ላይ የሚከሰቱ የመብት ጥሰቶችን መከታተልና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መከላከል፣ የባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በመናበብ በበቂ ሁኔታ ለመስራት አለመቻሉ ናቸዉ፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉትን ጉድለቶች ለይቶ በመፍታት ከተፈጥሮ ሀብታችንን አንዱ የሆነውን ቡናችንን ለዓለም የማስተዋወቅ እና የንግድ ባለቤትነት መብት እንዲያገኙ የተጀመሩ ስራዎች መቀጠልና ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ማድረግ ይገባል ፡፡

## 4.9 ክልል ግብርና ቢሮዎች

በዋና ዋና ቡና አምራች ክልሎች ውስጥ በሚገኙና ቡናን ስፔሻላይዝ በሚያደርጉ ዞኖች፤ወረዳዎችና ቀበሌዎች ላይ በተለየ መልኩ ትኩረት በመስጠት ለቡና ልማት፤ጥራትና ግብይት መሻሻልና እድገት አስፈላጊ የሆኑ የግብዓት አቅርቦትና የተሟላ የሰው ሃይል ምደባ በማካሄድና የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ከሰብሉ ጠቀሜታ ጋር የተገናዘበ አደረጃጀት በመፍጠር እስከ ወረዳ ድረስ ተዘርግቶ ቡና አምራቹ ተገቢዉን ድጋፍ የሚያገኝበትና የአፈጻጸም ክትትል የሚደረግበት አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በግብዓትና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና አጠቃቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣቱ በምርትና ምርታማነት እንዲሁም በቡና ጥራት ላይ ተስፋ ሰጪ ዕድገት እየተመዘገበ መሆኑ በጥንካሬ የሚወሰድ ነዉ፡፡

ይሁንና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ በዉስን ዓመታዊ የምግብ ሰብሎች ላይ ይበልጥ ስለሚያተኩር በክልል፤ በዞን፤ በወረዳና በቀበሌ ያሉ የግብርና አመራሮችና ባለሙያዎች ለቡናዉ ዘርፍ ትኩረት ሰጥቶ በቂ ጊዜና በጀት ተመድቦ መስራቱ ላይ ጉልህ ክፈተት ይታያል፡፡ በመሆኑም በቡና ልዩ ባህርይ ላይ የተመሰረተና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀምን እያሰፋ፣ የቴክኖሎጂዎቹ ዉስንነትን በተግባር እየለየ ለምርምር ሥርዓቱ ባግባቡ ግብረ-መልስ እየሰጠ ለመሄድ የሚያስችል የቡና ልማት፤ምርት ዝግጅትና ጥራትን ያማከለ ዕዉቀትና ከህሎት ባላቸዉ ባለሙያዎች ለቡና አምራቹ በሙያዉ የተሻለ ድጋፍ በማድረግ ዘመናዊ የቡና አመራረትና አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚቸሉበት አቅም የገነቡ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ቡና አምራቹ በዘመናዊ አመራረትና ምርት አያያዝ ላይ ያለውን ክህሎት እንዲያሳደግና በቡና ምርታማነትና ጥራት ላይ ለውጥ በማምጣት ለራሱና ለሀገራችን የበለጠ ጥቅም ለማስገኘት ተገቢውን ድጋፍ ሊሠጡ የሚችሉበት አቅም በመፍጥር ላይ በበቂ ቁርጠኝነት መሥራት ላይ ብዙ ይቀራል፡፡

## 4.10 ክልል ግብይትና ህብረት ሥራ ቢሮ/ ኤጀንሲ

የቡና ምርት ለገበያ በሚቀርብባቸው ቡና አምራች አካባቢዎች ላይ የሚገኙ በየደረጃው ያሉ ግብይትና ህብረት ስራ ማህበራት አካላት የቡና ምርት ዝግጅትና ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን በመከታተልና አርሶአደሩ በህብረት ሥራ ማህበራቱ አማካኝነት ቡናን በብዛትና በጥራት በማቅረብ ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸትና መከታተል ይጠበቅባቸዋል፡፡በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት በማስፋፋትና በማጠናከር ግብይቱ ዘመናዊነትን እንዲላበስ፣ ሻጩና ገዥዉ ነጻ ዉድድር ላይ የተመሰረተ ግልፅና ፍትሃዊ በሆነ ግብይት ሥርዓት እንዲገበያዩ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ ለዘርፉ ቀጣይ ዕድገት እያበረከተ ያለዉ አስተዋጽዖዉ የጎላ ነዉ፡፡

ሆኖም ዘመናዊ ምርት ግብይት እንቅስቃሴ በማሳደግ በኩል የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ አስፈጻሚ አካላትን በመደገፍና አፈጻጸማቸውን በመከታተል፣ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ጥራትን መሠረት ያደረገ የከፍያ ሥርዓት ማስፈን፣ ምርት ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘኖች በግል ባለሀብቶች እንዲገነቡ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፤ ወጥነት ያለው ከክልል እስከ ቀበሌ የሚደርስ የቡና ግብይት መዋቅር እንዲዘረጋ በማድረግና በበጀት በመደገፍ በኩል ከክልል ክልል የሚለያይ ቢሆንም በርካታ ውስንነቶች ይታያሉ፡፡

በየደረጃ ባለው አደረጃጀት የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት አመራርና ፈጻሚ ባለሙያዎችን በበቂ ያለመመደብ፤ የምርት ዝግጅትና ጥራት ቁጥጥር እና የቡና ዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ዝርጋታን ወጥ በሆነ መንገድ ያለመተግበር፤ የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላትን በሁሉም ቡና አምራች አካባቢዎች ያለማቋቋም፤ የግብይት ሥርዓቱ ውስጥ የሚከሰቱ ህገ-ወጥ የግብይት ድርጊቶችን ተከታትሎ ፈጣን እርምጃ ያለመውሰድ አሁንም ትርጉም ባለዉ መልኩ ያልተቀረፉ ክፍተቶች ናቸዉ፡፡

አቅራቢዎች የገዙትን ምርት ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ስለመቅረቡ የሚቆጣጠሩበት ሥርዓት የተቀመጠ ቢሆንም የክልል ፈጻሚዎች ትርጉም ሰጥተው በመከታተል ስለማይቆጣጠሩት ሕጋዊ አቅራቢዎች ጭምር በሕገ-ወጥ መንገድ የኤክስፖርት ቡናን ለሀገር ውስጥ ገበያ እንዲያቀርቡ ክፍተት ፈጥሯል፡፡ አቅራቢን በተመለከተ በየጊዜው እየተገመገመ ሕጉ ላይ ባለው መሠረት የብቃት ማረጋገጫውን መሥርፈት በሚመለከተው ተዘጋጅቶ እንዲተገበር ከየክልሎቹ ወደ ዞኖች የወረደ ቢሆንም የአፈጻጸም ድርጊት መርሐ-ግብር ተዘጋጅቶ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ተዘርግቶ እየተሰራበት አይደለም፡፡

በቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት ሥርዓት ዝርጋታ በወቅቱ የሚታዩና ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለይቶ በመገንዘብና በማቀናጀት ፈጣን የማስተካከያ እርምጃዎች በመውሰድ ሥርዓቱ ወጥ ሆኖ እንዲገነባ ያለማድረግ፤ ከአርሶ አደር ጀምሮ ምርት በወቅቱና በጥራት ለገበያ እንዲቀርብ በየደረጃው ያለው አመራርና ፈጻሚ ባለሙያ በተቀናጀ ሁኔታ በሚፈለገው ደረጃ ያለመንቀሳቀስ፤ ተከታታይ የሆኑ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማዎችን በማድረግ ውጤት እንዲመዘገብ ያለማስቻል፤ የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት ወጥ በሆነ መንገድ ተገንብተው ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡና የአርሶአደር ቡና ምርት ግዢ በእነዚህ ማዕከላት ብቻ እንዲካሄድ ያለማድረግና የመሳሰሉት በግብይቱ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

## 4.11 የአገልግሎት ሰጪዎች

### *4.11.1 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ*

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ለቡናው ኢንዱስትሪ እድገት እያደረገ ካለው አስተዋፅኦ አንፃር የቡናው ኤክስፖርት ንግድ ስርዓት ባለው መንገድ እንዲካሄድና የውጭ ምንዛሪ ገቢን የመቆጣጠር ተግባር ያከናውናል፡፡ ከዚህ አንፃር የቡን ኤክስፖርት ሽያጭ ኮንትራት ሰነዶች በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ እንዲመዘገብ ማድረግ፤ የገዢና የሻጭ የባንክ ለባንክ ግንኙነት በሺያጭ ውል

ሰነድ ትክክለኛነት በማረጋገጥ የውጭ ሀገር መላኪያ የባንክ ፈቃድ መስጠት (Bank Permit) ፡፡ በተጨማሪም የቡና ሻጭና ገዥን ውል ሰነድ ይይዛል፤በውሉ መሰረት ቡና መሸጡንና ገንዘቡ ገቢ መደረጉን ይቆጣጠራል ፡፡ በአንፃሩ በቡናው ንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ በበገዢ እና በሻጭ መካከል የተገባውን ውል እንዲጠበቅ የሚያደርገው ጥረት በቂ ያለመሆን፡፡የቡና ላኪዎችን ለማበረታታት በሚደረጉ አሰራሮች ቡናን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጥ ቀዳዳ መክፈቱና የመሳሰሉ የአሰራር ክፍተቶች ሲሆኑ በተጨማሪም እሴት በጨመሩ የቡና ውጤቶች የመነሻ ዋጋ መወሰኛ/ማነፃፀሪያ ስርዓት (Bench mark) አለመኖሩ ለዘርፉ እድገት አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 4.11.2 ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት

በቡና ግብይት ሰንሰለት ውስጥ ገንዘብ በዋሰትና በማበደር፣በማስተላለፍና በማስቀመጥ በቀጥታም ሆነ በተጓዳኝ አገልግሎት የሚሰጡ የመንግስት፤በማህበር/በአክስዮን የሚሰሩ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው፡፡ የፋይናንስ ተቋማት ለቡና ምርት ዝግጅትና ግብይት፤ መሠረተ ልማት ግንባታ በተለይ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ግንባታ አንጻር የማይናቁ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡ ሆኖም የሚከተሉት ክፍተቶች ይስተዋላሉ፡፡ ለአነስተኛ አርሶ አደሮችና ሰፋፊ ቡና አልሚዎች፣ ለአቅራቢዎች፣ ለላኪዎችና ለሕብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች ለቡና ልማት፣ ግዢ፣ ዝግጅትና ኤክስፖርት የሚያስፈልጋቸው ፋይናንስ በባንኮቹ በኩል ወቅታዊ ገበያን በማጥናትና ለዚህም ዝግጅት በማድረግ በቂ የፋይናንስ አቅርቦት አለመኖር፤ ቡና አልሚዎች ብድር ስለማያገኙ ምርትና ምርታመናተቸዉን ለማሳደግና ጥራት ለማሻሻል አስፈላጊ ግብዓቶችንና ዘመናዊ መሰሪያዎች ያለመጠቀም፣ አቅራቢዎችና የሕብረት ሥራ ማሕበራት የሚያገኙት ብድር በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት የሚገባውን ጀንፈልና እሸት ቡና በተሟላ ሁኔታ ለመግዛት መቸገር፤ እንዲሁም በቡና ኤክስፖርት ኮንትራት ምዝገባ፣ ኤልሲ መቀበልና የኤክስፖርት ሰነዶችን በወቅቱ አዘጋጅቶ በማወራረድ እየተደረገ ባለው የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅልጥፍና ማነስ ዋና ዋና ውሱንነቶች ናቸው፡፡

### *4.11.3 የትራንስፖርትና የትራንዚት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች*

ከየአምራች አካባቢው ቡና ወደ ምርት ገበያ ቅርንጫፍ ማዕከላት በማጓጓዝ እንዲሁም ለኤክስፖርት የተዘጋጀውን ቡና ወደ ወደብ በማጓጓዝና ወደ መዳረሻ አገራት በማስተላለፍ አገልግሎት የሚሰጡ ዘርፎች ናቸው፡፡ አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ እንዲሆን የተደረጉ ጥረቶች በየጊዜው መሻሻሎችን አሳይተዋል፡፡ ሆኖም ገበያውን በተወዳዳሪነት እንዲንቀሳቀስ በማድረግ አንጻር አሁንም ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ ከእነዚህ ክፍተቶች መካከል እሸት ቡና ወደ ማዘጋጃ ማእከላት ለማጓጓዝ የሚያስችል ምቹ ትራንስፖርት ለማግኘት አስቸጋሪ መሆን፣ ቡና ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማዕከላት ለማስገባት በቂ ትራንስፖርት እንዲሠማራ ያለመደረጉ፣ ላኪዎች የገዙትን አቅርቦት ቡና ከየማዕከላቱ ለማጓጓዝም ሆነ ኤክስፖርት ቡና ወደ ወደብ ለማድረስ በሚፈለገው መጠን በወቅቱ የትራንስፖርት አገልግሎት ያለማግኘት፣ የጭነት ትራንስፖርት ታሪፍና የአገልግሎት አሰጣጡ ወጥነት የሌለው መሆን፣ የትራንስፖርት ደላሎች ከፍ ያለ የድለላ ወጪ መጠየቅ፤ በደረቅ ጭነት አገልግሎት ያለው አሠራር በላኪና የደረቅ ጭነት ተሽከርካሪ ባለንብረት በቀጥታ ግንኙነትና ከዚህ ጋር ተያይዞ አስቀድሞ በማቀድና በማስተሳሰር ስለማይሠራ ከፍተኛ የኤክስፖርት ምርት ጭነት በሚኖርብት ወቅት የትራንስፖርት እጥረትና የጭነት ታሪፍ መጨመር በዋናነት የሚጠቀሱ ቡናን በማጓጓዝ እና በማስተላለፍ ሂደት የሚታዩ ችግሮች ናቸው፡፡

### 4.11.4 የቡና ሰርቲፊኬት ሰጪ ድርጅቶች / አካላት

በቡናው ዘርፍ የተለያዩ የቡና ሰርቲፊኬሽን አይነቶች ያሉ ሲሆን እነሱም፡- Fair Trade, Rainforest Alliance,UTZ Certified, 4C, CAFE Practice, Bird Friendly, Organic certification የመሳሰሉት ናቸው፡፡እነዚህ ሰርቲፊኬሽኖች የየራሳቸው መመዘኛ መስፈርት /ስታንዳርድ/ ስለአላቸው በመስፈርቱ መሰረት ቡና እንዲመረትና እንዲዘጋጅ ይፈልጋሉ፡፡ የአብዛኞቹ ሰርቲፊኬሽኖች መስፈርት የሚያተኩረው የአካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረገና ከአካባቢ ብክለት የፀዳ ቡና፤

የተፈጥሮ ሚዛንን ባላዛባ ሁኔታ፤ የተፈጥሮ ደንና የዱር አራዊት ጥበቃንና የአፈርና ውሃ ጥበቃን ማዕከል ያደረጉና እንዲሁም የአምራቹን አርሶ አደርና በጉልበት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞችን ገቢና ጤና፤ የስራ አካባቢ ደህንነትን፤የአሰሪና ሰራተኛ ደንቦች መከበራቸውን ማዕከል ባደረገው ሂደት ውስጥ የሚየልፍ፤ ተከታታይነት ያለው ቋሚና ዘላቂ የሆነ ስነ-ምህዳሩን ጠብቆ የተመረተ ቡናን ለተጠቃሚው መቅረቡን የሚያረጋግጡ ድርጅቶች ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት የቡና ገዢ ደንበኞች ፍላጎትም በየሰርቲፊኬሽን አይነቱ ይለያያል፡፡ በመሆኑም የሰርቲፊኬት ኖርት የተመረተና የተዘጋጀ ቡና በገበያ ዋጋ ላይ ተጨማሪ ዋጋ (Premium price) ስለሚያስገኝና ለዓምራቹ ተጨማሪ የማበረታቻ ክፍያን ስለሚያስገኝ በዘርፉ ለተሰማሩ አርሶአደሮችና ህብረት ስራ ማህበራት ጉልህ ጠቀሚታ ከማስገኘቱም በላይ የቡናን ኤንዱስትሪ ዘላቂነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ ጥራትን ጠብቆ እንዲቀርብ ያስችላል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ድርጅቶች ተቀማጭነታቸው በውጭ ሀገር በመሆኑ ሰርቲፊኬቱን ለማረጋገጥ የሚጠይቁት የአገልግሎት ክፍያ በዓብዛኛው በውጭ ምንዛሪ በመሆኑና በሀገር ውስጥ ይህን ማረጋገጫ የሚሰጡ አካላት ውስንነትና እጥረት ሀገሪቱና አምርቹ በዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡ በመሆኑም ሀገሪቱ እንደ ሌሎቹ የአፍሪካ ሀገሮች ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ሀገር በቀል የሰርቲፊኬሽን ስራ አገልግሎት ሰጪ አካላትና ባለሙያዎች ይህን ስራ እንዲያካሂዱ ማድረግ ይጠበቅባታል፡፡

## 4.12 ሌሎች ባለድርሻዎች

- **yb#Â Bzh¦ ?YwT _b"½ MRMR½ L¥TÂ NGD xUéÒCN** btwsn dr©M b!çN yÍYÂNSÂ t&Kn!K DUF y¸ÃdRg# b!çNM ytqÂj DUF lmS-T ÃlW xdr©jT |‰ãCN btb¬tn h#n@¬ y¸ÃkÂWN bmçn# lDUF xQRïTÂ tGÆ‰êEnT XMB²M xmcE xYdlMÝÝ

- ***xlM xqF½ xHg#‰êEÂ hg‰êE*** yb#Â DRJèC ytqÂj túTæ Ãl¥DrG½ b›lMÂ xF¶µ xqF yb#Â DRJèC ÃlN túTæ kb#Â mg¾n¬CNÂ b›lM ƒSt¾ xrb!µ xM‰Cn¬CN k¸-bqW dr© xNÉR ZQt¾ mçN bg#LH y¸¬Y CGR nWÝÝ

## 5.የቡና ዘርፍ ነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና

ኢትዮጵያ የአረቢካ ቡና መገኛ፤ የብዝሀ-ሕይወት ማዕከል ከመሆኗም ባሻገር ምርቱን ለዓለም ገበያ በማቅረብ ከአፍሪካ ቀዳሚውን ደረጃ ስትይዝ፤ ከዓለም ቡና አቅራቢዎች ደግሞ በጠቅላላዉ በአምስተኛ በአረቢካ ቡና በሦስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ የሀገራችን የቡና ምርት 95% የሚደርሰዉ አራት ሚሊዮን በሚሆኑ አነስተኛ አርሶአደሮችና ቀሪዉ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ በባለሀብቶች በኋላቀርና ልማዳዊ የአመራረት ዘይቤ በጫካ፣ በከፊል ጫካና በጓሮ በተከላ ቡና የአመራረት ስርዓቶች የሚለማ በመሆኑ ምርቱ፤ ምርታማነቱና የጥራት ደረጃዉ ከለ✍ሎች ቡና አምራች አገሮች ጋር ሲወዳደር በጣም አነስተኛ ነዉ፡፡በጫካ ቡና ከሚለማዉ ቡና መሬት 7-10% የሚሸፍን ሲሆን፤በደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ እንዲሁም ደቡብ ምስራቅ የሃገሪቱ ክፍሎች በተለይም በቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ጅማ፣ ካፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ማጂና በባሌ ዞኖችን ይገኛል፡፡ ከፊል ጫካ ቡና ተክልም እንደዚሁ በአብዛኛው በደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኝና እስከ 35% የአገራችን የቡና ይዞታ እንደሚሸፍን ይገመታል፡፡የጓሮ ቡና ተክል በየአርሶ አደሩ መኖሪያ አከባቢ የሚገኝና ከጠቅላላው የቡና ይዞታ 50% ድረስ የሚሸፍን ሲሆን አብዛኛው በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብና ምሥራቅ የሃገራችን ክፍሎች የሚለማ ነው፡፡በዘመናዊ የቡና

ልማት የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች፣ ተስማሚ የተከላ ርቀት፣ ጉዝጓዝና ኬሚካል መጠቀም፤ አረምና የጥላ ዛፍ ቁጥጥር ሥራ እንዲሁም ምቀሳና ጉንደላ የመሳሰሉ የቡና ተክልና ማሳ እንክብካቤ ሥራዎች በተሻለ ሁኔታ ይካሄዳል፡፡ ከጠቅላላው 5 - 7% የሚሸፍን ሲሆን በዋናነት በሰፋፊ የግልና እርሻዎች ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ እና ፀረ-አረም ኬሚካልን በከፊል ጥቅም ላይ በማወል የቡናን ልማት ያካሂዳል፡፡

ምንም እንኳን የሀገሪቱ ኤኮኖሚ ምሰሶ በሆነዉ የግብርና ክፍለ ኤኮኖሚ ዉስጥ ቡና የዉጭ ምንዛሪ በማምጣት ያለተወዳዳሪ መሪነቱን ለረዥም ዓመታት ይዞ በመቆየት አንጋፋነቱን ያረጋገጠ፤ ሩብ የሚሆነው ህብረተሰባችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ኑሮው በቡና ዘርፍ ባሉት እንቅስቃሰ✍ዎች ላይ የተመሰረተና ለሰብሉ መስፋፋት አመቺ የተፈጥሮ ሁኔታዎች ያሉ ቢሆንም አገሪቱ በዓለም ቡና ገበያ ላይ ያላት ድርሻ ከ 3% ያልበለጠ ከመሆኑም ባሻገር ማግኘት የሚገባትን ያህል ጥቅም ከዘርፉ ሳታገኝ መቆየቷ ይታወቃል፡፡

ቡና በኤኮኖሚ ልማታችን ዉስጥ ከሚጫወተዉ ወሳኝ ሚና አኳያ ምርታማነቱንና ምርቱን ከእጥፍ በላይ ለማሳደግና ጥራቱንም በከፍተኛ ሁኔታ ለማሻሻል የተጣለዉ ግብ ከሌሎች የግብርና ወጪ ንግድ ምርቶች ግብ ሁሉ የላቀ ነዉ፡፡ ስለሆነም በማስፋት ስትራቴጂያችን ከፍተኛ የኤኮኖሚ ጠቀሜታ ላላቸዉ ሰብሎች በተሰጠዉ ልዩ ትኩረት መሰረት በቡና ልማት ባለፉት ዓመታት አበራታች ዉጤቶች የታዩ ቢሆንም የተሻሻሉ የአመራረት ቴክኖሎጂዎቸን በማስፋት ረገድ ያሉትን ጉድለቶች በትክክል ለይቶ በመፍታት የላቀ ዉጤት ለማስመዝገብ በወሳኝ መልኩ ገና ብዙ መሰራት እንዳለበት አያጠያይቅም፡፡ በዚህም መሰረት በሀገራችን የቡናን ምርት፤ ምርታማነትና ጥራት መቀንስ ዘርፉን ሊያዳክሙ የሚችሉ በርካታ ተግዳሮቶች ያሉትን ያህል ጠንካራ ጐኖችና ለዕድገቱ መልካም አጋጣሚዎች አሉ፡፡እነዚህን በቡና ልማቱ እና ንግዱ ተጠቃሚ የሆኑትን ባለድርሻዎችና በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ  አካላት ዉስጣዊ ጥንካሬዎችና ድክመቶች እንዲሁም ዉጫዊ እድሎችና ስጋቶች በመተንተን አዎንታዊ ጎኖችን በበለጠ በማስፋት አሉታዊ ተጽእኖዎችን በማስወገድ ግባችንን ለማስካት ርብርብ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

***ሠንጠረዥ 5፡ የቡና ዘርፍ  ጥንካሬ፣ ድክመት፣ ምቹ ሁኔታና ስጋቶች ትንተና***

| **ጥንካሬዎች** | **ድክመቶች** |
|---|---|
| - የግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲያችንና የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂያችን በኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገታችን ዉስጥ ከሚጫወተዉ ወሳኝ ሚና ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እንዲደገፍ በመንግሥት ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱ፣ | - የቡናው ዘርፍ ከሚሰጠው ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ አኳያ በየደረጃው ባሉ አስፈፃሚ አካላትና ባለሙያዎች ከአፈጻፀም አንፃር  የተሠጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን፤ |
| -በዘርፉ ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ የሰዉ ኃይል የተሰማራ መሆኑ፣ | -  ኋላቀርና ልማዳዊ የአመራረት ዘይቤዎችን በተሻሻሉ የቡና አመራረት ዘዴዎች ለመተካት ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በስፋትና በፍጥነት ለተጠቃሚዉ የሚደርሱበት በቡና ባህርይ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የኤክስቴንሽን ድጋፍና የመረጃ ሥርዓት ያለመኖር፣ |
| - በርካታ የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች፣ የአመራረትና ምርት አዘገጃጀት የምርምር ውጤቶች መኖራቸው፣ | - ለየስነምህዳሩ ተስማሚ የሆኑና የተጠቃሚዎችን  ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የቡና አመራረት ቴክኖጂዎችን<br>በጥራትና በብዛት ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅና የማሰራጨት ሥራ አዝጋሚ መሆን፤ |
| - የቡና ልማት ለአረንጓዴ ልማት (Green economy) የሚያበረክተው ከፍተኛ አስተዋጽዖ ለዘላቂ ልማታችን ያለዉ ጠቀሜታ ዓለም አቀፍ እውቅና እያገኘ | |

| | |
|---|---|
| መምጣቱ፣<br><br>- አርሶአደሮች ካላቸዉ የረጅም ጊዘ✍ የቡና አመራረት ልምድና ባሕል መኖሩ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት ለመቀበልና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ፣<br><br>- ዘመናዊ የቡና ግብይት ሥርዓት በመዘርጋቱ የቡና አምራች ገበሬዎች በህብረት ሥራ (ዩኒየን) ተደራጅተው እንዲሁም አልሚ ባለሀብቶች ምርታቸውን ለዓለም ገበያ በቀጥታ በማቅረብ ወይም ለአቅራቢዎች ግልጽና ፍትሃዊ በሆነ አሰራር በመገበያየት የንግድ አድማሳችንን ለማስፋት አበራታች ጅምሮች መኖራቸዉ፣<br><br>-የቡና አምራች እና ላኪዎች በማህበር ተደራጅተዉ በተለያዩ ዓለምአቀፍና ሀገራዊ መድረኮች በመሳተፍ አቅማቸዉን በማሳደግ ረገድ የተጠናከረ ልምድ ማግኘት እያደገ መምጣቱ፣“<br><br>-የአገራችንን ቡና በዓለም አቀፍ ደረጃ የማስተዋወቅ ሥራ በግሉ ዘርፍ የተሻለ መሠራቱ”<br><br>-በብሔራዊ ደረጃ የቡና ላቦራቶሪ እና የጥራት ምርመራ ማዕከላት መቋቋማቸው፣<br><br>-የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በተደራጀ ሁኔታ መቋቋሙ<br><br>-የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት መቋቋማቸው፣ | - ለቡና ተስማሚ ሆኖ በለ✍ሎች ሰብሎች የተያዘና ያለማ መሬት በመለየት የአካባቢን የተፈጥሮ ሁነ✍ታዎች ባገናዘበና የለ✍ሎች ሰብሎችን ሚዛን በማያዛባ መልኩ የቡና ልማትን ለመስፋፋት የተደራጀ የገጠር መሬት አጠቃቀምና የአፈር ለምነት መረጃ ያለመኖር፣<br><br>- በተለያዩ የቡና ሥነ-ምሕዳራት ከቡና ጋር በተጓዳኝነት (በደባልነት) ወይም በአማራጭነት ለሚመረቱ ሰብሎች የተሰጠው የምርምርና የኤክስቴንሽን ትኩረት በቂ አለመሆን፤<br><br>- ጠንካራ የቡና ምርጥ ዘር አቅርቦት፣ የቡና ዘረ-መል ጥበቃና ቁጥጥር እንዲሁም ፍትሐዊ ልውውጥና አጠቃቀም ሥርዓት ያለመኖር፣<br><br>- በቡና አመራረት፤ አዘገጃጀት፣ በቡና ጥራት ቁጥጥር እና ግብይት ላይ የሚወጡ ፓኬጆች፣ ማኑዋሎች መመሪያዎችና ደንቦች ላይ የሚሰጡ ወቅታዊና ተከታታይ ሥልጠናዎችና ተግባራዊ ያለመደረግ፤<br><br>- ለቡና አምራቾችና የግብይቱ ተዋንያን የብድርና የግብአት አቅርቦት እንዲሁም የሎጂስቲክስ ድጋፍ በበቂ ሁኔታ ያለመመቻቸት፤<br><br>- የቡና ምርምር፣ ልማትና ግብይት ተዋንያን በሰዉ ሀይልና በማቴሪያል አቅም ያለመጠናከርና ቅንጅታቸዉ የላላ መሆን፣<br><br>- የቡና ገበያ ጥናትና ልዩ ልዩ ጣዕም ያላቸው ቡናዎች ምርት የማስተዋወቅና የንግድ ስያሜ የማሰጠት ሥራ የተጠናከረ ያለመሆን፤<br><br>- በዓለም ገበያ የቡና ዋጋ ሲያሽቆለቁል ለአምራቹ እና ግብይት ተዋንያኑ ማካካሻ ሥርዓት (Risk Management System) ያለመኖር፣ |
| ***ምቹ አጋጣሚዎች*** | ***ሥጋቶች*** |
| - የአረቢካ ቡና የተፈጥሮ መገኛ በመሆኗ ባህርያቸው እጅግ ከፍተኛ ልዩነት<br>ያላቸው የቡና ጀርምፕላዝም ምንጭነት ለዘላቂ ልማት፣ ለብዝሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ ለኢኮ-ቱሪዝምን ለማስፋፋት ከአጋሮች የልማት ድጋፍ ለማግኘትና ተባብሮ ለመሥራት ምቹ መሆኑ፣<br><br>- በጣዕማቸው በዓለም ገበያ የታወቁ፣ ተፈላጊ/ተወዳጅ የሆኑና የንግድ ስያሜ የተሰጣቸው በርካታ የቡና ዓይነቶች ባለቤት መሆናችን፣<br><br>- ለቡና ልማትና ምርታማነት ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ሥነ-ምህዳራት መኖራቸው፣<br><br>- በህብረተሰቡ ዘንድ የቆየና የዳበረ ማህበራዊና ባህላዊ እሴትነት ያለዉ መሆኑ፣<br><br>በአለም ገበያ እያደገ የሚሄድ ከፍተኛ የቡና ፍላጎት መኖሩ፣<br><br>- የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች መዋዕለ- | åRUn!K b#Â §Y GL} y±l!s! xQÈÅ ÃlmñR<br><br>- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የዝናብ ስርጭት መዛባትና ማነስ፣ የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር፣ የጫካ ቡናች መመናመን ፤የበሽታችና ነፍሳት ተባዮች ክስተቶች መበራከትና፣ የመሳሰሉት ሁኔታዎች መከሰት፣<br><br>- በወይና ደጋማ አከባቢዎች በህዝብ ብዛት ማደግ ባስከተለዉ የመሬት ጥበት በህገወጥ መንገድ በተፈጥሮ ቡና ጫካዎች የእርሻ መሬቶችን ማስፋፋት የቡና ዘረ-መል ቋት ይዘት እያመናመነ መሆኑ፣<br><br>- የተለያዩ ባህርያት ያላቸው የአካባቢ ቡና ዝርያዎች በተሻሻሉና በተመረጡ ጥቂት ዝርያዎች ያለጥንቃቄ እየተተኩ መምጣት፣<br><br>- የአገሪቱን በጣም ሰፊ የቡና ብዝሀ-ሕይወት ሀብት ከጥፋት ለመታደግ የሚፈለገውን ያህል እንዲሰበሰብና ወይም እንዲጠበቅ ያለማድረጉ፣<br><br>- የአለም የቡና ዋጋ መዋዠቅ በልማትና ግብይት ሂደት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፣<br><br>- በዓለም የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት የአረቢካ ቡና ተጠቃሚዎች በዝቅተኛ ዋጋ ወደሚያገኙት ሮቡስታ ቡና ተጠቃሚነት እያዘነበሉ መምጣት፣ |

| | |
|---|---|
| ነዋያቸውን በዘርፉ ኢንቨስትመነት ላይ ለማዋል የሚያደርጉት ጥረት እየጨመረ መምጣቱ፣ | - የንዑስ ዘርፉ አደረጃጀት የቡና ኤክስቴንሽን ምርምሩንና ግብይቱን ከተገል?ዮችና ከሌ✍ሎች ባለድር☆ አካላት ጋር የሰብሉን ሀገራዊ ጠቀሜታ በሚመጥን ደረጃ ተናበና ተቀናጅቶ ለመሥራት ያለማስቻል |
| -yxRîxdéCÂ yÆlhBèC túTæÂ yt&KñlÖ©! F§¯T m=mR | • bb#Â bZh HYwT _b" §Y bh#l#M ÆlDRšãC Xk#L GN²b@ ¥ÈT<br>• L¥t$N GBYt$NÂ l@lÖC ÆlDRšãC l!ÃStúSR y¸CL xdr©jT xlmñR<br>• bb#Â x!NdST¶ Æl# ygbÃ sNslèC xSt¥¥" mr© xlmñR<br>• yW+ PéjKT bjT xlmñRÂ hg¶t$ kM¬gßW yW+ MN²¶ yMTmDbW bjT xnSt¾ mçN<br>• béb#S¬ xm‰rTÂ GBYT ymNGST ±l!s! xlmñR<br>• bqE ymsrt L¥T GNÆ¬ xlmñR<br>• tlêê+ ymêQR lW_<br>• ytšl x¥‰+ Ã§cW sBlÖC mSÍÍT<br>• yhgR WS_Â yWÀ µ*‰N¬YN xlmñR<br>• yb#Â GND xDRQ b>¬ mSÍÍT |

## 6.የቡና ልማትና ጥራት ወሳኝ ተግዳሮቶች

በሃገራችን ያለውን የቡና ልማት ነባራዊ ሁኔታ ስናየው ከ80% የማያንሰዉ በኋላ ቀርና ባህላዊ የአመራረት ዘይቤ እየለማና እየተመረተ ስለሚገኝ ምርትንና ምርታማነትን ሊያሳድጉ እንዲሁም ጥራትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ተከታታይነትና ተያያዥነት ያላቸው የተሻሻሉ የአመራረት ዘዴዎች በስፋት እየተተገበሩ አይደሉም፡፡ ስለሆነም እንደ ሞዴል የቡና አምራች አገሮች ምርቱን፤ ምርትማነቱንና የጥራት ደረጃዉን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥና ተግባራዊ ማድረግ ግድ ይላል፡፡ በዚህም መሰረት በአሁኑ ወቅት ካለው የቡና ምርት፤ ምርታማነት፤ ጥራትና ግብይት አበይት ችግሮች በመነሳት የቡና ልማት፤ ጥራትና ግብይት ተግዳሮቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 6.1 የምርትና ምርታማነት ችግሮች

#### 6.1.1 ለቡናው ንዑስ ዘርፍ የተሠጠው ትኩረት አናሳነት

በየደረጃው ያለው አመራርና ፈጻሚ ባለሙያ በተቀናጀ ሁኔታ የቡናን ምርት፣ምርታማነት፣ጥራትና ግብይት በሚፈለገው ደረጃ እንዲካሄድ ያለመንቀሳቀስ፤ ተከታታይ የሆኑ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማዎችን በማድረግ አበራታች ውጤት እንዲመዘገብ ያለማስቻል፤ ለቡናዉ ዘርፍ በቂ የሰዉ ኃልና በጀት ተመድቦ በቡና ልዩ ባህርይ ላይ የተመሰረተና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀምን እያሰፋ፣ የቴክኖሎጂዎቹ ዉስንነትን በተግባር እየለየ የቡና ልማትና ጥራትን ያማከለ ዘመናዊ የቡና አመራረትና አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎችን በስፋትና ቀጣይነት ለተጠቃሚ ለማድረስ የሚያስችል አሰራር አልተፈጠረም፡፡ የቡና ግብይት በአዋጁ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ብቻ እንዲካሄድ ያለማድረግ፣ በዘመናዊ የቡና አመራረትና ምርት አያያዝ ላይ ሰብል ካሌንደሩን ተከትሎ ተገቢው የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲሰፋ በየደረጃዉ ያሉ አመራሮችና የግብርና ባለሙያዎች በቂ ድጋፍ ሊሠጡ የሚችሉበት አቅም በመፍጥር በቁርጠኝነት በመሥራት ረገድ ውስንነቶች ይታያሉ፡፡ ለአብነትም በከፍተኛና መካከለኛ ቡና አምራች ዞኖችና ወረዳዎች ብዙዎቹ የቡና፣ ሻይና ቅ/ቅመም ልማትና ጥራት ክፍት የሥራ መደቦች ለረዥም ጊዜ በባለሙያ ያልተያዙ በመሆናቸዉ ለአርሶ አደሩ በዘመናዊ ቡና አመራረትና አዘገጃጀት ስራ ላይ በቂ ድጋፍና ክትትል እየተደረገለት አይደለም፡፡

#### 6.1.2 ከኋላቀር የአመራረት ዘይቤዎቹ የሚያላቅቅ ጠንካራ የድጋፍ ክትትልና ግብረ- መልስ ሥርዓት ያለመኖር

በአብዛኛዎቹ ቡና አብቃይ አካባቢዎች እየተተገበሩ ካሉት ኋላቀርና ልማዳዊ የቡና አመራረት ዘይቤዎች የተነሳ የአገራችን የቡና ምርትና ምርታማነት ዕድገት ብዙም ለውጥ ሳያመጣ ከክልል ክልል ቢለያይም በአማካይ 7.5 ኩ/ል በሄ/ር ያልበለጠ

ስለሚመረት ከሌሎች ዋና ዋና ቡና አምራች ሀገሮች ባነሰ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ካለፉት ሶስት አስርተ ዓመታት ወዲህ በየስነ-ምህዳሩ የተለዩና በምርታማነትና በሽታን በመቋቋም የሚታወቁ የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች በምርምር የወጡ ቢሆንም ስርጭቱና ተደራሽነቱ ከአንዳንድ ሞዴል አርሶአደሮች ባለፈ የሁሉንም ቡና አምራች አርሶአደሮች ፍላጎት ማሟላት ከሚያስችልበት ደረጃ አልደረሰም፡፡ እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በምክረ-ሀሳቡ መሠረት በስፋት በማዳረስና ግብዓቶችን በማቅረብና በመጠቀም ምርቱን እንዲያድግ በማድረግ በኩልም ሆነ የተሻሻሉ የቡና አመራረትና የምርት ዝግጅት ዘዴዎችን በስፋት ለመጠቀም የሚያስችል በቡና ባህርይ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ የኤክስቴንሽን ድጋፍና ክትትል ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡

ለአብነትም ሰው ሰራሽ ማዳበሪያን በመጠቀም ረገድም ለቡና ተክል እድገትና ምርት በዋናነት አስፈላጊ የሆኑ ንጥረነገሮች ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ በምርምር ተረጋግጦ ያለ ቢሆንም አርሶአደሩ በስፋት እንዲጠቀምባቸው በማድረግ ረገድ ብዙ አልተሄደበትም፡፡ በአጠቃላይ የተለያዩ የቡና አብቃይ ሥነ-ምሕዳራትን ያማከሉ የቡና ዝርያዎችን፣ የተ☆☆ሉ የቡና አመራረት ዘዴዎችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን በሚፈለገው መጠን ያለማስፋት የሀገሪቱ ቡና ምርት፤ ምርታማነትና ጥራት ማነቆዎች ሆነዉ በስፋት ይታያሉ፡፡

ቡና እንደሚደረግለት ያልተቋረጠ እንክብካቤ ለምሳሌ በመስኖና ከፍተኛ ማዳበሪያ በመጠቀም በዉስን ማሳዎች ከ50 ኩ/ል በላይ ምርት ሊሰጥ እንደሚችል ከቬትናምና ብራዚል ልምድ ቢታወቅም፣ ከዋና ዋና አምራች ሀገሮች አማካኝ ምርታማነት የኛ ከ30-60% ያነሰ ነዉ (ሰንጠረዥ 6)፡፡ በቡና በምርትና ምርታማነት እንዲሁም በምርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተ💻እኖ ከሚያሳድሩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል የቡና ተክል ቁመት ያለመገራትና አላስፈላጊ እድገቶችን በወቅታዊ ምቀሳና ገረዛ ያለመቆጣጠር፤ በአንድ ማሳ ባሉ የቡና ዛፎች መካከል የዕድሜ✍ና የዝርያ ልዩነት መኖር፣ በቡና ዛፎች መካከል ያለዉ የተከላ ርቀት ያለመስተካከል፣ ያልተስተካከለ የጥላ መጠን፤ በቂ ያልሆነ የአረም፣ የበ⚍ታዎች እና ተባዮች ቁጥጥር እንዲሁም የአፈር ለምትና ዕርጥበት ማሻሻያ ዘዴዎች አጠቃቀም ናቸዉ፡፡ በነዚህም ምክንያቶች የተነሳ የቡናችን ምርታማነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

***ሠንጠረዥ 6. የተመረጡ ቡና አምራች ሀገሮች አማካይ የቡና ምርታማነት***

| ተ.ቁ | ሀገር | ምርታማነት (ኪ/ግ በሄ/ር) |
|---|---|---|
| 1 | ቬትናም | 2347 |
| 2 | ብራዚል | 1257 |
| 3 | ሁንዱራስ | 1066 |
| 4 | ኢትዮጵያ | 743 |
| 5 | ኡጋንዳ | 598 |

*ምንጭ፡ ዓለም አቀፍ ቡና ድርጅት (ICO, 2011)*

በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በየክልሉ፣ በየዞኑ፣ በእያንዳንዱ የቡና አምራች ወረዳና ቀበሌ ያሉትን የቡና ይዞታዎች በአመራረት ዘይቤ፣ በቡናዎች እድሜና ዝርያ አይነት፣ በተከላ ርቀት፣ በማሳ አያያዝና ግብአት አጠቃቀም፣ በአፈር ለምነትና ርጠበት ሁነ✍ታ፣ በመሬት እንዲሁም ተዳፋትነት፣ ለቡና ተስማሚ የሆነ ሥነ-ምህዳር ለይቶ የሚገልፅ ዝርዝርና ወቅታዊ የሆነ ተጨባጭ የመረጃ ሥርዓት መኖር ለልማቱና ግብይቱ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ቢሆንም በተደራጀ መልኩ የተያዘበት ሁኔታ የለም፡፡ በመሆኑም በሀገራችን ያለዉን የቡና ይዞታ የመሬት ስፋትና የአመራረት ዘይቤ፣ ዓመታዊ የምርት መጠንና ምርታማነት በተመለከተ የተለያዩ የሀገር ዉስጥና ዓለም አቀፍ ምንጮች በየወቅቱ የሚያወጡት መረጃ የተለያየ ነዉ፡፡

### 6.1.3. አብዛኛው የቡና ተክል ያረጀና ተገቢውን እንክብካቤ የማያገኝ መሆን

አብዛኛው ከነባርና ከተሻሻሉ ዝርያዎች የተተከሉ ቡናዎቻችን ኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸዉን የጨረሱና በእርጅና ምክንያት በመዳከማቸዉ ለቡና ምርትና ምርታማነት መቀነስ ዋነኛ ምክንያት የሚሆንበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ እነዚህን ቡናዎች በጉንደላ ማደስ ካልሆነም ነቅሎ ከተመሳሳይ ዝርያ በተዘጋጀ ችግኝ መተካት እንደሚቻል የሚታወቅ ቢሆንም ትርጉም ባለዉ መልኩ ሲተገበር አይታይም፡፡

በሃገራችንና በሌሎች በቡና ልማት በሚታወቁ ሃገሮች በምርምርና አርሶ አደር ማሳዎች የተደረጉ ሙከራዎች እንደሚያረጋግጡት ያረጀ ቡናን በማደስ ምርታማነትን ማሻሻል ቢቻልም ጉንደላ አዋጭ ቴክኖሎጂ የሚሆነዉ እንደቡናው ዝርያ ዓይነት፣ ዕድሜና ጤናማነት፣ በአተገባበሩ ላይ በምንወስደዉ ጥንቃቄ፣ ከጉንደላ በኋላ የሚወጡትን ቅጥያዎች ለማስተካከል በምናደርገዉ ክትትል፣ አረምና ተባይ ቁጥጥር፣ እንደዚሁም ጉዝጓዝና ማዳበሪያ በአግባቡ ከተሟሉለት ብቻ መሆኑ ላይ የግንዛቤ እጥረትና የአመለካከት ችግር በሰፊዉ ይስተዋላል፡፡

ጉንደላ ሲታቀድ በሥራዉ የሚሳተፉ አርሶ አደሮች አምነዉና ፈቅደዉ እንዲገቡበት ስለማይደረግ ለዉጤታማነቱ የሚጠይቀዉን እንክብካቤ ማድረግ ላይ ሰፊ እጥረት አለ፡፡ እንዲሁም በቀደምት ጊዜያት በዘመቻ ያለ በቂ ጥንቃቄ በተካሄዱ የጉንደላ ሥራዎች በተወሰኑ አከባቢዎች የቡና ግንድ አድርቅ በሽታን ከማዛመት ጋር በማያያዝ አርሶአደሩ ጉንደላ መፍትሔ መሆኑን አምኖና ፈቅዶ እንዲቀበል ማድረግ ላይ እስካሁን የተፈጠረዉ እምነት አለ የሚባል አይደለም፡፡

በለ✍ሎች ዋና ዋና ቡና አምራች አገሮች በጥሩ ሁኔታ የተያዘ የአንድ ቡና ተክል የምርታማነት ዕድሜ ከ25 ዓመት የማይበልጥ ሲሆን በአገራችን ግን እስከ 50 ዓመትና ከዚያም በላይ ዕድማ✍ ያላቸዉ የቡና ዛፎች በጫካ ከፊል ጫካና በ⮙ሮና ተካላ ቡና ማሳዎች ዉስጥ በስፋት ይታያሉ፡፡ የቡና ዛፍ የምርታማነት ዕድማ✍ እንደ አካባቢዉ የአየር ⌨ባይና የአስተዳደጉ ፍጥነት የሚለያይ ቢሆንም፣ በማንኛዉም ሁነ✍ታ አብዛኛዉ ቅርንጫፎቹ ከምርት ዉጭ ሲሆኑና ምርታማነቱ ማ⫝ቆልቆል በሚጀምርበት ዕድማ✍ ላይ ሲደርስ ካልታደሰ ወይም በአዲስ ተከላ ካልተተካ በስተቀር ምርታማነቱን ጠብቆ ማቆየት አይቻልም፡፡ እንደዚህ ያሉ የቡና ዛፎች ምርታማነታቸዉን ከማጣት ባ☆ገር የምርቱ ጥራትም በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስ አያጠራጥርም፡፡

### 6.1.4 *ሥነ-ምህዳርን ያማከሉ የቡና አመራረት ቴክኖጂዎች አቅርቦትና አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆን*

የብሐ✍ራዊ ቡና ምርምር ፕሮግራም በእስካሁኑ ሂደት የቡናን ምርት፣ ምርታማነትና ጥራትን ሊያ☆⫝ሉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን አፍልቆ ለተጠቃሚዉ እያሰራጨ ያለ ቢሆንም በሀገሪቱ ያለዉን ገበያ ተኮር፣ ዘመናዊና የተ☆☆ለ የቡና አመራረት ቴክኖሎጂ ፍላጎት በሚፈለገዉ መጠንና ዓይነት በበቂ ሁነ✍ታ ማርካት አልቻለም፡፡ በአብዛኛዉ ለአንዱ የቡና አብቃይ ሥነ-ምሕዳር የወጣ ቴክኖሎጂ ለለ✍ላ የተለየ አካባቢ ሊያገለግል ስለማይችልና በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አገልግሎት ላይ ቢዉል በምርትና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተ💻ዕኖ ሊያሳድርና የምርቱ ጥራት ደረጃ የአካባቢዉን ቡና የማይወክል ስለሚሆን፣ ለየስነምህዳሩ ተስማሚ የሆኑ (Agro-ecology specific)፣ የገበያዉንና የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የቡና አመራረት ቴክኖጂዎችን በጥራትና በብዛት በቀጣይነት ማፍለቅ አስፈላጊ ነዉ፡፡

በአገሪቱ ልዩ ልዩ ቡና አምራች ክልሎች ባሉ የአርሶአደር የቡና ይዞታዎች በተለይም በ⮙ሮ ማሳዎች እንደየሥነ-ምሕዳሩ አመቺነት የተለያዩ የአገዳ፣ የብርዕ፣ የአትክልትና ፍራፍረ✍፣ የስራስር፤ የጥራጥሬና የቅመማቅመም ሰብሎች በአብዛኛዉ ከቡና ጋር በደባልነት ሲመረቱ ይታያል፡፡ ይህ አሰራርና የአመራረት ልምድ አመታዊ የምግብ አቅርቦትን ከማረጋገጥ፣ አረምን ከመቆጣጠር፣ የመሬት ምርታማነትን ከማሳደግ፣ የሰብል ምርትን ከማስፋት፣ ከማሳዉ የሚገኘዉን ገቢ ከመጨመርና

የአፈርን ለምነትና ርጥበት ከማ☆☆ል ወይም ዉጠ✍ታማ በሆነ መንገድ ከመጠቀም አኳያ ዘርፈ ብዙ ጠቀማ✍ታ ስላለዉ የሚደገፍ ነዉ፡፡ ነገር ግን የደባል ወይም የአማራጭ ሰብሎችን ባሕርይ በማወቅና ከቡና ጋር ለማልማት ተስማሚነታቸዉን በማረጋገጥና በማስፋት ረገድ ምርምሩና አ✍ክስቴንᏑኑ ለተለያዩ ሥነ-ምሕዳራት ገና ብዙ መስራት ይጠበቃል፡፡

ምንም እንኳን ¾u<“ U`U` KG<K<U u<“ ›wnÃ ¡MK<‹“ Y’-UIÇ^ƒ }eTT> ¾J’<“ ¾u<“” U`ƒ፣ U`ታT’ƒ“ Ø^ƒ ¾T>Á☆ᏑK< ,¡•KAÍ=-‹” uum“ k×Ã’ƒ vK¨< G<’@ታ Tp[w vÃ‹MU' ቀደም ሲል ያወጣቸዉና በእጅ ያሉ ቴክኖጂዎች ሊሰሩ በሚችሉበት ሥነ-ምሕዳራት ላሉ ተጠቃሚዎች በሚፈለገዉ ጥራትና መጠን ሙሉ ለሙሉ አልተሰራጩም፡፡ uGÑ^‹” ¾u<“ U`ƒና U`ታማነት•¾T>ÁdÉÑ<፣ ጥራትን የሚያሻሽሉ ¬Ö?ታT ,¡•KAÍ=-‹” ŸU`U` ðØ• uSkuM ûŸ?Ï ›É`Ô“ ŸU`Ø }V¡a Ò` kUa“ ›hiKA u›?¡e,”i’< uŸ<M k×Ã’ƒ vK¨< G<’@ታ•K}ÑMÒ¿ uTp[w ²Lm }ÖnT>’ƒ” T[ÒÑØ ኦ”Ç=‰M um ¾S<Á“ ¾KAÍ=e+¡e ÉÒõ አልተÅ[ገU፡፡ ለአብነትም uU`U` ¾T>¨Ö< ¾u<“ ´`Á-‹” u›Óvu< ›v´„ K}KÁ¿ ¾u<“ ›wnÃ ¡MKA‹ ¾T>Ác^ß uQÓ ¾}ᏩᏩS S”ÓYታ©U J’ S”ÓYታ© ÁMJ’ ›ካል ›KS•` ›”Æ“ ¨d˜ ¡õ}ƒ ’¬፡፡ ለዚህ ችግር አቢይ ምክንያት የምርምርና አ✍ክስቴንᏑን ግንኙነት የሚፈለገዉን ያህል ጠንካራና ወጥነት ያለው ያለመሆንና አገልግሎት አሰጣጡም ቡና ቋሚ ሰብልና የኤክስፖርት ምርት መሆኑን ያገናዘበ ስላልሆነ ነዉ፡፡

### 6.1.5 የቡና ልማትን ለማስፋፋት የመሬት አጠቃቀምና መረጃ ሥርዓት ያለመዘርጋት

በሃገራችን ከአፋርና አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ሱማሌ በስተቀር በሁሉም ክልሎች ቡናን ለማልማት ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለቡና ልማት በጣም ተስማሚ የሆነ ከ5 ሚሊዮን ሄ/ር በላይ መሬት የደቡብና ደቡብ ምዕራብ አከባቢዎች በአማራና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች ዉስጥ እንደሚገኝ እንዲሁም በመካከለኛ ደረጃ ለቡና ልማት ሊዉል የሚችል ከዚህ ዕጥፍ የሚልቅ መሬት በነዚህ ክልሎችና በትግራይ ክልል ተሰራጭቶ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ የአካባቢን የተፈጥሮ ሁነ✍ታዎችና የለ✍ሎች ሰብሎች ልማትና የተለያዩ አገልግሎቶች ፍላጎትን ባገናዘበ መልኩ ለቡና ተስማሚ ሆኖ ባግባቡ ያለማ መሬትን በመለየት የቡናን ልማት ለማስፋፋት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ በቂ አይደለም፡፡

በአንፃሩ የሀገራችንን የቡና ይዞታ፣ በቡና ዝርያ፣ እድሜና የአተካከል ስርዓት የያዘ መረጃ በትክክል ያልተለየበት እና በየሰብሉ ዓይነት ሊለማ የሚችል መሬት ስፋት በዝርዝር ቢታወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለዉ መገመት ባያዳግትም በሀገራችን እነዚህን መረጃዎች ለማግኘት የምንችልበት የመረጃ ሥርዓት የለም፡፡

### 6.1.6 የግብአትና የብድር አቅርቦት ያለመኖር

#### 6.1.6.1 ጠንካራ የቡና ምርጥ ዘር አቅርቦት ሥርዓት ያለመኖር

K¾Y’-UQÇ\ }eTT> ¾J’< uiታ”“ }vÃ”“ ›c†Ò] G<’@ታ-†” SssU ¾T>‹K< Ÿõ}— U`ƒ ¾T>cÖ<“ Ø\ Ø^ƒ/×°U ÁL†¨< uU`U` }[ÒÓÖ¨< ¾¨Ö< ¾}hhK< ¾u<“ ´`Á-‹ uum SÖ”“ uØ^ƒ ›v´„/›²ÒÏ„ K}ÖnT>¨< ÁKTÉ[e Ÿõ}—¨<” É`h ¾T>Ã´ ¾U`ƒ“ U`ታT’ƒ T’q ኦ”ÅJነ }KÃ…M፡፡

K²=IU ኦ”Åª’— S”e¯@ ¾T>¨cÅ¬ u›Ñ]~ u<“” Ákð ¾²` Y`¯ƒ ÁKS•` c=J” G<K<›kõ ¾²` e`¯ƒ“ Å”w uS”ÓYƒ ተግባራዊ ሆኖ ²Lm SõƒH@ XeŸT>Ñ˜ É[e ‹Ó\” KSp[õ“ ¾}ËS[¨<” ¾MTƒ ኦ”penc? KTekÖM Ãቻ M ²”É ›G<” ÁK<ƒ” ¾u<“ ²` U”à‹“ ›Sታ© ¾²` T²ÒËƒ ›pT†¨<” KÃ„ T¨p“ u²=I S[Í LÃ uSS`¢´ ¾Teóóƒ eƒ^‚Ï¨<” S”Åõ }ገu= ÃJ“M፡፡

uGÑ^‹” ÁK¨<” ¾u<“ ²` ›p`xf H>Åf e”SKŸf ¾u<“ U`U` T°ŸLf& ¾›`f ›Å` TX-‹“ S”ÓYታ©“ S”ÓYታ© ÁMJ’< ¾ÓM ¾u<“ ኢ`h-‹ ኢ”Å²` U”ß’f c=ÁÑKÓK< ኢ”Å’u` Ãታ¨nM:: u}KÃU up`w Ñ>²? ÁK< S[Í-‹ ኢ”ÅT>ÁSK¡~f ¾ÏT Ów`“ U`U` T°ŸM“ ¾u<“ }¡M MTf É`Ï„‹ ›pU uðkÅ SÖ” ¾u<“ ²` ኢÁS[~ K}ÖnT>¨< እያቀ[u< u=J”U um J• ›M}Ñ–U:: ¾²=IU U¡”Áf wH@^© ¾u<“ U`U` T°ŸM ¾²` ´ÓÏf” ŸእØ[~ ›ኳያ u}ÚT]’f ¾T>c^ ኢ”Í= ኃላፊነቱ ሆኖ um ¾u<“ Td •af“ ›eðLÑ>¬” uËf }SÉxKf ›ÃÅKU:: ¾u<“ }¡M MTf É`Ï„‹U ኢ”Å²=G< uª‘’f u<“” ›U`„ ¾SgØ ¯LT ›”Óu¬ ¾T>c\ uSJ’< KiÁß ¾T>Ák`u<f ²` uª‘’f Ÿ^d†¬ õLÔf vKÃ c=ÁS`~ ’¨<:: eKJ’U u’²=I ›"Lf ¾T>S[}¨<“ uiÁß ¾T>k`u¨< ¾²` SÖ” u¾›S~ ÁK¨<” õLÑAf Ÿ2®% ÁKð ›Ãgõ”U፡፡

#### 6.1.6.2 የብድርና የግብአት አቅርቦት ሥርዓት ያለመኖር

¾u<“” U`f“ U`ታT’f KTdÅÓ“ Ø^f ለThhM ብሎም ¾ÓwÃ~” ¨<Ö?¬T’f KT[ÒÑØ ¾T>Áe‹M ¾wÉ`“ አቅርቦት ያለመመቻቸት እና ¾Ów›f ›p`xf Y`¯f ያለመኖር በተለይም የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ፤ የእርሻ መሳሪያዎች፤ ለምርት ዝግጅት ስራ አስፈላጊ የሆኑ የማድረቂያ ፤ማከማቻና የቡና መያዣ ቁሳቁሶች አቅርቦት እጥረት መኖር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ X”Ç=G<U ›=”Æef]¨< u}KÁ¿ U¡”Á„‹ (በቡና ዋጋ መዋ✈ቅ/ ማ♎ቆልቆልና በለ✍ሎች ክስተቶች) }ÓÇaf ኢ”ÇÁÒØS¨<፣ ካጋጠመውም Ñ<Ç~” KSk’e ¾T>Áe‹M ¾›ÅÒ SssT>Á eMf ላይ በቂ እና ወቅታዊ የሎጅስቲክና ስልጠና ድጋፍ uT>ðKÑ¬ SÖ”“ u}Ñu=¬ S”ÑÉ ÁKSS‰†f በዘርፉ እድገት ላይ አሉታዊ ተ🖳ዕኖ አሳድሯል፡፡

#### 6.1.7 በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ያልተለመዱ ክስተቶች መበራከት

የተፈጥሮ ሀብት በተለይ የደን መመናመን፣ የዓለም አየር ንብረት መቀያየርና የአካባቢ አየር ፀባይ ለውጥ ችግር እየተባባሰ መምጣት የተለያዩ ያልተለመዱ ክስተቶችን እያስከተለ ነዉ፡፡ ከነዚህም ክስተቶች መካከል የዝናብ እጥረት (የተራዘመ የደረቅ ወራት) እና የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር፣ በሀገሪቱ ዉስጥ ቀደም ሲል ያልታዩ የቡና በ♎ታዎችና ተባዮች መከሰት እንዲሁም የቡና ተክል ተፈጥ⑤ዊ የአስተዳደግ ስርአትና ሂደት ባሕርያት መዛባት (Physiological disorders) ዋና ዋናዎች ናቸዉ፡፡

በሀገራችን በተለይም በደጋማና ወይና ደጋማ ቡና አብቃይ አካባቢዎች የምርት ጥፋት እያስከተለ የነበረዉን የቡና ፍሬ በሽታ ችግርን ለመግታት በተደረገዉ ጥረት በሽታዉን በተፈጥሮ መ➿ም የሚችሉ የቡና ዝርያዎች በምርምር መገኘታቸዉ በዘርፉ እድገት ደረጃ የታየዉ አንዱና የመጀመያዉ ትልቅ እርምጃ ነዉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዝርያዎች በሁሉም የሀገሪቱ ቡና አምራች ሥነ-ምሕዳራት እኩል የመላመድና የምርታማነት 🖮ባይ ስለሌ✍ላቸዉ ችግሩን ሙሉ በሙሉ መቅረፍ ስልተቻለ አሁንም አልፎ አልፎ እስከ 20% ጉዳት ሲያደርስ ይስተዋላል፡፡ በሌ✍ላ መልኩ ደግሞ ለየሥነ-ምሕዳሩ ከአካባቢዉ የቡና ዝርያዎች በሽታዉን መ➿ም የሚችሉና ከፍተኛ ምርትና ጥራት ያላቸዉን ለይቶ የማዉጣቱ ሥራ አበርታችና ተስፋ ሰጭ ዉጤቶችን እያሳየ ሲሆን በሽታዉን የመቋቋም ችሎታቸዉን ለማሻሻል የተጠናከረ ምርምር እየተካሄደ ይገኛል፡፡

እንደዚሁም የቡና ግንድ አድርቅ በሽታ በአገራችን በተለያዩ የቡና አምራች አካባቢዎች በሁሉም የቡና ይዞታዎችና የአመራረት ዘይቤዎች በፍጥነት እየተዛመተና በዘርፉ እድገት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተ🖳ዕኖ እየፈጠረ ያለ ሲሆን የበ♎ታዉ አምጭ ተዋስያን ወደ ቡናዉ ግንድ የሚገቡት በዋናነት በቆሰሉ ቀዳዳዎች መሆኑ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በ♎ታዉን የሚ➿ሙ የቡና ዝርያዎች እስካሁን በሃገራችን ያልተገኙ በመሆናቸዉ ያለዉ ጊዜያዊ መፍትሐ✍ በባሕላዊና በተፈቀዱ 🖮ረ-ፋንገስ መድሐኒቶች አቅም በፈቀዳ መጠን መከላከል ነዉ፡፡ በአረም ቁጥጥር ጊዘ✍ የቡናዉን ግንድ በገጀራ

ያለማቁሰል፣ ከመገጀር ይልቅ አፋኝ ሰብሎችንና ጉዝ⮙ዝን እንዲሁም ⌨ረ-አረም ኬሚካል እንዳመቺነቱ በመጠቀም አረምን መቆጣጠር፣ በቡና ምቀሳ፣ ገረዛና ጉንደላ ወቅት የምንጠቀማቸዉን መሳሪያዎች በሚገባ ማ💻ዳት አማራጩና አዋጩ የመከላከያ ዘደ✍ መሆኑ እና በለ✍ላ መልኩ ደግሞ በ⛼ታዉን የሚ✂ሜሙና ምርታማ የሆኑ የቡና ዝርያዎችን ለየአካባቢዉ ማፍለቅ እንደ ዋነኛ የምርምር ስትራቴጂያዊ አቅጣጫ መያዝ ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

የነዚህና የለ✍ሎች በ⛼ታዎችና ተባዮች ስርጭት በብዛት የሚታየዉ በጫካ፤ በከፊል ጫካና በጓሮ ቡናዎች ሲሆን እነዚህ ቡናዎች ደግሞ የሰብሉ ከፍተኛ የብዝሀ-ሕይወት ክምችትና የተለያዩ ባሕሪያት ያላቸዉ ዘረመል ማዕከላት በመሆናቸዉ፣ በነዚህ አካባቢዎች ጠባብ የዘረ-መል መሰረት ያላቸዉና በሽታን መ✂ሜም የሚችሉ ጥቂት ዝርያዎች ያለቅድመ ጥንቃቄ ቢስፋፉ የብዘሃ-ህይወት መጥፋት አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 6.1.8 የቡና ብዘሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ ፍትሐዊ ዘ ረ መል ልውውጥና አጠቃቀም ያለመጠናከር

በቡና ብዘሃ ህይወት ጥበቃ፣ልዩ ልዩ ባሕርያት ያላቸዉ የአካባቢ ቡና ዝርያዎች የጫካ፣ የከፊል ጫካና የጓሮ ቡናዎች በልዩነታቸው መሠረት ተሰባስበው በእዘ-ቦታ (ex-situ conservation) ወይም በአካባቢያቸው (በዘቦታ) እንዲጠበቁ (in-situ conservation) በማድረግ ጥናት ሳይካሄድባቸው በፊት እንዲነቀሉና ሌሎች ሰብሎች ወይም አዳዲስ የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች እንዲተኩ የማድረግ አዝማሚያዎች ጎጂነት ቀላል አይደለም፡፡

## 6.1.9. የዘርፉ አደረጃጀት ችግር

የኢትዮጵያ ቡና ኢንዱስትሪ ከ50 ዓመት በፊት በግብርና ሚኒስቴር ስር በሥራ ክፍል ደረጃ ተዋቅሮ ሥራዉን የጀመረ ሲሆን በሂደት ሲታይ በዚህ ሁኔታ በቂ አገልግሎት እንደማይሰጥ ስለተረጋገጠ ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ አንድ ወጥ አመራር እንዲኖረዉ ተወስኖ የኢትዮጵያ ቡና ቦርድ ተቋቁሞ የቡና ልማቱንና ግብይቱን አጣምሮ ለ18 ዐመታት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ቦርዱ እራሱን ችሎ በመንቀሳቀሱ ለቡናው ልማትና ጥራት የቡና ተክል ማሻሻያ ፕሮጀክት ስራ ላይ እንዲውል ከማድረጉም ባሻገር የቡናውን ግብይት ለማሻሻል የቡና ቅምሻ ላቦራቶሪና የቡና ጨረታ ማዕከል እንዲቋቋም አድርጓል፡፡ ቡና ቦርድ እየተጠናከረና ተጨማሪ ሃላፊነቶችን እየወሰደ ስለመጣ ተቋማዊ አደረጃጀቱ እስከ ቡናና ሻይ ልማት ሚኒስቴር ደረጃ ደርሶ የነበረ ሲሆን ከብዙ የአወቃቀር ለዉጦች በኋላ ከ2003 በጀት ዓመት ጀምሮ የቡና ልማትና ጥራት ቁጥጥሩ በግብርና ሚኒስቴር፤ ግብይቱ ደግሞ በንግድ ሚኒስቴር ስር ተዋቅሮ እየሰራ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ የቡናው ዘርፍ የተፈለገውን ያህል ወደፊት እንዳይራመድ ካደረጉት ተግዳሮቶች መካከል የተቀናጀና ጠንካራ የምርምር፣ የልማትና የግብይት አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ያለመኖር ዋነኛው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም የቡና ምርምር፣ ልማትና ግብይት በተበታተነ የአደረጃጀት መዋቅር ሥር ሆነው በፌዴራል ደረጃ ከመመራታቸውና በክልሎችም ወጥነት የሌለው አወቃቀር ከመኖሩ በተጨማሪ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በየደረጃዉ የሚሳተፉባቸው የጋራ የቡና መድረኮች የሉም ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን አሰራር ለማ☆☆ል፤ ቅንጅታዊ እንቅስቃሰ✍ን ለማጠናከርና የቡናዉን ዘርፍ እድገት ለማፋጠን መንግሥት ካለዉ ፍላጎት የተነሳ የአደረጃጀት መዋቅር ለዉጥ በባለሙያዎች ተጠንቶ ለዉሳኔ እንዲቀርብለት ያደረገ ቢሆንም አስፈላጊነቱ ከዚህ ስትራቴጂ ሰነድ በብቃት ከመተግበር አኳያ የሚቃኝ ይሆናል፡፡

## 6.1.10. የአቅም ግንባታ ድጋፍ በበቂ ሁኔታ ያለመመቻቸት

በቡና ምርታማነትና ጥራት ያሉትን ምቹ ሁኔታዎችና ቴክኖሎጂዎች አሟጦ በመጠቀም ቁልፍ ችግሮችን መፍታት የሚቻለው አርሶ አደሩን በዘመናዊ የቡና አመራረት፣ ጥራት አጠባበቅና ግብይት በቂ ግንዛቤና እምነት የሚፈጥርለት የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሠጥ ብቁ ባለሙያ ሲኖር ነዉ፡፡ በመሆኑም በምርምርም ሆነ በልማቱና በጥራቱ በቂ የሰለጠነና ልምድ ያካበተ የሰው ሃይል አለመኖር፤ ተከታታይና በቂ የሙያ ስልጠና አለመሰጠት፤ ያለውን የሰው ሃይል በአግባቡ ያለመያዝና ያለመጠቀም፤ ከፍተኛ ተመራማሪዎችና ባለሙያዎች የተ☆ለ ክፍያ ወዳለባቸዉ ለ✍ሎች መ/በ✍ቶች ፍልሰት መበራከት፤ ለምርምር የተማ♉ሉ በ✍ተ-ሙከራዎች እና የመሰተዋት ቤቶች አለመኖር፤ ለመስክ ስራ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ፋሲሊቲዎችና የበጀት እጥረት፤በዘርፉ የሚሰተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ናቸዉ፡፡

በአንፃሩ የሰብሉን ቋሚ ተክልነት ባህሪ ያገናዘበ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ከልማት ሰራተኛ እስከ ከፍተኛ ባለሙያ ድረስ የሚፈለገዉን የሰዉ ኃይል አቅም በፈቀደ መጠን በጀት በመመደብ በቅጥርና በተከታታይ አቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ለመሙላት የተሠጠዉ ትኩረት በቂ ነዉ ሊባል አይችልም፡፡ በየደረጃዉ ላሉት አዳዲስና ነባር ባለሙያዎች ይህን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችሉ የአጭርና ረዥም ጊዜ የሥራ ላይ ሥልጠናዎች የተሠጠዉ ትኩረት አነስተኛ ነዉ፡፡

## 6.2 ጥራትና ግብይት ተግዳሮቶች

### 6.2.1 ሥነ ምህዳሩን ያማከሉ የተሻሻሉ የቡና ምርት አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ አጠቃቀምና ግንዘቤ ዝቅተኛነት

የታጠበና ያልታጠበ ቡና በሀገሪቱ የተለመዱ የቡና አዘገጃጀት ሂደቶች ሲሆኑ ከአለቃቀም፤ ከአዘገጃጀትና ከአያያዝ ጋር በተያያዙ ችግሮች የቡና ጥራትን በማሻሻል ረገድ መሰረታዊ ለውጥ ሊመጣ አልቻለም፡፡ በ2005 በጀት ዓመት ለገበያ ከቀረበው 150.5 ሺህ ቶን ያልታጠበ ቡና (ከጠቅላላዉ 72 %)

ዉስጥ 97% የሚሆነው ከደረጃ 4 በታች ያለ ሲሆን በዋናነት ለዝቅተኛ የጥራት ደረጃ መንስኤዎቹ ከአለቃቀም፣ ከአደራረቅና አከመቻቸት ጋር በቀጥታ የተያያዙ ችግሮች ናቸው፡፡ በአንፃሩ የታጠበ ቡና የጥራት ደረጃ ካልታጠበ ቡና ሁኔታ ጋር ሲታይ የተሻለ ቢመስልም ለታጠበ ቡና ከምንጠቀምባቸው የተሻሻሉ ግብዓቶችና አዘገጃጀት ዘዴዎች አካ♉ያ ሲታይ እሱም ብዙ መሻሻል በማሳየት ላይ ያለ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ይህም ልክ እንዳልታጠበ ቡና ችግሮቹ የሚከሰቱት በምርት አቀባበልና አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎች አያያዝና አጠቃቀም ጉድለት ምክንያት ነው (ሠንጠረዥ 7)፡፡

ቡና በተለያዩ ሥነ-ምህዳራት የሚመረት ሰብል እንደመሆኑ ከአካባቢዉ የአየር ▭ባይ ጋር የተዛመደ የቡና አዘገጃጀት ዘደ✍ና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ችግሮች ይታያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከፍተኛ የአየር እርጥበት ባለቸው እንደ ምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ባሉ አካባቢዎች በተለይ የደረቅ ቡናን (ጀንፈል) በተመለከተ የምንጠቀምባቸው የቡና አዘገጃጆቶች በመካከለኛውና በደቡብ አካባቢዎች ከምንጠቀማቸው ተመሳሳይ ስለሆነ ከፍተኛ የቡና ምርት ካለባቸዉ የሚቀርቡ ቡናዎች በጥራት ይዘታቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ ናቸዉ፡፡

***ሠንጠረዥ 7፡* በ2005 ዓ.ም ለማዕከላዊ ገበያ የቀረበ የኤክስፖርት ቡና ጥራትና መጠን***

| የቡናዝግጅትዓይነት | መጠን<br>በቶን | ድርሻ<br>በመቶኛ | የጥራት<br>ደረጃ | መጠን<br>በቶን | ድርሻ<br>በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| የታጠበ ቡና | 57790.09 | 27.75 | ልዩ ቡና (Speciality) | 6304.12 | 10.90 |
| | | | መካከለኛ ደረጃ | 50175.01 | 86.82 |
| | | | ዝቅተኛ ደረጃ | 1310.95 | 2.28 |
| ንዑስ ድምር | | | | 57790.09 | 100 |
| ያልታጠበ ቡና | 150480.28 | 72.25 | ልዩ ቡና | 1551.77 | 1.03 |
| | | | መካከለኛ ደረጃ | 79991.91 | 53.16 |
| | | | ዝቅተኛ ደረጃ | 68936.59 | 45.81 |
| ንዑስ ድምር | | | | 150488.03 | 100 |
| ጠቅላላ | | | ልዩ ቡና | 7855.89 | 3.77 |
| | | | መካከለኛ ደረጃ | 130166.92 | 62.5 |
| | | | ዝቅተኛ ደረጃ | 70247.54 | 33.73 |
| | | | ድምር | 208278.12 | 100 |

*) ልዩ ቡና ከ80% በላይ፣ መካከለኛ ደረጃ ከ50-79% እና ዝቅተኛ ደረጃ ከ19 - 49% አማካይ የጥራት ውጤት ያለዉ ነዉ፡፡

በመካከለኛውና በደቡብ አካባቢዎች በታጠበ ቡና ኢንዱስትሪዎች የምንጠቀምባቸው አብዛኛዎቹ ቴክኖሎጂዎች ጊዜ ያለፈባቸውና ያልተሻሻሉ በመሆናቸዉ ለከፍተኛ ምርት ብክነትና ጥራት መጓደል ተጋልጠዉ ይገኛሉ፡፡ ሌላው ፈታኝ ችግር የሆነው ለታጠበም ሆነ ለደረቅ ቡና ማድረቂያዎች እና ለማከማቻነት የምንጠቀምባቸው መጋዘኖች በተገቢው መመዘኛ የተሰሩና በሚፈለገው መጠንና ቦታ የሚገኙ ባለመሆናቸው ለምርት ብልሽትና ጥራት ጉድለት አስተዋጽኦ ማድረጋቸዉ ነዉ፡፡

የጥራት ምርመራ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ወጥና ተመጋጋቢነት ያለው ተግባር ሊሆን ሊገባው በሃገሪቱ ያለው የጥራት ቁጥጥርና ክትትል ሥራ በተለያዩ አደረጃጀቶች የተዋቀረና በውስን የሰው ሃይልና ትኩረት የሚከናወን ነው፡፡ በመሆኑም የጥራት ቁጥጥሩ በሚፈለገው መጠንና ሁኔታ ከላይ እስከ

ታች ድረስ በወጥነት ተዘርግቶ ባለመጠናከሩ በቀላሉ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎባቸው ሊስተካከሉ የሚችሉ የጥራት ችግሮች ይታያሉ፡፡ በተጨማሪም ይህ የአሰራር ሂደት በመረጃ አያያዝና ግብረ መልስ ስርዓት ክፍተቶችን በመፍጠሩና ለጥራት መሻሻል ግብዓት የሚሆን የተጠናከረና ተመጋጋቢ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዳይኖር በማድረግ ሀገሪቱ ካላት አቅም አንጻር በዘርፉ ብቁና ተወዳዳሪ ሆና በዓለም ገበያ እንዳትቀርብ ከሚያደርጉ አይነተኛ ተግዳሮቶች መካከል አንዱ ነዉ፡፡

## 6.2.2 እንደየአካባቢው ሥነ-ምሕዳር ልዩ ባህርይና የጣዕም ይዘት ያላቸው ቡናዎች በጥናት ያለመለየት

አንድ ሀገር ያላትን ልዩ የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡና በሚፈለገው መጠን በቀጣይነት መጠቀም የምትችለው የሀብ•ን ስርጭት በመጠንና በዓይነት በአግባቡ ለይታና ትኩረት ሰጥታ በማስተዋወቅ የተጠቃሚዎችን ፍላጎትና እርካታ ስታረጋግጥ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ የአረቢካ ቡና ብዝሃ ህይወትና ልዩ ባህርይ በአግባቡ በሥነ-ምሕዳር መለየትና ትኩረት ሰጥታ በመስራት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ልዩ ጥቅም እስካሁን በሚገባ ልታገኝ አልቻለችም፡፡ ቀደም ሲል በተደረጉት እንቅስቃሴዎች አንዳንድ የሀገራችን የቡና ዓይነቶች (ሀረር፣ይርጋጨፌ፣ ሲዳማ፣ ጉጂ፣ ባሌ፣ ጅማ/ሊሙና ወለጋ ያሉ) በአለም ገበያ ላይ እዉቅና በማግኘት እየተለመዱ መምጣታቸውና በዚህም የተነሳ እየተገኘ ያለው ጥቅምና ተፎካካሪነት በዘርፉ ያሉ ጅምር ሥራዎች ምን ያህል ተጠናክረዉ መቀጠል እንዳለባቸዉ በጉልህ የሚያሳይ ቢሆንም ተጠቃሚነታችንን በስፋት ለማረጋገጥ ብዙ ሥራዎች ይቀሩናል፡፡

ኢትዮጵያ ቡና በጣዕምም ሆነ በይዘቱ በአለም እጅግ ተወዳጅ መሆኑ በሚደረጉ የቡና ጣዕም ውድድሮች የተረጋገጠ ነው፡፡ እያደገ ከመጣዉ የቡናዎቻችን የጥራት ደረጃና የቡናችን በዓለም ተጠቃሚዎች ዘንድ ተወዳጅነት ጋር የሚመጣን ዋጋ በዓለም ገበያ ስለማይከፈል ከዘርፉ እየተገኘ ያለው ጥቅም ካለን እምቅ የብዝሃ-ሕሃይወት ሀብትና ልዩ ጣዕም አንጻር አነስተኛ ነው (ሰንጠረዥ 8)፡፡

ለዚህም ዋነኛ ምክንያቶች የገበያ ማፈላለግና ማስፋፋት እንዲሁም ተከታታይና ጥልቀት ያለው የማስተዋወቅ ሥራ ውስንነት፣ ልዩ ባህርይና ጣዕም ያላቸዉ የቡና አይነቶችን በዝርዝር ለይቶ ማወቅ፤ ማስመዝገብና ከባለቤትነት መብት ጋር የተያያዙ እውቅናና ለ✍ሎች ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት አለመቻልና ለዘርፉ ተገቢዉን ትኩረት አለመስጠት ናቸው፡፡

**ሡንጠረዥ 8፡ የታጠበ ቡና አቅርቦት መጠንና ደረጃ በማዕከል (2004/05ዓ/ም)**

## 6.2.3 የአቅርቦትና የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራ ደረጃ ምደባ ተመጋጋቢ ያለመሆን

በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ የቡና ገዢዎቻችን የሚጠቀሟቸው ቴክኖሎጂዎችና የጥራት ማረጋገጫ ዘዴዎች

| ማዕከል | መለኪያ | ደረጃ | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Q1 | Q2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | ደረጃ በታች | ድምር | % ድርሻ |
| ዲላ | ቶን | 58.01 | 2039.27 | 6584.06 | 1509.23 | 180.78 | 114.49 | 67.12 | 39.10 | 28.15( | 288.58 | 10908.81 | 18.88 |
| | % | 0.53 | 18.69 | 60.36 | 13.83 | 1.66 | 1.05 | 0.61 | 0.36 | 0.26 | 2.64 | 100 | |
| ሃዋሳ | ‘’ | 193.4 | 1041.53 | 21265.78 | 7796.25 | 1419.7 | 557.4 | 147.0 | 17.83 | 25.18 | 435.54 | 32889.68 | 56.91 |
| ሶዶ | ‘’ | 0 | 124.52 | 860.68 | 97.32 | 51.79 | 0.66 | 0 | 1.48 | 0 | 0.03 | 1136.51 | 1.97 |
| ጅማ | ‘’ | 0 | 562.58 | 2916.0 | 1283.63 | 154.89 | 55.75 | 2.29 | 1.17 | 0 | 13.13 | 4989.44 | 8.63 |
| ቦንጋ | ‘’ | 39.97 | 2037.6 | 1064.66 | 606.45 | 306.62 | 59.91 | 0.06 | 5.38 | 0 | 61.07 | 4181.72 | 7.24 |
| በደሌ | ‘’ | 0 | 0 | 80.81 | 145.17 | 43.45 | 26.42 | 0 | 0 | 0 | 0 | 295.86 | 0.51 |
| ጊምቢ | ‘’ | | 38.03 | 550.29 | 138.45 | 0 | 0.74 | 0 | 0 | 0 | 0 | 727.52 | 1.26 |
| አ/አ | ‘’ | 0 | 169.2 | 1220.27 | 552.51<br>78.24 | 452.52 | 78.24 | 16.51 | 46.13 | 15.59 | 99.56 | 2650.55 | 4.51 |
| ድምር | ‘’ | 291.38 | 6012.74 | 34542.6 | 12129.0 | 2609.77 | 893.64 | 233.0 | 111.1 | 68.92 | 897.91 | 57790.09 | 100 |
| ድርሻ | % | 0.5 | 10.4 | 59.77 | 20.99 | 4.52 | 1.55 | 0.40 | 0.19 | 0.12 | 1.55 | 100 | 100 |

እጅግ በጣም በጠበቀ ሁኔታ የምግብ ደህንነትን ሊያረጋግጥ ከሚችል የቁጥጥር ስርዓት አኳያ የተቃኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ለምግብና ለመጠጥ የሚጠቀሙባቸውን ጥሬ ዕቃዎች የሚያስገቡባቸው ሀገሮች የምግብ ደህንነትን የሚያረጋግጥ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓትና በዘመናዊ መልኩ የተደረጁ ላቦራቶሪዎች ያላ♉ቸው መሆኑን እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ይጠቀሙበታል፡፡ ነገር ግን በሀገር ደረጃ ያለን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ በሰው ሃይልም ሆነ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም የተጠናከረ ካለመሆኑም በተጨማሪ የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች እጅግ በጣም ያረጁና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚፈለገውን ዝቅተኛ መስፈርት እንካ♉ን ሊያሟሉ በሚችሉ ሁኔታ ላይ አይደሉም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጥራት መመዘኛ መስፈቶች ውስን ሁኔታዎችን ብቻ የሚያሳዩና ከአለም አቀፍ የጥራት መመዘኛ ፍላጎት አንጻር የተሻሻሉ አይደሉም፡፡

በተጨማሪም የአቅርቦትና የኤክስፖርት የጥራት መስፈርቶች ተቀራራቢና ተመጋጋቢ ባለመሆናቸው በጥራት መረጃ አቀባበልና አጠቃቀም ላይ ተፅእኖ ከመፍጠራቸዉ በላይ በአለም አቀፍ የቡና ጥራት ቁጥጥርና ተወዳዳሪነት አንጻር ዓይነኛ

ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ እንደዚሁም የተጠናከረና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቡና ጥራት ላቦራቶሪ አለመኖሩ የተለያዩ ለቡና ጥራት ኢንዱስትሪው እሴት የሚጨምሩ ምርምሮችን ለማካሄድና ጠቃሚ ምክረ-ሃሳቦችን ለማፍለቅ ያላስቻለ ሲሆን እሴት በመጨመር የቡናዉን ኢንዱስትሪና ገበያዉን የበለጠ ማስፋፋትና ማጠናከር እንዳይቻል የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

ኢትዮጵያ ዉጭ የምትልከዉን ምርት ጥራት በተመለከተ ከተጠቃሚው የምናገኘዉ ግብረ መልስ ለቀጣይ ሥራችን መሻሻል አይነተኛ ሚና እንዳለው አያጠያይቅም፡፡ ከዚህም አንጻር ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በብዙ ሃገራት ለሚገኙ ገዢዎችና ደንበኞች ቡና የምትልክ ቢሆንም ገዢዎቻችን ስለገዙት ቡና ጥራትም ሆነ ሌሎች ሁኔታዎች የሚገልጹ ወጥነት ባለው መልኩ የተማከላ መረጃ ስለማይልኩ ክፍተቶቹን ለመድፈንና ጥንካሬዎችን የበለጠ ለማጎልበት የሚያስችል ሥርዓት በተደራጀ መልኩ ተዋቅሮ ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡

### 6.2.4 ዘመናዊ የቡና ግብይት ስርዓት ተጠናክሮ ያለመተግበር

ረጅም ቅብብሎሿና ኋላቀር የገበያ ስርአት የግብይት ወጪዎችን በማናር ለቡና አምራቹ የሚደርሰውን የዓለም ቡና ዋጋ ድርሻ ከፍ እንዳይል አንቆ የኖረውን ባህላዊ የቡና ግብይት ወደ ዘመናዊነት ለማሸጋገር የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ቁጥር 602/2000 እና ደንብ ቁጥር 161/2001 ወጥተው ተግባራዊ በመሆናቸዉ እንደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የመሰሉ ዘመናዊ የግብይት መድረክ ተፈጥሮ አበራታች ውጤት እያሳየ ቢሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላትና ያለው የቡና ግብይት ሂደት የሁሉንም የግብይት ተዋናዮች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ሙሉ በሙሉ ያረጋገጠ አልሆነም፡፡ ይኸውም ስለ ዘመናዊ ግብይት ጠቀሜታ በሁሉም አርሶ አደር ዘንድ እኩል የሆነ ግንዛቤ በበቂ ሁኔታ ካለመፈጠሩ፤ የግብይት ተዋንያን አዲሱን ስርዓት በተሟላ መልኩ ተቀብለው እየተገበሩ ካለመሆኑና የቡና አቅራቢነት ላይ የተሰማሩ የህብረት ስራ ማህበራትና ግለሰቦች የፋይናንስና የአቅም ውሱንነት ካለመቀረፉ እንዲሁም በየደረጃዉ የተቋቋመው የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት ግብረኃይል ኃላፊነቱን በአግባቡ የሚወጣበት አቋም ላይ ካለመሆኑ ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ነው፡፡

የቁጠባና ብድር ባህልና ተደራሽነት ውሱን በመሆኑና በሚፈለገው መጠንና ወቅት አለመገኘቱ ህገወጦች አጋጣሚውን በመጠቀም በአበባ ደረጃ የሚገኝ ቡናን ሳይቀር ማሳ ላይ ምርቱን በመግዛትና ወዳልተፈቀደለት አካባቢ በማጓጓዝ እንዲሁም ከማይመሳሰለው የአካባቢ ቡና ጋር በመቀየጥ ቡናዎቻችንን የሚታወቁበትን ልዩ ባህርይ እስከ ማሳጣት የሚያደርስ ጥፋት የሚፈጽሙ ስግብግቦች እንዲያንሰራሩ ምቹ አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል፡፡

### 6.2.5 የቡና ዋጋ አለመረጋጋትና ማካካሻ ሥርዓት ያለመኖር

በተደጋጋሚ የዓለም ቡና ዋጋ በተለያዩ ምክንያቶች አንዴ ከፍ አልያም ከተጠበቀው በታች ዝቅ ሲል አምራቹ፣ አቅራቢውም ሆነ ላኪው አንዴ ሲጠቀም ሌላ ጊዜ ከተጠበቀው በላይ ሲጎዳ ለተለያዩ የባንክ ዕዳዎች ሲጋለጥ አንዳንዴም ከገበያ ውጭ እስከመሆን ሲያደርስ ይታያል፡፡ ይህንን እጅግ ፈታኝ የሆነ ተግዳሮት ትርጉም ባለው መልኩ ለመቋቋም፤ አልያም የጉዳቱን መጠን ለመቀነስ (Risk Management System) በሚያስችል መልኩ ስልት ቀይሶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በእውቅና ሰጪ ድርጅቶች ሰርቲፊኬት የሚያገኙ ቡናዎች በአለም ገበያ ከሚሸጠው የቡና ዋጋ እስከ 20% እና ከዚያም በላይ ተጨማሪ የመሸጫ ዋጋ እንደሚያገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በዚህም መሰረት በዓለም ገበያ የኦርጋኒክ ቡና ፍላጐት በየአመቱ ከ10% በላይ ዕድገት ያሳያል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ኢትዮጵያ ለዚህ የንግድ ዘርፍ አዲስ እንደመሆኗ ያለው ጠባብ የገበያ ዕድል ለመጠቀምና የአምራቹን ገቢ ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ

ይኖርባታል፡፡ የኦርጋኒክና የሌሎች ቡና አመራረትና አዘገጃጀት ዕውቅና ሰርቲፊኬ✍ት የመስጠት ተግባር በአሁኑ ወቅት በውጭ ሀገር ድርጅቶች አማካይነት የሚካሄድ ሲሆን ለዚህም ከፍያ የሚያስፈልገውን ወጪ በተለያዩ አጋሮች እንዲሸፈን እየተደረገ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ እንደ ለ✍ሎች ቡና አምራች የአፍሪካ፣ ደቡባዊ አሜሪካና ደቡብ ምስራቅ ኤሽያ ሃገራት በሀገራችን ዉስጥ ሀገር-በቀል እውቅና ሰጪ አካላት ያለመኖራቸዉ ለዘርፉ እድገት አንዱ ማነቆ ሆኖ ይገኛል፡፡

### 6.2.6 የኤክስፖርት ቡና ዝግጅት፣ ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን በክልሎች ያለመስፋፋት

#### 6.2.6.1 የኤክስፖርት ቡና ዝግጅት በክልሎች ያለመኖር

በዋና ዋና ቡና አምራች ክልሎች የሚዘጋጀው ቡና በአቅራቢያቸው የቡና ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ባለመተከላቸው ወደ ማዕከል በማምጣት ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡ ከዚህ የተነሳ ኤክስፖርት ቡና ዝግጅት ከአቅርቦት ቡና ጋር ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ እንዳይስፋፋ አድርጎታል፡፡ በሙኖኑም ያላለቀለት የቡና ምርት ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ሂደት ከፍተኛ መዋዕለነዋይና ጊዜን ከማባከንም በላይ በክልሎች የቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች እንዳይስፋፉ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም ዘርፉ ከአምራቹ ጋር በማስተሳሰር ረገድ ክፍተት ፈጥሮ የቆየ ጉዳይ ነዉ፡፡

#### 6.2.6.2 የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራና ሰርቲፍኬሽን በክልሎች ያለመቋቋም

የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን ማዕከላት በአዲስአበባና ድሬዳዋ ብቻ መሆናቸው ቡና በከፍተኛ ደረጃ በሚመረትባቸው ዋና ዋና አካባቢዎች የሚቀርበውን ቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማስተናገድና አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ በማይቻልበት ደረጃ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክነያት ተገልጋዩ በአቅራቢያው አገልግሎቱን እንዲያገኝ ካለማስቻሉም በላይ ለዘርፉ መስፋፋትና መጎልበት አይነተኛ ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል፡፡

## 7. የቡና አምራች ሀገሮች ተሞክሮ (Benchmark)

የሀገራችን ቡና ምርትና ምርታማነት ከሌሎች ቡና አምራች ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ሆኖ ለመገኘቱ (ሠንጠረዥ 6) በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ቢቻልም አብዛኛው በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ቡና አምራች ሀገሮች ለየት ባለ መልኩ ኋላቀር የአመራረት ዘዴዎችን በስፋት ስለምንከተል ነዉ፡፡ የቡና ተክል በዕድሜ ያረጀ መሆን፤ የተ☆☆ሉ የቡና ዝርያዎች ዘርና ችግኝ አቅርቦትና ጥራት ማነስ፤ የቡና ተክልና ማሳ እንክብካቤ ተገቢዉን ምክረ-ሀሳብ የተከተለ ያለመሆን፤ ሥነ-ምህዳርንና የአካባቢውን ባህርይ ያገናዘቡ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና ስርፀት በቂ ያለመሆን፤ የቡና በሽታ፤ ተባይና አረም መስፋፋት፤ የአየር ንብረት ለውጥና የተለያዩ የተፈጥሮ መዛባት ችግሮች እና የባለሙያና የሎጂስቲክስ እጥረትና የአቅም ውስንነት በዋናነት ትኩረት ተሰጥቷቸዉ ሊቀረፉ የሚገቡ አበይት ተግዳሮቶች ናቸዉ፡፡

በሃገራችን በቡና ከተሸፈነው የመሬት ስፋት አንጻር እየተገኘ ያለው ዓመታዊ ምርት ከሚጠበቀው በታች በመሆኑ የዋና ዋና ቡና አምራች አገሮችን አማካይ ምርታማነት ስንመለከት፤ ለምሳሌ ቬትናም፣ ብራዚልና ሁንዱራስ እንደቅደም ተከተላቸዉ 23፣ 12 እና 10 ኩ/ል በሄ/ር፤ በላይ ሲሆን የሃገራችን አማካይ ቡና ምርታማነት በሄ/ር ከ7 ኩ/ል የማይበልጥ መሆኑ ያለንበትን ዝቅተኛ ደረጃ ያመለክታል (ሠንጠረዥ 2)፡፡ ይህ ችግር እየከረረ በመጣዉ የዓለም ገበያ ፉክክር ዉስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነን ለመቅረብ ካለማስቻሉ ባሻገር የአምራቹንና የአገሪቱን ተጠቃሚነት ከዘርፉ በቀጣይነት ለማረጋገጥ

በሚደረገዉ ጥረት ላይ አሉታዊ ጫና ያሳድራል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከቡና መሬት ስፋት መጨመር ጋር ተያይዞ የቡና ጠቅላላ ምርት እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በአማካይ በሄክታር የሚመረተዉ ከ7.3 ኩ/ል አልዘለለም፡፡ ይህ የምርታማነት ደረጃ  እንደ ዝርያዉ አይነት፣ የአከባቢዉ ተስማሚነትና የእንክብካቤ ሁኔታ፤ በምርምር ማሳ ከ10–26 ኩ/ል እና በጥቂት ሞዴል አርሶአደሮች እንዲሁም በአንዳንድ ዘመናዊ የግል እርሻዎች እስከ 15 ኩ/ል በሄ/ር ከሚገኘዉ አንጻር ሲታይ ከግማሽ በላይ ዝቅ ያለ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ለተሞክሮ ይረዳ ዘንድ ከማዕከላዊና ደቡባዊ አሜሪካ ሁንዱራስ፣ ጓትማላ፣ ኮስታሪካ እንዲሁም ኮሎምቢያ፣ ብራዚልና ፔሩ በዘላቂ የቡና ልማት የተሻለ ከሚባሉት የሚመደቡ ሲሆኑ ከኤሲያ ቬትናምን ጨምሮ የአምስት ቡና ሞዴል አብቃይ ሀገሮችን አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## 7.1 ብርዚል

ብራዚል ከፍተኛ የቡና መጠን በማምረት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘች ሀገር ስትሆን፤ከቡናው የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ከ12 በመቶ አይበልጥም ፤ሆኖም የቡናን ስራ ለብቻው የሚከታተልና የሚያስፈፅም ራሱን የቻለ የቡና ኢንስቲተዩት አላት፤ኢነስቲቲዩቱ ቡናን የሚመለከት ትምህረት ለተማሪዎች ከመስጠቱም ባሻገር፤ አጫጭር ስልጠናዎችን ለቡና ልማት ሰራተኞች በመስጠት የቡናው ኢንዱስትሪ እንዲያድግ የበኩሉን ድርሻ ይወጣል፡፡ ይህ ተቋም የቡና ምርምርን፤ምርትን፤ግብይትንና ሌሎች ቡናን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ይከታተላል፡ ያስፈፅማልም ፤ሙሉ ሀላፊነት አለው፡፡

ሀገሪቱ በተለያዩ የልማት ዘርፎች ተሞክሯዋ የላቀ ሲሆን በቡና ግን ልዩ የሚያደርጋት በ18ኛዉ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ የጀመረቿዉና በአጭር ጊዜ ዉስጥ በምርትና ኤክስፖርቱ በዓለም ደረጃ የመሪነቱን ሥፍራ ከ170 ዓመታት በላይ በከፍተኛ ልዩነት አስጠብቃ መቆየቷ ነዉ፡፡ በሀገሪቱ የቡና ማህበራዊና ባህላዊ እሴትነቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቶ ከሌሎች አልኮል አልባ መጠጦች ተመራጭ ሲሆን በመቻሉ ከአሜሪካ ቀጥላ ሁለተኛዋ ከፍተኛ የቡና ፍጆታ ያላት ሀገር ለመሆን በቅታለች፡፡

በሀገሪቱ 300 ሺህ ከሚደርሱ የቡና እርሻዎች ዉስጥ ሶስት አራተኛዉን እጅ የሚይዙት ከአሥር ሄክታር በታች ይዞታ ያላቸዉ አነስተኛ አርሶ አደሮች ናቸው፡፡ ይህም  የሀገሪቱን ቡና መሬት 37 በመቶ እና የቡና ምርት ደግሞ  35 በመቶ የሚሸፍን  ሲሆን ከአንድ በመቶ በታች የሆኑት ከ100 ሄክታር በላይ ይዞታ ያላቸዉ አልሚዎች ደግሞ 20 በመቶ መሬትና 25 በመቶ የሚጠጋ የምርት ድርሻ አላቸዉ፡፡

አነስተኛ ቡና አልሚዉ የአክስቴንሽን አገልግሎት የሚያገኘዉ በዋናነት በግብርና ሚኒስቴር ባለሙያዎችና ከቡና አምራቾች ካዎንስልና በህብረት ሥራ ማህበራት ተቀጥረዉ በሚሰሩ ሙያተኞች አማካይነት ነዉ፡፡ በተጨማሪም የግብርና ግብዓትና የእርሻ መሣሪያዎች አቅራቢ ኩባንያዎች በግብዓትና መሣሪያ አጠቃቀም ላይ የሙያ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

በሀገሪቱ የቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በልማቱና ግብይቱ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸዉ፡፡ የእሴት ሰንሰለቱን ተከትሎ ለአባላት ከምርት ግብዓትና ብድር አቅርቦት እስከ ኤክስፖርት ድረስ ባለዉ ሂደት ጠንካራ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡ በዚህም ማንኛዉም አነስተኛ የቡና አምራች የተሻሻሉ የቡና አመራረት፣ አዘገጃጀትና ግብይት ክህሎትና ዕዉቀት ለመጨበጥ የሚችልበትና የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች፣ ቴክኖሎጂዎችንና የብድር አገልግሎት በቀላሉ የሚያገኝበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

ቡናዉ የኢንዱስትሪ ማህበሩ ባስቀመጠዉ መስፈርት መሠረት በሚዘጋጅበት ቦታና የጥራት ማረጋገጫ በሚሰጠዉ መንግሥታዊ አካል በመጠን፣ በክብደት፣ በከለርና በጣዕም ተለይቶ ደረጃዉ በአስተማማኝ ሁኔታ ተረጋግጦ ነዉ ለገበያ የሚቀርበዉ፡፡  አነስተኛ ቡና አምራችም እንደ ምርጫዉ በግሉ ኤክስፖርት ሊያደርግ፣ ለሀገር ዉስጥ ነጋዴዎች ወይም ከ2 - 3% የማይበልጥ ትርፍ እየታሰበላቸዉ እሸቱን ወይም ደረቁን ቡና ተረክበዉ በማዘጋጀት ለሚሸጡ ህብረት ሥራ ማህበራት መሸጥ ስለሚችል የግብይት ሰንሰለቱ አጭርና ቀልጣፋ ነዉ፡፡

በሀገሪቱ ቡና ዘርፍ ላይ በሚሰሩ መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች (ማህበራት) በፈጠሩት ካዎንስል አማካይነት ከቡና አመራረት እስከ መጨረሻ ተጠቃሚ ባለው የምርቱ ግብይት ሂደት ይመራል፣ በስሩ ባደራጀው የጥራት ቁጥጥር ኢንስቲትዩት ደግሞ የቡና ጥራትን ከቡና ማሳ እስከ ኤክስፖርት ባለው ሂደት ይቆጣጠራል፣ በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ ለሚሸጥ የአገሪቱ ቡና ቀጥተኛ ኃላፊነት ስለአለበት የግብይት ሂደቱን ሱፐርቫይዝ ያደርጋል፣ የአገር ውስጥ እና የአለም አቀፍ የቡና ገበያ ሁኔታ መረጃን ያሰባስባል፣ ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል እንዲሁም የህግ፣ የንግድ እና የመሳሰሉትን የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

የቡናዉ ዘርፍ ከመኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪስ እየገጠመዉ ያለዉን ብርቱ ዉድድር ለመቋቋም የቡና ልማትና ምርት ዝግጅትን ሜካናይዝ በማድረግ ላይ ስትሆን በዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ጃፓን፣ ፈረንሳይና ቤልጅየም በቅደም ተከተል 21.2፣ 26.5፣ 30.9፣ 19፣ 16.1፣7.2 በመቶ የገበያ ድርሻ ይዛ ትገኛለች፡፡

ለብራዚል የቡና ኢንዱስትሪ ከፍተኛ ደረጃ መድረስ አስዋጽኦ አድረገዋል ከሚባሉት መካከል ወሳኞቹ፡-

- የግሉ ሴክተር ከመንግሥት ሙሉ ዕዉቅና ተሰጥቶት የቡና ምርምር፣ ልማት እንዲሁም ጥራትና ግብይት ቁጥጥር በኃላፊነት ስለሚያካሄድ፣
- የገጠር ብድር ሥርዓት ቡና አምራቾችን ከልማቱ ጀምሮ እስከ ግብይቱ ድረስ በፋይናንስ እጥረት ኪሳራ እንዳይደርስባቸዉ ድጋፍ ከማድረጉ ጎን ለጎን በFuncafe’ (Coffee economy defence fund) በኩል ለቡና ዘርፍ የተለየና ቀጣይ የፋይናንስ ድጋፍ መስጠት፣
- ሁሉንም አምራች፣ አዘጋጅና፣ ነጋዴ እኩል የሚያስተናግድ አጭርና ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓት መኖሩ፣
- በዓለም ገበያ ዝናንና የበላይነትን ይዞ መቆየት ያስቻለ የመንሥት፣ አምራቹና የንግዱ ህብረተሰብ ቅንጅታዊ አሰራር መተግበሩ፣
- የቡና ልማትን ወደ አመቺ ሥነ ምህዳር በማስፋፋት በመስኖ በመታገዝ ምርታማነቱን በአንዳንድ እርሻዎች እስከ 50 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ የሚያስችል ሳይንሳዊ የአመራረት አቅም መፈጠሩ፣
- ቡናን በጥሬ ከመሸጥ ባሻገር አምራቹ በተለያየ ደረጃ ወደ ያለቀለት ምርት በሂደት ለመተካት ሥራ መጀመሩ ናቸው፡፡

## 7.2 ቬትናም

ከ20 ዓመት ባነሰ ጊዜ ዉስጥ በተደረገዉ ከፍተኛ ርብርብ ምርት የሚሰጥ ቡና መሬትን ከ135 ሺህ ወደ 550 ሺህ ሄ/ር፣ አማካይ ምርታማነቷን ከ10 ኩ/ል ወደ 23 ኩ/ል በሄ/ር በላይ እንዲሁም ኤክስፖርቷን ከ68.7 ሺህ ቶን ወደ 1.2 ሚሊዮን ቶን ለማሳደግ ችላለች፡፡ ይህን እመርታዊ ዕድገት ለማስመዝገብ ያስቻላት ከጠቅላለዉ ቡናዋ 85% ከ 5 - 20 ዓመት ዕድሜ ክልል ዉስጥ በመያዝ መቻሏና ምርታማ ዲቃላ ዝርያዎችና በአፈር ምርመራ ዉጤት ላይ የተመሰረተ ማዳበሪያና የመስኖ ዉሃን በከፍተኛ መጠን በመጠቀም እያንዳንዱ የቡና እግር በሙሉ አቅሙ ምርት እንዲሰጥ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ነዉ፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ልማቱን በጣም ተሰማሚ በሆኑ ሥነ ምህዳራትና ምርታማ ዝርያዎች ለመገደብ በጀመረችዉ እንቅስቃሴ ለልማቱ ተስማሚነታቸዉ በተሟጠጡ መሬቶች ቡናን በሌሎች ሰብሎች እንዲሁም ነባር ዝርያዎችን በተሻሻሉ ዝርያዎች ከመተካት በተጨማሪ ኤክስፖርቱንም በጥሬዉ ከመላክ ይልቅ እሴት ጨምራበት ዉጭ ወደ መላክ በማሸጋገር አምራቹ የተሻለ ዋጋ አግኝቶ እንዲበረታታ ጠንክራ እየሰራች ትገኛለች፡፡

በዚህም ጥረቷ ከሚፎካከሯት ህንድና ኢንዶኔዥያና ብራዚል የማምረቻ ወጪዋን ዝቅ ያለ በማድረግ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪነቷን አስፍታ 100 በሚደርሱ ሀገሮች ቡናዋን ትሸጣለች፡፡ ጣሊያን፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ቤልጅየም፣ዩ.አስ.ኤና

ጃፓን በመሳሳሉ ትላልቅ ቡና ገዢ ሀገራት ከ8-15% የገበያ ድርሻ ያላት ሲሆን ባላት ከፍተኛ የምርታማነት ደረጃና አነስተኛ የማምረቻ ወጪ የገበያ ድርሻዋን የማስፋት ዕድል አሁንም እንደሚኖራት ይገመታል፡፡

ለዚህ ስኬታማ የቡና ዘርፍ ዕድገት ቬትናምን ካበቋት ዋናዋናዎቹ፡-

- ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኖ በተቋቋመዉ የግብርና ልማት ባንክን ጨምሮ ሌሎች የገጠር ፋይናንስ ተቋማት የቡናን ቋሚ ሰብልነት ባገናዘበ ሁኔታ ከፍ ያለ የኢንቨስትመንት ካፒታል ፍላጎትን በአነስተኛ ወለድ ለአርሶ አደሮች እንዲያሟሉ በመንግሥት መደንገጉ፣
- የቡና ሰብል አያያዝ ዘዴ በምክረ ሀሳብ በተገቢው መንገድ በመተግበር አነስተኛ አርሶ አደሮች በትንሽ መሬት ላይ የሚያለሙትን ቡና ተክል ከተሟላ እንክብካቤ ጋር በምርታማ ዕድሜ ዉስጥ በመያዝ ከፍተኛ ምርት በማምረት የማምረቻ ወጪዎችን ዝቅ ማድረግ መቻላቸዉ፣
- የምርት ዕድገቱን የሚያበረታታ የሀገር ዉስጥ ግብይትና ኤክስፖርት ማስፋፊያ ሥርዓት በመዘርጋት መዳረሻ ገበያዎችን ዋነኛ ቡና ሸማች እና አጎራባች አገሮች ላይ በማስፋፋት ለቡና አምራቹ የሚደርሰዉ ዋጋ ከኤክስፖርት ዋጋዉ 90% በላይ በማድረስ የቡና አቅርቦትን ማሳደግ
- የአመራረትና ግብይት አሠራሩን ከተፎካካሪዎች ጋር በቀጣይ በማነፃጸር በየጊዜዉ የማስተካከያ እርምጃ በመዉሰድ ተወዳደሪዎችን መቅደም፡፡
- እንዲሁም
  - ✓ የቡናውን ዘርፍ ለማሳደግ የሚያስችል ጠንካራ አወቃቀር በማዘጋጀት፤
  - ✓ ለአረቢካ ቡና እና ለሮቡስታ ቡና ተስማሚየሆኑ ስነ-ምህዳራትን ለይቶ በማውጣት ወደተግበራ በመግባት ፤
  - ✓ የተሻሻሉ የቡና እንክብካቤና ድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን በአርሶ አደሩ እንዲተገበሩ በማድረግና ተከታታይ ስልጠና በመስጠት፤
  - ✓ የቡናን ልማትና የጥራት ደረጃውን እንዲሻሻል በማድረግና ዕሴት የመጨመር ስራን በመስራት፤

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሰትራተጂዎችን በስራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ የቡናው ዘርፍ እንዲያድግ ለማድረግ ችለዋል፡፡

## 7.3 ኮሎምቢያ

የኮሎምቢያን የቡና ኢንዱስትሪ በበላይነት የሚያንቀሳቅሰው የቡና አምራቾች ፌዴሬሽን /Association of Coffee Growers of Colombia, FNC/ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ1927 ጀምሮ የተጣለበትን ኢንዱስትሪውን በበላይነት የመምራት ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት ሃገሪቷን በቡና ጥራት ቀዳሚ፣ በምርትና ኤክፖርት ደግሞ ከአራቱ ቀዳሚዎቹ አንዷ እንድትሆን አስችሏታል፡፡

ፌዴሬሽኑ ከቡና ኤክስፖርት ከሚገኘዉ አነስተኛ ቀረጥ የድጎማ አሰራርን በማመቻቸት ገበያውን የማረጋጋት ሥራ በተጨማሪ በየደረጃው ለሚገኙ ባለሙያዎች የተሻሻሉ ቡና አመራረትና ተባይ ቁጥጥር ስልጠናዎችን በተከታታይ የመስጠት፣ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድና መደገፍ፣ የግብዓትና ሥራ ማስኬጃ ብድር አቅርቦትን ማመቻቸት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኮሎምቢያን ቡና የማስተዋወቅ፣ የቡና ጥራትን የመቆጣጠርና ስፔሻልቲ ቡናን በማስፋፋት የኮሎምቢያ ቡና አመራረትና ግብይት ሥርዓትን በበላይነት የመምራት ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ማህበሩ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን በማሻሻልና ግብይትን በማሳለጥ ለአምራቹና ለሃገሪቱ ትርፍ ከማስገኘት ባለፈ “በዛሬ የቡና ኤክስፖርት ገቢያችን የነገዋን ኮሎምቢያ እንገንባት” በሚል ሀገራዊ መርህ በመንቀሳቀስ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲመዘገብ

ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግ መቻሉ ልዩ ያደርገዋል፡፡ በምርምርና ሥልጠና፣ በህብተሰብና ሰብዓዊ ልማት እንዲሁም አካባቢ ጥበቃ ሥራዎቹ ዘላቂነት ያለዉ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማት በተዋኒያኑ ዘንድ እንዲሰፍን ረድቷል፡፡

የነገዉን ቡና አምራች ትዉልድ ለመፍጠር ትምህርትና ቡና በሚል ፕሮግራሙ በቡና አምራች አካባቢዎች የፋይናንስ ድጋፍ በመስጠት በአንደኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ካሪኩለም ዉስጥ ቡና ነክ ርዕሶች ተካተዉ ትምህርት እንዲሰጥ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ከቡና የሚገኘዉን ትርፋማነት ማሳደግ ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የቡና አመራረት እና ቢዝነስ አስተዳደር ሥልጠናዎች ላይ ኢንቨስት ያደርጋል፡፡

የአነስተኛ ቡና አምራቹን ቤተሰብ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ችግርን ለመቅረፍም ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር ከ2004 ዓ/ም ጀምሮ የጤና መደህን ዋስትና ተግባራዊ በማድረግ በርካታ ቤተሰቦችን ተጠቃሚ ያደረገበት ሁኔታ እንዲሁም በገጠር መንገድና መኖሪያ ቤቶች ግንባታ እንደዚሁም ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ከፍተኛ ተሳትፎዉ የአደረጃጀቱን ትክክለኛ የህብረተሰብ አገልጋይነት በእዉን ያረጋገጠ ነዉ፡፡

ፌዴሬሽኑ የፖሊሲ ሃሳቦችን በማመንጨትና ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ፤ በምርምር የሚገኙ ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዉ በማቅረብ፣ ቡና በመግዛት፣ በማዘጋጀት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ አገር በማቅረብ፣ የአገሪቷን የቡና ምርት የጥራት ደረጃ በማስጠበቅና በዓለም ገበያ እንዲቀርብ በማድረግ  የቡና ገበያን ለማሳለጥ የሚጠቀምባቸውን ልዩ ልዩ ድርጅቶችን በስሩ ያስተዳድራል፡፡

መንግስትም በግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር አማካኝነት በቡና ዘርፍ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን በአገር ደረጃ በፌዴሬሽኑ የሚወጣውን የቡና ዋጋ ማስጸደቅ፣ ኤክስፖርት የሚደረግ የቡና ምርት ጥራት ህግ በማውጣትና ተግባራዊነቱን የመከታተል፡ የኢንዱስትሪውን ባለደርሻ አካላትን የማስተባበር፣ የመምራትና የመቆጣጠር፡ ጥናትና ምርምር የማበረታታት፡ የቡና ዋጋን በፌዴሬሽኑ አማካኝነት የማረጋጋት፡ አዳዲስ ገበያዎችን ለማግኘት እና ነባር ገበያዎችን ለማጠናከር ከሌሎች አገሮች መንግስታት ጋር በመደራደርና ስምምነቶችን የመፈጸም ኃላፊነት እየተወጣ ይገኛል፡፡

በዚህ ቅንጅታዊ አሰራሯ ዛሬ ዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ጃፓን፣ ፈረንሳይና ቤልጂየም በመሳሰሉ ዋና ቡና ሸማቾች ከ 6 -16 በመቶ የገበያ ድርሻ ልትይዝ ችላለች፡፡

## 7.4 ጓቲማላ

ከዘላቂ የቡና ልማት አኳያ የተሻለ እየሰራች ሲሆን በተፈጥሮ ማዳበሪያ ሊሸፈን የማይችለውን ማሳ በመለየት አናካፌ በመባል በሚታወቀዉ የቡና አምራቾችና ሻጮች ማህበር ላቦራቶሪዎች በየሁለት ዓመቱ በሚካሄድ የአፈር ምርመራ ዉጤት ላይ በመመርኮዝ የሚያዋጣውን ኬሚካል ማዳበሪያ ምክረ-ሀሳብ በመጠቀም አፈሩን ንጥረ ነገር ጉድለት ማሟላት ላይ ያነጣጠረ ነዉ፡፡ የሃገሪቱ ህግ የቡና ተረፈ ምርቱ በኮምፖስት መልክ በማዘጋጀት ለማዳበሪያነት ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ስለሚያስገድድ ማንኛዉም ቡና አዘጋጅ የአካባቢ ብክለትን የመከላከል ሃላፊነቱን ባግባቡ እንዲወጣ ክትትልና ድጋፍ ስለሚደረግ አካባቢንና የህብረሰቡን ጤና ለጉዳት የማያገልጥ የቡና አመራረትና አዘገጃጀት ዘዴያቸዉ የሚደነቅ ነዉ፡፡

የነዚህን ሀገሮችና የሌሎችንም መልካም ተሞክሮ ወስደን ከላይ የተጠቀሱትን የምርት፤ ምርታማነትና ጥራት ማነቆዎች በሚገባ ለመቅረፍና ሀገሪቱ በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ ዓመት ላይ ለማሳካት ያስቀመጠችውን ምርታማነትን ከ 7.3 ወደ 10.2 ኩ/ል በሄ/ር የማሳደግና ከ600,0000 ቶን በላይ ቡና ኤክስፖርት የማድረግ ግብ እዉን ለማድረግ በምርምሩ፤ በልማቱና ግብይቱ ብዙ መስራት የሚጠበቅ ሲሆን በተለይ እምርታዊ ለዉጥ ለማምጣት የተሻለ እምቅ አቅም (ፖቴንሻል) ባለቸዉ አከባቢዎች የተለየ ርብርብ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን

እንዲሁም ጥራትን ከእጥፍ በላይ ማሻሻል የሚቻልበት አቅጣጫ ተቀምጦ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ያለዉን እንቅስቃሴ የበለጠ በማጠናከር መሥራት ከመንግሥትና ሁሉም የዘርፉ ተወኒያን ብዙ ይጠበቃል፡፡

በዓለም ገበያ ላይ እየከረረ የመጣዉ ፉክክር ኋለቀርና ልማዳዊ በሆነ የአመራረት ዘይበ✍ና አሰራር ቡናን ማምረትና ማዘጋጀት የምንቀጥል ከሆነ ሀገራችን በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከዉድድር ዉጭ ሆና መተዳደሪያዉ ቡና ልማትና ግብይት ላይ የተመሰረተዉ የህብረተሰባችን ክፍልና በኤክስፖርቱ ከፍተኛዉን የዉጭ ምንዛሪ ከዘርፉ እያገኘ ያለዉ ኤኮኖሚያችን ትልቅ አደጋ በመሆኑ ያለንን እምቅ አቅም ተጠቅመን ባጭር ጊዜ ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ እንዲሁም ጥራትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለቡና አምራቾች በተለይም ከፍተኛዉን ድርሻ ለሚይዙ አርሶ አደሮች በማድረስ የላቀ ዕድገት ለማምጣት የምንችልበትን መንገድ በመቀየስ ለመተግበር ከዚህ በላይ መዘግየት የለብንም፡፡

በመሆኑም በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለዘርፉ ከተቀመጠዉ ግብ ባሻገር ሀገሪቱ በቀጣይ ስድስት እስከ ሰባት ዓመታት ዉስጥ በዓለም ቡና አምራችነትና አቅራቢነት ከፍተኛዉ ደረጃ ላይ ደርሳ ለማየትና ይህንን ራዕይ ዕዉን ለማድረግ በአገሪቱ የቡና ምርምር፣ አ✍ክስቴንሿን እና ጥራት/ግብይት ሂደት ያሉትን ወሳኝ ጉድለቶችን በመለየት፣ የቡናን ምርት፣ ምርታማነትና ጥራትን በላቀ ደረጃ በቀጣይነት የሚያሻሿሉ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ ሀገራዊ ግዴታችን ነዉ ብለን መረባረብ ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ እንደ አረቢካ ቡና መገኛ ሀገር የሰፊ ብዘሀ ሕይወትና የልዩ ጣዕም ቡና ባለቤት እንደመሆኗ ከቡና ዘርፍ ማግኘት የሚገባት ጥቅም በሚፈለገው መጠንና ዓይነት እያገኘች አይደለም፡፡ ለዚህም ዋንኛ መንስኤ ቡናን ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ተጠቃሚው ድረስ ባሉ ሰንሰለቶች መከናወን የሚገባቸው ተግባሮች ተገቢው ትኩረት አግኝተውና ባለመስራታቸው ቡና ለገበያ በሚፈለገው መጠንና ጥራት ማቅረብ ባለመቻላችን ነው፡፡ ደህንነቱ የተጠበቀና ጥራት ያለው ምርት በአሁኑ ሰዓት በአለም ገበያ ተቀዳሚ ፍላጐትና ምርጫ እየሆነ በመምጣቱና ወሳኝ የቡና አምራች ሀገራት የሸማቾችን ፍላጎት ለማርካት በሰፊው ትኩረት ሰጥተው ከመቅረብና ጋር ተያይዞ ከፍተኛ በሆነ የገበያ ፉክክር የዋጋ መዉረድና መዋዥቅ እንዲሁም ተጠቃሚዎች የምግብ ደህንነታቸውንና ጥራት ሊያረጋግጥላቸው የሚችል የሰው ኃይልና የቴክኖሎጂ አቅም በመዳበርና ከፍተኛ ጥራት ያለው ልዩ ቡና ለሚያቀርቡ ከፍተኛ ዋጋ የሚከፍሉ መሆኑ ሀገራችን በዘርፉ ብቁና ተወዳዳሪ ሆና ለመቀጠል አይነተኛ ተግዳሮት ሆኖ ይታያል፡፡

በሠንጠረዥ 3 እንደተመለከተው በ2005 ለማዕከላዊ ገበያ ከቀረበው 208,278.12 ቶን የኤክስፖርት ቡና 7855.89 ቶን ወይም 3.77% ብቻ የልዩ ቡና (Specialty) ደረጃ ሲሆን ከታጠበ ቡና በ10.9% የተሻለ ሊባል ቢችልም ባልታጠበ ቡና 1.03% ብቻ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው (96.33%) በመካከለኛ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቡና ነው፡፡ ለዚህም ችግር ዋነኛ መንስኤዎቹ ቡናን ከማሳ ጀምሮ እስከ ገበያው ባለው ሂደት ውስጥ የሚከሰት ሲሆን በዋናነትም ከቡና አለቃቀም አዘገጃጀት ድህረ ምርት አያያዝና የገበያ አቅርቦት ጋር የሚፈጠሩት ችግሮች ዋነኞቹና ሰፊውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ ስለዚህ ሀገራችን በዓለም የቡና ገበያ ብቁና ተወዳዳሪ በመሆን ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝም የአ/አደሩንና የአምራቹን ገቢ ከፍ ለማድረግ የዝቅተኛ የቡና ጥራት አቅርቦትን ማሻሻልና የልዩ ቡና (Specialty coffee) ድርሻን በእጅጉ ማሻሻል በምርት ዝግጅት ጥራትና ገበያ ማስፋፋትና ድጋፍ በበቂ ሁኔታ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መስራትና ቡና ለአ/አደሩም ሆነ ለሀገሪቷ ሊያበረክት ከሚገባው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም አንፃር የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

## 8. ስትራቴጂያዊ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት

አገሪቱ በጀመረችው ፈጣንና ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ጉዞ የቡና ልማት ዘርፍ ራእይ፣ ተልእኮ፣ አላማና ግብ ከተገመገመ በኋላ ከቡና ኢንዱስትሪዉ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ትስስር በጥንቃቄ በመመርመርና በመተንተን፣ ችግሮቻቸውንና የቴክኖሎጂ ፍላጐታቸውን በማጤንና የቡና ልማት፣ ምርት፣ምርታማነትና ጥራት ለማሳደግ/ለማሻሻል ወሳኝ ናቸው የሚባሉ ዋና ዋና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ተቀር▭ዋል፡፡ በዚህ መሰረት በረካታ ዋና ዋና ጉዳዮች ከተለዮ በኋላ የአንዳንዶቹ መሰረተ ሃሳብና ይዘት ስለሚዋዋጥ በተጠቃለሉ ወሳ✂ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ስር እንዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት የቡናን ምርትና ምርታማነት በእጥፍ ሊያሳድጉና ጥራቱንም ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለዉ የታመነባቸዉ ዋና ዋና ወሣኝ ጉዳዮችና አማራጭ ስትራቴጂዎቻቸዉ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

## 8.1 ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል

### 8.1.1 ጠንካራ የኤክስቴንሽን ድጋፍና የመረጃ ሥርዓት መፍጠር

- በአብዛኛዉ የሀገሪቱ የቡና ማሳ የተስፋፋዉን ኋላቀርና ባህላዊ የአመራረት ዘይቤዎች

ማሻሻልና በዘመናዊዉ መቀየር፤

- እንደ አጭር ጊዜ መፍትሔ የነባር ቡና ይዞታዎችን በዕድሜ✍ በመለየት እንደአካባቢዉ ሁኔ✍ታ የተለያዩ የምርታማነት ማ☆☆ያ ምክረ-ሀሣቦችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን በፓኬ✍ጅ መቀመር፣ ማዘጋጀት፣ ማሰራጨትና በየደረጃዉ የተግባር ሥልጠና መስጠትና ተፈጻሚነቱን መከታተልና መደገፍ

የጥላ መጠኑን ማስተካከል፤ በቡና ዛፎች መካከል ያለዉ ቦታ/ርቀት ከሚመከረዉ በላይ ስፋት ካለዉ ተመሳሳይ ከሆኑ ዝርያዎች ችግኝ አዘጋጅቶ ባዶ ቦታዎች ላይ በተገቢዉ የተከላ ርቀት መትከልና ማሳዉን መሙላት፤ አረምን በወቅቱና በሚፈለገዉ መንገድ መቆጣጠር፤ ተዳፋት በሆኑ ማሳዎች/መሬቶች ላይ የተለያዩ የአፈርና ወሀ እቀባ ዘደ✍ዎችን መጠቀም፤ የአፈር ለምነቱ ዝቅተኛ በሆነበት መሬት ላይ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን በማዘጋጀትና እንዳስፈላጊነቱ ኬሚካል ማዳበሪዎችን በመጠቀም የአፈሩን ለምነትና ወሀ የመያዝ ችሎታ ማ☆☆ል እንዲሁም ደጋፊ መስኖ አማራጮችን መጠቀም፡፡

- በእንክብካበ✍ ማነስ ምክንያት ምርታማ ያልሆኑትን በወጣትነትና መካከለኛ ዕድሜ✍ ያሉ ቡናዎችን በተመለከተ በተሟላ ፓኬጅ መሠረት ለማልማት የሚያስችሉ የኬሚካል ማዳበሪያን በኦርጋኒክ ቡና ሰርትፊኬት ባልታቀፉ አከባቢዎች በሰርቶ ማሳያ ደረጃ በግምባር ቀደም አርሶ አደሮች ማሳ በማካሄድ አዋጭነቱን በማስተዋወቅ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ፡፡
- በኦጋኒክ ሰርቲፊኬት በተሰጣቸዉ ማሳዎች ላይ የአፈር ለምነቱን መጠበቅ አሰፋላጊና ለምርታማነት ዕድገትና አከባቢ ጥበቃ ወሳኝ በመሆኑ በቂ የተፈጥሮ ማዳበሪያ፣ የአፈርና ዉሃ ጥበቃ፣ በሽታ፣ ተባዮችና አረም ቁጥጥር ባግባቡ ማከናወን
- በረጅም ጊዜ ለአካባቢዉ ተስማሚና ምርታማ በሆኑ ሌሎች የተ☆☆ሉ ዝርያዎች በመተካት አስፈላጊዉን እንክብካቤ ማድረግና ከነባር የአካባቢ ቡና ዝርያዎች መካከል የተሻሻሉና የአከባቢዉ ልዩ ጣዕምና ባህርይ ያላቸዉን በምርምር በቀጣይ ማፍለቅ፤ በእነዚህ ማሳዎች የሚገኙ ቡናዎች (የጫካ፤ የከፊል ጫካና የ⮙ሮ ቡና ይዞታዎች)

ባብዛኛዉ የአካባቢ ዝርያዎችበመሆናቸዉ፤ በተ☆☆ሉና ጠባብ የዘረ-መል መሰረት ባላቸዉ ጥቂት ዝርያዎች መተካት ሰፊ የቡና ዘረ-መልና (ብዝሀ-ሕይወት) ሀብታችንን አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ በመጀመሪያ እያንዳንዱን ዝርያ እንደ ልዩነቱ ሰብስቦ ለወደፊት ጥቅም በአንድ ማዕከል እንዲጠበቅ ማድረግ፡፡

## 8.1.2. የቡናን ምርትና ምርታማነት ለመጨመር የቡና እደሳ ስራዎችን በስፋት ማከናወን

አብዛኛው ቡና በእርጅና ምክንያት ከመዳከሙ የተነሳ በቡና ምርትና ምርታማነት ላይ ያለዉ አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በምርምርና አርሶ አደር ማሳዎች የተደረጉ ሙከራዎች እንደሚያሳዩት በአገራችንና በሌሎች በቡና ልማት በሚታወቁ አገሮች ያረጀ ቡናን በማደስ ምርታማነትን ማሻሻል እንደሚቻል ይታወቃል፡፡ በዕድሜ✍ መግፋት ምክንያት ምርታማ ያልሆኑትን (ያረጁ) ማሳዎች (ከ25 ዓመት በላይ ዕድሜ✍ ያለዉን የቡና ማሣ) በተለያዩ የእደሳ ዘደ✍ዎች ተጠቅሞ ደረጃ በደረጃ የምርት ዙሩን መቀየር፤ ከነዚህ ያረጀ ቡና እደሳ ዘደ✍ዎች ዉስጥ ሙሉ ጉንደላ ማካሃ✍ድ ማሳዉ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት ያለ ምርት እንዲቆይ ማድረግ ስለሆነ፤ የተጎነደሉ ዛፎች ምርት መስጠት እስከሚጀምሩ ድረስ አርሶ አደሩ ካልተጎነደሉ ዛፎች በመጠኑም ቢሆን ምርት እያገኘ እንዲቆይ ከፊል ጉንደላና ማሳዉን በዓመታት ከፋፍሎ በመጎንደል/በማደስ የምርት ዙሩን መቀየር የበለጠ ይመረጣል፡፡ ጉንደላ አዋጭ ቴክኖሎጂ የሚሆነዉ እንደየቡናው ዝርያ ዓይነት፣ ጤናማነት፣ በምንጠቀመዉ የመጎንደያ መጋዝ ንጽህና በአስተማማኝነት፣ ከጉንደላ በኋላ የሚወጡትን ቅጥያዎች ለማስተካከል የምናደርገዉ ክትትል፣ አረምና ተባይ ቁጥጥር፣ እንዲሁም ጉዝጓዝና ማዳበሪያ በአግባቡ ተሟልተዉለት ወደምረታማነት እንዲመለሱ ማድረግ ሲቻል ነዉ፡፡

**ጉንደላን መጠቀም ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-**

- ከዘርና ችግኝ ዝግጅት፣ ጉቶ ነቀላና ተያያዥ ስራዎች ጋር ተያይዞ ወጪው አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ቡናው ለምርት የሚደርስበትን ጊዜ ቢያንስ በአንድ ዓመት የሚሳያጥር መሆኑ፤
- የተሻሻሉ ዝርያዎች የዘርና ችግኝ አቅርቦት በቂ ባልሆነባቸው አካባቢዎችና መተኪያ የሌላቸው የአከባቢ ዝርያዎች በተሻለ ደረጃ ተጠብቀዉ የአካባቢውን ጣዕምና ባህርይ ሳይፋለስ በዘላቂነት ለማቆየት፣
- የሚጎነደለዉን ቡና ማሳ በሦስት ወይም አራት ቦታ በመክፈል ሩቡን ወይም ቢበዛ ሲሶዉን ብቻ በየዓመቱ በመጎንደል ዓመታዊ ደባል ሰብሎችን በማልማት ገቢ እንዳይቀንስ ማድረግ መቻሉ እና
- ለዘረ-መል (ጀርም ፕላዝም) ጥበቃ እንደሚረዳ ተመራጭ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

**ለዚሁም፤**

- በሠርቶ ማሳያዎች፣ በምርምር ሙከራ ጣቢያዎችና በአርሶአደር ማሳ የልምድ ልዉዉጥና በተግባር የተደገፈ ሥልጠና በስፋት ይካሄዳል፡፡
- በዉጤታማነታቸዉ የሚታወቁ የተለያዩ የጉንደላ ዓይነቶች ቢኖሩም ከአገራችን ተጨባጭ ሆኔታ በመነሳት ሙሉ/ከፊል የጉንደላ ስልት ተጠቅሞ ቡናውን ማደስ የተሻሉ ጥቅሞችን ስለሚያስገኝ ተመራጭነቱ ላይ ግንዛቤና እምነት እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

- ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖ ከዕድሜ ብዛት፣ በበሽታና ተባይ ጥቃት እና አያያዝ ችግር የተጎዱ ቡና ዛፎች ተጎንድለዉ ወደ ምርታማነት መመለስ ስለማይችሉ እነዚህን ነቅሎ ዘረ-መላቸው እንዳይጠፋ በተመሳሳይ ዝርያ ችግኝ መተካት ስላለበት በቂ የዘርና የችግኝ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ ላይ ልዩ ትኩረት የሚሰጠዉ ይሆናል፡፡

- በቡና ግንድ አድርቅና ሌሎች በሽታዎች የተጠቁትን ነቅሎ በቦታዉ መትከል ላይ በሽታዉ እንዳይተላለፍ ስለሚደረግ ጥንቃቄና አርሶ አደሩ በፈቃደኛነት እንዲቀበለዉ እምነት የተፈጠረለት ስለመሆኑ ማረጋገጥ ልዩ ትኩረት የሚሰጠዉ ይሆናል፡፡

### 8.1.3 በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚ አካላትና ባለሙያዎች ለቡናው ዘርፍ የተለየ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ማድረግ

በየእርከኑ ኃላፊነት የተጣለባቸዉ ተቋማት አመራሮችና ሙያተኞች የአርሶ አደሩን/ሯን በልማቱ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን እንዲጎለብት የሚያስችል ቀልጣፋና ዉጤታማ የቡና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት የተሟላ የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት አቅርቦት ለሚሟላት ቁርጠኛ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ጎታች አመለካከትን በማስወገድ በአርሶአደሩ ዉጤታማነታቸዉ ተፈትሸዉ የተረጋገጡ አሰራሮችን በማስፋት ረገድ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል ይጠይቃል፡፡ በዋና ዋና ቡና አምራች ክልሎች በሥራ ሂደት ደረጃ ዘርፉ መዋቀሩ ብቻዉን በቂ አለመሆኑ እምነት ተይዞ በአስፈላጊ የሰዉ ሃይልና በጀት አቅም በፈቀደ መጠን መደገፍ፣ ከሰብሉ ከፍተኛ የኤኮኖሚ ጠቃሜታ፣ ሃገራዊ ፋይዳና ጠንካራ የገበያ ዉድድር የሚመጥን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ ከሞላጎደል በሁሉም ዘንድ የሚታዩትን ክፍተቶችን በመቅረፍ በጥቂት አርሶአደሮች ላይ ብቻ የተወሰኑትን ዉጤታማ ተሞክሮዎችን በቀጣይነት በማስፋት ለቡና ልማት ካለን ምቹ ሁኔታ ጋር የሚመጣጠን የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ለብዙሃኑ የቡና አምራች ቀበሌዎች አርሶአደሮች ቡና የኑሯቸዉ መሠረት ከመሆኑ አንፃር በየደረጃዉ ያለዉ አመራር የህዝቡን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በቀጣይነት ማረጋገጥ ኃለፊነቱና ግዴታዉ አድርጎ መዉሰድና ባግባቡ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ በነዚህ አከባቢዎች ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ፣ ለመኸር እና ለበልግና መስኖ ሥራዎቻችን የምንሠጠዉን ትኩረት ለዓመታት በቋሚነት ማሳ ላይ ለሚከርመዉ ቡናችን መስጠት የሚያስችል ህዝባዊ ንቅናቄ መፍጠር የሚበዛበት አይሆንም፡፡ ይህ ግንዛቤ ግን ከከፍተኛዉ እስከ ዝቅተኛዉ አመራር የተያዘ ባለመሆኑ የቡና ልማትና ጥራት ሥራ እንደ ደባል አጀንዳ የሚታይበት ሁኔታ በሰፊዉ ይስተዋላል፡፡ ይህ አመለካከት በቡና ዘርፍ የተሰማሩትን አርሶአደሮች፣ ልማታዊ ባለሀብቶችና የንግዱን ህብረተሰብ ኑሮ ከማናጋት ባለፈ ለሀገር ዕድገት ጠንቅ መሆኑ ታዉቆ በፍጥነት መቀረፍ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ይህ ስትራቴጂ ሀገራዊ ይዘት ቢኖረዉም እያንዳንዱ ቡና አምራች ክልል፣ ዞን፣ወረዳና ቀበሌ በሱ መነሻነት የራሱን ስትራቴጂ አዘጋጅቶ አፈጻጸሙን መደገፍ፣ መከታተልና መገምገም ይኖርበታል፡፡

### 8.1.4 ለየስነ-ምህዳሩ ተስማሚ የሆኑ የቡና አመራረት ቴክኖጂዎችን በቀጣይነትና ማፍለቅና ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ

- **የአጭር ጊዜ መፍትሔ**

  - ያለዉን የምርምር አቅም በመጠቀም የገበያዉን ፍላጎትና የተለያዩ ሥነ-ምሕዳራትን መሰረት ያደረጉ ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ፤ እስካሁን ለይ ርጋጨፌ፤ ሲዳማ፤ ሀረር ወለጋና ሊሙ አካባቢ የወጡ ልዩ የቡና ዝርያዎችን እንዲስፋፉ ማድረግ፤

- በሥልጠና፣ በልምድ ልውውጥና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) በመታገዝ ተመራማሪዎች በየሙያ ዘርፋቸው የተሻሻሉ የቡና አመራረትና አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎችን ከሌሎች ቡና አብቃይ ሀገራት በማስገባት ለሀገራችን ተስማሚ ሊሆኑ የሚችሉትን መርጦ የማላመድ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

➢ **የረጅም ጊዜ መፍትሔ**

- የምርምሩን ሁለንተናዊ አቅም (በአደረጃጀት፤ በሰዉ ሀይል፤ በበጀት/ፋይናንስ፤ በላቦራቶርና በመስክ መሣሪያዎችና ፋሲሊቲዎች፤ ወዘተ.) በመገንባትና በማጠናከር ለተለያዩ ቡና አብቃይ ሥነ-ምህዳራት ተስማሚና ለቡና ልማትና ጥራት መሻሻል መፍትሔ የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያፈልቁ/እንዲላመዱ ማድረግና ማስፋት፡፡

- እስካሁን ባልተዳሰሱና በተለያዩ ሌሎች ቡና አብቃይ ሥነ-ምህዳራት ወካይ የቡና ምርምር ማዕከላትን/የሙከራ ጣቢያዎችን በማቋቋምና በማደራጀት ቴክኖሎጂዎች እንዲፈልቁና እንዲላመዱ በማድረግ ጥቅም ላይ ማዋል፡፡

## 8.1.5 ለቡና ተስማሚ ሆኖ ያለማ መሬት በመለየት ዘመናዊ የቡና ልማትና ምርት ዝግጅት ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት

- አግባብነት ያላቸዉን ሙያተኞች በማሰማራት ለልማት ጣቢያ ሰራተኞች፣ ለወረዳና ዞን ቡና አ✍ክስፐርቶች አስፈላጊዉን ስልጠና በመስጠት፤ ያለዉን የሰዉ ኃይልና መሣሪያ በመጠቀም በአገሪቱ ልዩ ልዩ ቡና አምራች አከባቢዎች የዳሰሳ ጥናት ማካሃ✍ድ፤ ዝርዝር መረጃ መሰብሰብና ብሐ✍ራዊ የቡና ካርታ ማዘጋጀትና መረጃ ቋት ማደራጀት፡፡

- ለቡና ተስማሚ የሆኑ ነገር ግን በለ✍ሎች ዝቅተኛ ኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባላቸዉ ሰብሎች የተያዙ የአነስተኛ አርሶአደር ማሳዎችን እንደ አርሶአደሩ ፍላጎትና እንደ መሬቱ ስፋት ማሳዉን አራት ቦታ በመክፈል በመጀመሪያ ዓመት አንዱን ክፍል ቡና መትከልና የተቀረዉን በለ✍ሎች አዋጭ ሰብሎች መ"ፈን፤ በሁለተኛዉ ዓመት ሁለተኛዉን ክፍል ማሳ ቡና መትከል፤ መጀመሪያ የተተከለዉ ቡና ማፍራት ሲጀምር ሶስተኛዉን ክፍል ማሣ መትከል እንደዚሁ እያለ በሂደት ጠቅላላዉን መረ✍ት በቡና መተካት፡፡

- የቡናዉንና የለ✍ሎች ሰብሎችን ሚዛንና ምርታማነት በጠበቀ መልኩ የምርምር ምክረ-ሀሳቦችን በመጠቀም ማሳዉን በሙሉ በስብጥር (Intercropping) የአተካከል/የአዘራር ዘደ✍ በቡናና በለ✍ሎች ሰብቦች መ"ፈን፡፡

- ማሳዉን ሁለት ቦታ በመክፈል ግማ"✍ን ቡና መትከልና ቀሪዉን ግማ" ደግሞ ለአካባቢዉ በሚስማሙ በለ✍ሎች ሰብሎች መ"ፈን፡፡

- በአነስተኛ አርሶአደሮች ያልተያዘና ለቡና ተስማሚ የሆነ ያልለማ መረ✍ት በመለየት የአካባቢን የተፈጥሮ ሚዛንና ሁነ✍ታዎች ባገናዘበ መልኩ በግል ባለሀብቶችና በሕብረት ሥራ ማሕበራት ተሳትፎ በዘመናዊ መንገድ በቡና እንዲለማ/እንዲ"ፈን ማድረግ፤

- ለቡና ተስማሚ የሆኑ ሰፋፊ መሬቶችን ለኢንቨስትመንት እንዲመቻች ማድረግ

- ያለዉን የምርምርና የልማት አቅም አቀናብቶ ለተለያዩ ቡና አብቃይ አካባቢዎች ተስማሚ የሆኑና ከቡና ጋር በስብጥር ሊመረቱ የሚችሉ ልዩ ልዩ ሰብሎችን በመለየት ምርታቸዉን፤ ምርታማነታቸዉንና ጥራታቸዉን የሚያሳድጉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ፤ በእጅ ያሉትን ደግሞ ማስተዋወቅና ማስፋፋት፡፡

- በሥልጠና፣ በልምድ ልውውጥና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ ከቡና ጋር በደባልነት፤ በተጓዳኝነት ወይም በአማራጭነት ሊመረቱ ለሚችሉ ልዩ ልዩ ሰብሎች የተሻሻሉ የአመራረት ቴክኖሎጂዎችን

ከዉጭ አገር በማስገባት የማላመድ ሥራዎችን ማከናወንና ተስማሚ የሆኑትን መርጦ ለተጠቃሚዉ ማስተዋወቅና ማሰራጨት፡፡

## 8.1.6. ለቡና አምራቾችና የግብይቱ ተዋንያን የግብአት ብድር አቅርቦት ማሳደግ

### 8.1.6.1 የቡና የዘር አቅርቦት የሥርዓቱ አካል ማድረግ

- ከምርምር ውጤታማነታቸዉ ተረጋግጦ የሚወጡና ቀደም ሲል የወጡ የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች ጥራታቸው ተጠብቆ ፈጥነው ወደ ምርት እንዲገቡ ለማስቻል በሚስማማቸዉ ሥነ-ምህዳር ቀጠና ብዜቱንና ሥርጭቱን የሚቆጣጠር፤ ፈቃድ የሚሰጥና የሚደግፍ የዘር ሥርዓት አካል ማ ማድረግ፡፡
- በዚህ ሥርዓት በዋናነት እውቅና በተሰጣቸው ግለሰብ/ በተደራጁ አርሶአደሮች፣ ፣ በገጠር ሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም በቡና አልሚ የግል ባለሀብቶች፤ በመንግሥት ሰርቶ ማሳያ እና ችግኝ ጣቢያዎች የቡና ዘርና ችግኝ ተዘጋጅቶ በተወዳዳሪና ተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው በሽያጭ ማቅረብ፡፡
- በምርምር የወጡ የዲቃላ ቡና ዝርያዎችን በቁርጥራጭና በቲ⅁✍ ካልቸር ዘደ✍ዎች በመጠቀምና በማባዛት ችግኞቻቸዉን በሚስማማቸዉ ሥነ-ምህዳር ቀጠና ለተጠቃሚዉ ለማሰራጨትና አቅርቦታቸዉን ለማሻሻል እንዲቻል የምርምሩን አቅም በሁለንተናዊ መልኩ ከመገንባት በተጨማሪ ብዜቱንና ሥርጭቱን ከላይእንደተመለከተዉ በማመቻቸትና በመደገፍ የምርምርና ኤክስተንሽን ቁርኙቱን ማጠናከር፡፡
- በረጅም ጊዜ አቅም ሲገኝ ደግሞ በተለያዩ ሥነ-ምሕዳራት የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች ጥራታቸው ተጠብቆ በቁርጥራጭና በቲ⅁✍ ካልቸር ወይም በችግኝም ሆነ በዘር የሚባዙበት ማዕከላትን ማ◌◌ም፡፡

### 8.1.6.2 የግብአት ብድር አቅርቦት ማሻሻል

¾u<“” U`f“ U`ታT’f KTdÅÓ“ Ø^f ለThhM ብሎም ¾ÓwÃ~” ¨<Ö?¬T’f KT[ÒÑØ ¾T>Áe‹M ¾wÉ`“ አቅርቦት ማመቻቸት እና ¾Ów›f ›p`xf Y`¯f መዘርጋት በተለይም የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ፤ የእርሻ መሳሪያዎች፤ ለምርት ዝግጅት ስራ አስፈላጊ የሆኑ የማድረቂያ ፤ማከማቻና የቡና መያዣ ቁሳቁሶች አቅርቦት ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡X”Ç=G<U ›=”Æef]¨< u}KÁ¿ U¡”Á„‹ (በቡና ዋጋ መዋ✈ቅ/ማ⅁ቆልቆልና በለ✍ሎች ክስተቶች) }ÓÇaf እ”ÇÁÒØS¨<፣ ካጋጠመውም Ñ<Ç~” KSk’e ¾T>Áe‹M ¾›ÅÒ SssT>Á eMf በቂ እና ወቅታዊ ድጋፍ uT>ðKÑ¬ SÖ”“ u}Ñu=¬ S”ÑÉ ማSS‰†f ያስፈልጋል፡፡

## 8.1.7 የአየር ንብረት ለውጥን መላመድና መቋቋም የሚያስችሉ የቡና ልማት ቴክኖሎጂዎችን ማስፋት

- **የተራዘመ የእርጥበት እጥረትን መ◌◌ም**
- ዝናብ አጠር በሆኑ ቡና አብቃይ አካባቢዎች የአፈርና ወሀ እቀባ ዘዴዎችንና ጉዝጓዝ፣ ብስባሽና ፍግ መጠቀም፤ ገረዛና ቅጥያ ማሳሳት ስራዎች እንዲሁም የደጋፊ መስኖ አጠቃቀም ሥርአቶችንና የተስተካከለ ጥላ ሊያጠሉ የሚችሉና የሚመከሩ የቡና ጥላ ዛፎችን በመትከል ችግሩን ማቃለል፡፡

- ለዝናብ አጠር ቡና አብቃይ አካባቢዎች ድርቅን ለመ✍✍ም የሚችሉ የቡና ዝርያዎችን በምርምር ለማፍለቅ የተጀመረዉን ጥረት ማጠናከር፡፡

- የቡናን ተክል ዉሃ የሚሻሙ ማንኛቸዉንም ዓይነት የጥላ ዛፎችና ደባል ሰብሎችን አለመጠቀም፡፡

- በጥናት ላይ በመመስረት ለሮቡስታ ቡና ልማት የበለጠ ተስማሚ በሆኑ አከባቢዎች አራቢካ ቡና ጋር በማሳም ሆነ በመጋዘንና ማጓጓዝ ሂደት የመቀላቀል ሥጋት እንዳይፈጥር ተደርጎ ማልማት የሚቻልበትን አማራጭ ማየት፡፡

## 8.1.8 የቡና በሽታና ተባይ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በስፋት መጠቀም

- **የቡና ፍሬ በሽታ ቁጥጥር**

  - በረጅም ጊዜየበ⏏ታዉ ጥቃት በጣም አስከፊ በሆነባቸዉ ይዞታዎች ያሉ ባለ ልዩልዩ ባሕርይ የአካባቢ ቡናዎች በልዩነታቸዉ ተሰብስበዉ በአንድ ማዕከል እንዲጠበቁ ማድረግ፤ ከአካባቢዉ ምርታማ የሆኑ፤ በ⏏ታዉን በሚ✍✍ሙ የተ☆☆ሉ የቡና ዝርያዎች መጠቀምና አዳዲሶችን በምርምር በማፍለቅና በማቅረብ ለአካባቢዉ ተስማሚና ምርታማ በሆኑ የተ☆☆ሉ የቡና ዝርያዎች ሙሉ በሙሉ መተካት፡፡

  - እንደ አጭር ጊዜ መፍትሔ የበ⏏ታዉ ጥቃት በጣም አስከፊ በሆነባቸዉ የቡና ይዞታዎች የተቀናጀ የበሽታ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን መጠቀም፡፡

- **የቡና ግንድ አድርቅ በሽታ መቆጣጠር**

**የአጭር ጊዜ መፍትሔ፡-** ባሕላዊ የመከላከያ ዘደዎችን መጠቀም (በአረምቁጥጥርና በኩትኳቶ ጊዘ✍ የቡናዉን ግንድና ሥር በገጀራና በመቆፈሪያ ያለማቁሰል፤ ከመገጀርና ከመኮትኮት ይልቅ በተለያዩ ዘደ✍ዎች (አፋኝ ሰብሎችን፣ ጉዝ⮙ዝና ▤ረ-አረም ከሚካል) በመጠቀም አረምን መቆጣጠር፤ በቡና ምቀሳ፤ ገረዛና ጉንደላ ወቅት የአንዱን ቡና ዛፍ ሥራ ጨርሰን ወደ ለ✍ላይኛዉ ዛፍ ስናልፍ የምንጠቀማቸዉን መሳሪያዎቸ በ⏏ታዉን ከሚያመጡ ተዋስያን የ▤ዱ ማድረግና በበሽታው የተያዙ ዛፎችን ነቅሎ ማቃጠል፤ ሊተገበሩ የሚገባቸው ተግባራት ናቸው፡፡

**በረጅም ጊዜ** ደግሞ በ⏏ታዉን የሚ✍✍ሙና ምርታማ የሆኑ የቡና ዝርያዎችን ለየአካባቢዉ ማፍለቅ እንደ ዋነኛ የምርምር ስትራቴጂያዊ አቅጣጫ መያዝ፡፡

- ሌሎች በሽታዎችንና ተባዮችን መቆጣጣር
- ሌሎች በሽታዎችና ተባዮች የከፋ ጉዳት በማድረስ ላይ ባይሆኑም አንዳንዴ የጎላ ጥቃት በሚያደርሱበት ወቅትና ቦታ በባለሙያ የሚመከሩ መከላከያ ዘዴዎችን በመጠቀም መከላከልና መቆጣጠር፡፡

## 8.1.9 የቡና ብዘሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ፍትሐዊ ልውውጥና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ

- ከምርምር ውጤታማነታቸዉ ተረጋግጦ የሚወጡና ቀደም ሲል የወጡ የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች ጥራታቸው ተጠብቆ ፈጥነው ወደ ምርት እንዲገቡ ለማስቻል በሚስማማቸዉ ሥነ-ምህዳር ቀጠና ብዜቱንና ሥርጭቱን የሚቆጣጠር፤ ፈቃድ የሚሰጥና የሚደግፍ መንግሥታዊ አካል ማ✍✍ም፡፡

- በዚህ አካል በዋናነት እውቅና በተሰጣቸው ግለሰብ አርሶአደሮች፣ በተደራጁ አርሶ አደሮች፣ በገጠር ሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም በቡና አልሚ የግል ባለሀብቶች፤ በመንግሥት ሰርቶ ማሳያ እና ችግኝ ጣቢያዎች የቡና ዘርና ችግኝ ተዘጋጅቶ በተወዳዳሪና ተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው በሽያጭ ማቅረብ፡፡

- በምርምር የወጡ የዲቃላ ቡና ዝርያዎችን በቁርጥራጭና በቲሹ ካልቸር ዘዴዎች በመጠቀምና በማባዛት ችግኞቻቸዉን በሚስማማቸዉ ሥነ-ምህዳር ቀጠና ለተጠቃሚዉ ለማሰራጨትና አቅርቦታቸዉን ለማሻሻል እንዲቻል የምርምሩን አቅም በሁለንተናዊ መልኩ ከመገንባት በተጨማሪ ብዜቱንና ሥርጭቱን ከላይ እንደተመለከተዉ ማመቻቸት፤ መደገፍና ማበራታታት አቅም ሲፈጠር ደግሞ በተለያዩ ሥነ-ምሕዳራት ጥራታቸው ተጠብቆ በቁርጥራጭና በቲሹ ካልቸር ወይም በችግኝም ሆነ በዘር የሚባዙበት ማዕከላትን ማቋቋም፡፡

- ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ተባይን፤ በሽታንና ድርቅን የሚቋቋሙና በተጠቃሚው ዘንድ ይበልጥ ተፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ጣዕም ያላቸው የቡና ዓይነቶች የሚገኙበት የተፈጥሮ ደኖች በጥንቃቄ ተለይተው ዘላቂነት ባለው ሁኔታ በመንግስት የተጠናከረ ጥበቃ እንዲደረግላቸው አስፈላጊውን ደንብና ሥርዓት በማዘጋጀትና ቀደም ሲል የወጡ መመሪያዎችንም ዉጤታማ በሆነ መልክ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

- ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ሀገሪቱ ካላት እምቅ የዘረ-መል ሀብት አኳያ የዘረመል ስትራቴጂ በማዘጋጀት የባለቤትነት መብታችንን በማስጠበቅ ዘረመሉን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መጠቀም የሚፈልጉ አካላት ተገቢዉን ክፍያ (Royallityfee) ፈፅመዉ አገልግሎቱን እንዲያገኙ በማድረግ ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት፡፡

- በቡና ጫካዎች ዙሪያ የሚኖረውን ህብረተሰብ በማደራጀትና በባለቤትነት ሀብቱን የማስተዳደር ኃላፊነቱን እንዲወስድ በማብቃት በአሁኑ ወቅት እየተስፋፋ በመጣው የጫካ ቡና ምርት የገበያ ፍላጎትና የጫካ ቡና ኢኮ-ቱሪዝም እንዲጠቀም በማድረግ ደኑ ተጠብቆ ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት፡፡

## 8.1.10 ቅንጅታዊ አሰራርን የሚደግፍ የአደረጃጀት ለውጥ ማድረግ

ቅንጅታዊ እንቅስቃሴን ለማጠናከርና የዘርፉን እድገት ለማፋጠን መንግሥት ካለዉ ፍላጎት የተነሳ የአደረጃጀት ማሻሻያ አማራጮችን በቅርቡ በባለሙያዎች ቡድን አሰጠንቶ እንዲቀርብለት በማድረግ እያጤነዉ ይገኛል፡፡ ጥናቱ ተግባራዊ ቢሆን በምርምር የወጡ የተሻሻሉ የቡና አመራረት ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች በስፋትና በፍጥነት ማስተዋወቅና ለማሰራጨት ወሳኝ መፍትሔ በመሆን ችግሩን ይቀርፋል የሚል እምነት አለ፡፡

### *8.1.11 የባለሙያ እጥረትና አቅም ውስንነትን መቅረፍ*

ከልማት ሰራተኛ እስከ ከፍተኛ ባለሙያና ተመራማሪ ድረስ ጎልቶ ከሚታየዉ የሰዉ ኃይል እጥረት በተጨማሪ የክህሎትና ዕዉቀት ውስንነቶች በስፋት አሉብን፡፡ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ፡-

- ለቡና ልማትና ጥራት መሻሻል መፍትሔ የሚሆኑ በምርምር ማሳ ላይ ያሉ አዳዲስና ነባር ቴክኖሎጂዎችን በተለያየ መንገድ (በሰርቶ ማሳያ፤ በልምድ ልዉዉጥ ወ.ዘ.ተ.) ቀጣይነት ባለው መልኩ ለባለሙያዉ ማስተዋወቅና እንዲተገብር መደገፍ
- በተለያዩ የቡና አብቃይ ሥነ-ምሕዳራት የተሻሻሉ የቡና አመራረት ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቂያ፤ ሰርቶ ማሳያና ቅድመ ማስፋፊያ ጣቢያዎችን ማቋቋም፡፡
- በወካይ ሥነ-ምሕዳራት ሁለገብ የቡና ማሰልጠኛ ማዕከላትን እንዲሁም በሀገሪቱ አንድ የተደራጀና ጠንካራ የቡና ኮሌጅ በማቋቋም ባለሙየዉንና አርሶ አደሩን ከተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች በቀጣይነት ማስተዋወቅ፡፡
- ለዘርፉ ተዋንያን አግባብነት ያለዉ የዉጭ አገር ልምድ ልዉዉጥና የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና ማመቻቸት፡፡

- የምርምሩን፤ የኤክስቴንሺኑን/የልማቱን፤ የምርት ዝግጅቱንና የጥራት ቁጥጥሩን በሰለጠነ የሰዉ ሀይል፤ በማቴሪያል፤ በፋሲሊቲዎችና በፋይናንስ አቅም ማጠናከር፡፡

## 8.2 የቡና ምርት ዝግጅት ጥራትና ግብይት ስርዓትን ማሻሻል

### 8.2.1 ሥነ ምህዳሩን ያማከሉ የተሻሻሉ የቡና ምርት አዘገጃጀት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና አጠቃቀም ማሳደግ

- ከቡና አለቃቀም፣ አዘገጃጀት፣ አከመቻቸትና ማጓጓዝ ጋር ተያይዘዉ የሚመጡትን ቁልፍ ችግሮች ለይቶ መፍታት፤
- የታጠበም ሆነ ያልታጠበ ቡና ለማዘጋጀት ጥራቱን የጠበቀ ቀይ እሸት ቡና ብቻ ለቅሞ መጠቀም፤ ደረጃውን በጠበቀ ማድረቂያና ማከማቻ መጋዘኖች ማስቀመጥ፤ ለማዕላዊ ገበያ የሚቀርበውን ቡና ጥራት ማሻሻል፤ ለአፈፃፀሙም በሥራ ላይ ያለዉን የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱን ማጠናከረና ውጤቱንም መገምገም፡፡
- ለታጠበ ቡና ኢንዱስተሪዎች የሥራ ዝርዝርና መስፈርት በማውጣት ኢንዱስትሪዎቹ ወቅታዊ ቅድመ-ምርመራ እንዲደረግላቸዉ፤ ዝቅተኛ ተፈላጊ ደረጃ በማስቀመጥና የማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት በየዓመቱ እንዲታደስ ለማድረግ የአፈጻጸም መመሪያና መርሃ ግብር ማዘጋጀት፡፡
- በታጠበ ቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂው እንዲሻሻል ወይም በተሻሻለ ቴክኖሎጂ እንዲተካ ማድረግ፤ በሁሉም የታጠበ ቡና ኢንዱስትሪዎች ከቴክኒክና ሙያ ማዕከል የተመረቀና በሙያው የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ያለው ባለሙያ እንዲኖር ማድረግ፡፡
- አነስተኛና መካከለኛ የቡና ማዘጋጃ ቴክኖሎጂዎች እንደየስነ-ምህዳሩና አካባቢው ተስማሚነታቸዉ ማስፋፋት፡፡
  - ከቡና አዘገጃጀት ጋር ተያይዞ የሚታየዉን ቁልፍ ችግር ለመቅረፍ ለአካባቢው ተስማሚ፣ አዋጭና በቀላሉ በአርሶአደሩ ተቀባይነት ያላቸውን የተሻሻሉ ቡና ማዘጋጃ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብና እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡
  - የአየር ርጥበት በሚበዛባቸው አካባቢዎች (በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ) በአጭር ጊዜ ቡና ሊያደርቁ የሚችሉ ዘመናዊ የቡና መፈልፈያና ማድረቂያ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ማዘጋጀት፡፡
- በደረቅ ቡና አቅርቦት ቁልፍ ችግር ሆኖ የሚታየው በጀንፈል መልክ ተዘጋጅቶ ለገበያ የሚቀርብ ቡና ጥራት በእይታ ብቻ ለይቶ በመከፈል በአርሶአደሩ ደረጃ የጥራት ተወዳዳሪነት ማምጣት የሚቻል ስለማይሆን ከጀንፈል ቡና ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን የጥራት ችግር ለመቅረፍ፤
  - መለሰተኛ የደረቅ ቡና መፈልፈያ ቴክኖሎጂ ለአርሶአደሩ በግል ወይም በቡድን እንዲቀርብ በማመቻቸት የተፈለፈለ ቅሽር ቡና ለገበያ እንዲቀርብ ማድረግ፡፡
  - ለጀንፈል ቡና የጥራት ደረጃ በማዘጋጀት ጥራትን ማዕከል ያደረገ የገበያ ስርዓት በመፍጠር በመጀመሪያ ገበያ ማዕከላት እንዲገበያዩ ማድረግ፡፡

- የተጠናከረና ተከታታይነት ያለው የቡና ኤክስቴንሽን ስርዓት በመዘርጋት የቡና ምርት አዘገጃጀት ቴክኖሎጂን የአፈፃፀም ደረጃ ከፍ ማድረግ፡፡

- ነባር የደረቅ ቡና ማበጠሪያ ኢንዱስትሪዎችን ብቃት መፈተሸና ደረጃቸው እንዲያሻሽሉ መደገፍ፡፡

## 8.2.2 የየአካባቢውን ሥነ-ምሕዳር ልዩ ባህርይና የጣዕም ይዘት ያላቸው ቡናዎች አዘገጃጀት ተግባራዊ ማድረግ

➢ የሃገራችንን ቡና ተፈላጊነትትና የገበያ ተወዳዳሪነት ባገናዘበ መልኩ የየአካባቢውን ሥነ-ምሕዳር ልዩ ባህርይና የጣዕም ይዘት ያላቸውን ቡናዎች ጥራት ለመጠበቅ፤የአካባቢውን የአየር ንብረት ያገናዘበ የቡና ምርት አዘገጃጀትና ጥራት አጠባበቅ በምርምር ተጠንተዉ እንዲለዩና በአምራቹ ዘንድ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤

## 8.2.3 የአቅርቦትና የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራ ደረጃ ምደባ ማጠናከርና ተመጋጋቢ ማድረግ

### 8.2.3.1 ጠንካራ የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብረ-መልስ ስርዓት መዘርጋት

- በአብዛኛው በቡና መረከቢያ አካባቢዎች/ጣቢያዎች ዋነኛ ሆኖ የሚታየው ከእርጥበት ጋር የተያያዘና የሚታይ ችግር በመሆኑ ይህን ችግር ለመቅረፍ የርጥበት መለኪያ መሳሪያ የያዘ የጥራት መፈተሻ ኪት (Quality inspection kit) ሁሉም ጣቢያዎች እንዲኖራቸው በማድረግ ለማዕከላዊ ገበያ የሚቀርቡ ቡናዎች ሙሉ በሙሉ የርጥበት መስፈርቱን ያሟሉ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

- በክልል ደረጃ ያለው የቡና ዝግጅት፤ ቁጥጥርና ግብይት ግብረ-ኃይል አወቃቀር በተለያዩ አደረጃጀቶችና መሥሪያ ቤቶች በመሆኑ በመረጃ አቀባበል፡ በቁጥጥርና ድጋፍ አሰጣጥ ረገድ ክፍተቶች ስለሚስተዋሉበት የቡና ጥራት ቁጥጥሩን ስርዓት ወጥነት ባለው መልኩ ለማከናወንና ለመደገፍ እንዲያመች አደረጃጀቱ እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት በሚያስችል መልኩ የተቃኘ ማድረግ፡፡

- በአገሪቱ ያሉትን የተለያዩ ቡና አይነቶች እንደሚበቅሉበት ሥነ-ምሕዳር፤ ያላቸውን ባህርይና ልዩ ጣዕም የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት (Coffee characterization & quality profile mapping)፡፡

### *8.2.3.2 ጠንካራ የኤክስፖርት መረጃና ግብረ መልስ ስርዓት መዘርጋት*

- ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ የምታቀርበው ቡና ከበቀለበት አካባቢና ልዩ ባሕርይና ጣዕም ካላቸዉ ዝርያዎች በመሆኑ በተመጋጋቢ መልኩ የውጭ ሀገር ሸያጭም ይህን የሀገሪቱን ልዩ ገፅታ ተመርኩዞ እንዲሆን የተደራጀ የመረጃ አያያዝና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፤ እንዲሁም በልዩ ውህድ ዝግጅት (Special blend) እየተሰራ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ቡና ከሆነ ተመዝግቦና በገበያው ታውቆ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት እንዲላክ ማድረግ፡፡

### 8.2.3.3 የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ መስፈርቶችን ማሻሻል

- ጥራት በአሁኑ ወቅት በጥሬና በቅምሻ ምርመራና ለዚህ በሚሰጥ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የአመራረት ስርዓትን፣ የምርት አመጣጥ ሂደቶችንና (Traceability and International standards) የምግብ ደህንነት ባገናዘበና የተጠቃሚዉን ፍላጎት በሚያረጋግጥ መልኩ የሚታይ እየሆነ መጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት ወደ ውጭ የሚላከዉ ቡና ከፍተኛ ጥንቃቄና ደህንነቱ የተረጋገጠ ሊሆን ስለሚገባው ይህንን ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ የሀገሪቱ የቡና ጥራት መስፈርት (Standard) የዋነኛ መዳረሻ ገበያዎችንና ከዓለም አቀፍ መስፈርቶች ጋር በማገናዘብ ማሻሻል፤ ለዚህም የአምራቾች፤ የአቅራቢዎች፣ የላኪዎች፣ የባለሙያዎችንና የገቢዎችና ጉምሩክ መ/በ✍ትን ዳሰሳ ጥናት በግብዓትነት መጠቀም፡፡

- የኤክስፖርት ቡና የጥራት መፈተሻ ላቦራቶሪዎችን ዘመኑ በሚፈልገው ቴክኖሎጂና በሰለጠን የሰው ሀይል ማጠናከርና የግብረ-መልስ የጥራት መረጃ ሥርዓት መዘርጋት፡፡
- የአረቢካ ቡና የብዝሃ-ህይወትና የልዩ ቡና ጣዕም ባለቤት መሆናችንን ተመርኩዞ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና በጎ ገጽታ ግንባታ በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ የተደራጀ፣ የተጠናከረና ሥርዓት የተዘረጋለት የብራንዲንግና የፕሮሞሽን ሥራ በሀገር ውስጥና በውጭ ትኩረት ሰጥቶ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

- ቡናን ያለወቅቱ መልቀም፤ ምርቱ ሳይበስል በማሳ ላይ እያለ መሸጥና ለህገ-ወጥ ድርጊትና ደላላዎች መጋለጥ እንዲሁም አርሶአደሩም ሆነ ለ✍ላዉ ቡና አምራች ምርቱን በጥራትና በገበያ ተወዳዳሪነት ላይ ተመርኩዞ እንዳያዘጋጅና እንዳያቀርብ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ዋናው ወቅታዊ የገንዘብ እጥረት በመሆኑ ይህንን ወቅታዊ ችግር ለመከላከል የቁጠባ ባህልን ማሳደግ፤ የቁጠባና ብድር አቅርቦትና ተደራሽነት እና የሰብል ዋስትና ብድር ማመቻቸት፡፡

- የአሰራር ደንቦችን፤ የአፈጻጸም መመሪያዎችን (Road map) እና የአሰራር ማንዋል ማዘጋጀት፤

### 8.2.4 ልዩ ባህርይና ጣዕም ካላቸዉ የቡና አይነቶች የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ

- የቡናን ምርት እሴት መጨመርና በገበያ የበለጠ ተወዳዳሪ መሆን፤

  ሀገራችን ልዩ ባህርይና ጣዕም ካላቸዉ የቡና አይነቶች የምታገኘው ጥቅም ከፍ ለማድረግና የቡናን ምርት እሴት በመጨመር በገበያ ጠንካራ ተወዳዳሪ መሆንና ከገበያው ሊገኝ የሚችለውን ሰፊ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፤ በዚያዉም የዘርፉ መጠናከር ከሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና የኢንዱስተሪ መስፋፋት ባሻገር ለዘጎች ሰፊ የሥራ ዕድልን መክፈት፡፡

### *8.2.5 ዘመናዊ የግብይት ስርዓትን የሚያጠናክር ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ግብረመልስ አሰራር መፍጠር*

- የቡና አርሶ አደሮች፤ የአምራቾች ሕብረት ሥራ ማህበራትና የንግዱ ተዋንያን የብድርና ግብዓት አገልግሎት በቀላሉ እንዲያገኙ ማድረግና የአደጋ ጊዜ ማካካሻ ስርዓትን (Risk management system) መዘርጋትና ማስፋፋት፤

- ግብይት በወቅታዊ መረጃ እንዲደገፍ ዘመናዊ የቡና ግብይት መረጃ ስርዓት መዘርጋት፤ ማጠናከር፤ ተገቢውን የገበያ ማስፋፊያና ትስስር ስራዎችን ማከናወን፣ የባለድርሻ አካላት ድጋፍ ስርዓት ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ የግብዓትና የሎጀስቲክስ ተግዳሮቶች በወቅቱ እንዲቀረፉ አመቺ አሰራር እንዲፈጠር ማድረግ፡፡
- የህብረት ስራ ማህበራትን የግብይትና ማኔጅመንት ክህሎት ማሳደግ፤ የምርት ማከማቻ መጋዘኖችን፣ የምርት ማዘጋጃ ፋሲሊቲዎችንና የፋይናንስ እጥረት መሠረታዊ ችግሮችን በመቅረፍ በምርት አቅርቦት እና በኤክስፖርት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ፡፡
- የቡና አምራቾችና የግብይቱ ተዋንያን ከገበያ ጋር በተያያዘ ሁነ✍ታ በሚፈጠር የዋጋ መዋዠቅና በተለያዩ ተግዳሮቶች ምክንያት የቡናው ዘርፍ አደጋ ላይ ሲወድቅ እንዳይጎዱ መከላከል የሚያስችል የኪሳራ ማካካሻ ፈንድና የገበያ ማረጋጊያ ስርዓት (Risk management system) መዘርጋት፤ በዚህም የቡና ዋጋ ከሚጠበቀው በላይ በሚወድቅበት ጊዜ ኑ⑤ቸዉ እንዳይናጋ የሚረዳ፤ እንዲሁም ለቡና ልማትና ለተጓዳኝ የግብርና ሥራዎች ቀጣይነት የሚደግፍ እና በግብይት ሂደት የሚከሰቱ ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ አሠራሮችን ማመቻቸት፡፡

### 8.2.6 የኤክስፖርት ቡና ዝግጅት፤ ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን በክልሎች ማስፋፋት

#### 8.2.6.1 የኤክስፖርት ቡና ዝግጅት በክልሎች ማስፋፋት

በማዕከላዊ ደረጃ የሚገኘውን ኤክስፖርት ቡና ዝግጅት ተደራሽና ከአቅርቦት ቡና ጋር ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ ለመፈፀም በዋና ዋና ቡና አምራች ክልሎች ማስፋፋት ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም ያላቀለት የቡና ምርት ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ሂደት የሚባክነውን ከፍተኛ መዋዕለነዋይና ጊዜን ከመቆጠቡም በላይ በክልሎች የቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ዘርፉ ከአምራቹ ጋር በማስተሳሰር የበለጠ ተወዳዳሪና ብቁ እንዲሆን ይረዳዋል፡፡ በመሆኑም በስትራተጂው ዘመን ከፍተኛ የቡና ምርት በመያቀርቡ ጊምቢ/ነቀምት፤ጅማና ሀዋሳ የቡና ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማድረግ

#### *8.2.6.2 የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን በክልሎች ማቋቋም*

በአዲስአበባና ድሬዳዋ ብቻ የሚገኘውን የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን ተደራሽ ለማድረግ አገልግሎቱን ቡና በከፍተኛ ደረጃ በሚመረትባቸው ዋና ዋና አካባቢዎች ማቋቋም ተገቢ ሲሆን በዚህም ምክነያት ተገል,ጋዩ በአቅራቢያው አገልግሎቱን እንዲያገኝ ከማስቻሉም በላይ ለዘርፉ መስፋፋትና መጎልበት አይነተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡በመሆኑም የኤክስፖርት ቡና ጥራት ምርመራና ሰርቲፊኬሽን አገልግሎት በጊምቢ/ነቀምት፤ጅማና ሀዋሳ እንዲቋቋሙ ማድረግ

## 9. የስትራቴጂዎች አፈፎ▭ም የድርጊት መረሐ ግብር

ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን የቡና ልማትና ጥራት ስትራቴጂያዊና ወሣኝ ጉዳዮች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎቻቸዉን ተግባራዊ ለማድረግ፤ የስትራቴጂዎች አፈፎ▭ም ስልትና መርሐ-ግብር ለማስፈ▭ም በዝርዝር ከተተነተነ በ♊ላ ጠቅለል ባለ መልክ እንደሚከተለዉ በሠንጠረዥ ቀርባ♉ል፡፡

### 9.1 የቡና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

የቡናን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያገለግሉ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግና ተደራሽ ግቦችን ለማስቀመጥ ቀደም ሲል የወጡ የተለያዩ መረጃዎች በግብአትነት ተወስደዋል፡፡

በዚህም መሰረት በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ባለፉት አምስት ዓመታት (2000-2004 በጀት ዓመት) አማካይ በቡና የተሸፈነ መሬት ስፋት፤የቡና ምርትና ምርታማነት ሁኔታ ሲታይ ምርት ሰጪ ቡና መሬት ስፋት 780000 ሄ/ር፤ አመታዊ የምርት መጠን 546000 ቶን፤ ምርታማነት 7.00 ኩ/ል በሄ/ር፤ በዚህ ወቅት ለምርት ያልደረሰ የቡና መሬት ሽፋን 320000 ሄ/ር እና አጠቃላይ በአገሪቱ በቡና የተሸፈነ መሬት ስፋት ግምት እስከ 1.1 ሚሊዮን ሄ/ር እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ ከዚህ ባሻገር የጫካ፤ የከፊል ጫካ፤ የጓሮ፤ የዘመናዊና ከፊል ዘመናዊ ቡናዎች የመሬት ይዞታ፤ የምርት ድርሻና ምርታማነት እንዲሁም ለቡና ልማት ተስማሚ የሆነ ነገር ግን በቡና ያልተሸፈነ የመሬት ስፋት ግምት ተደራሽ ግብ ለማስቀመጥ ከተወሰዱት ታሳቢዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

**ሠንጠረዥ 9፡ የእናት ቡና እደሳ***

**(ሄ/ር)**

| ክልል | እናት ቡና መሬት በሄ/ር | በጉንደላ የሚታደስ ቡና ጠቅላላ | ዓመታዊ የቡና ዕደሳ | | | | | | | በ2012 መጨረሻ ጠቅላላ የሚደረስበት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | |
| ኦሮሚያ | **482,882** | 193,153 | 13,800 | 16,560 | 20,700 | 26,910 | 37,674 | 54,627 | 81,941 | 252,212 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | **279,990** | 111,996 | 8,000 | 9,600 | 12,000 | 15,600 | 21,060 | 29,484 | 44,226 | 139,970 |
| አማራ | **7,630** | 1,526 | 109 | 131 | 163.5 | 212.6 | 298 | 431.5 | 647.2 | 1,992.4 |
| ጋምቤላ | **5,693** | 1,139 | 81 | 97.2 | 121.5 | 158 | 221.1 | 320.6 | 481 | 1,480.4 |
| ቤ/ጉምዝ | **4,503** | 901 | 64 | 76.8 | 96 | 124.8 | 168.5 | 236 | 354 | 1,120.1 |
| ትግራይ | **160** | 32 | 2.3 | 2.7 | 3.4 | 4.5 | 6.2 | 9 | 13.6 | 41.7 |
| ድምር | **780,858** | **308,747** | **24,062.3** | **28,474.7** | **35,092.4** | **45,018.9** | **61,437.8** | **87,119.1** | **129,674.8** | **396,816.6** |

*) ከእናት ቡና በኦሮሚያና ደ/ብ/ብ/ህ 40% እንዲሁም በአማራ፣ ጋምቤላ፣ ቤ/ጉምዝና ትግራይ 20% የሚሆነዉጉንዳላ እንደሚያስፈልገዉ ይገመታል፡፡

**ሠንጠረዥ 10: ያረጁ ቡናዎችን ነቅሎ ተከላ***

(ሄ/ር)

| ክልል | ጠቅላላ እናት ቡና መሬት | ነቅሎ ተከላ በሄ/ር | ዓመት | | | | | | | በ2012 መጨረሻ የሚደረስ በት (ሄ/ር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | |
| ኦሮሚያ | 482,882 | 120,725 | 8,450 | 10,560 | 13,200 | 16,504 | 20,630 | 25,800 | 32,250 | 127,394 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 279,990 | 55,998 | 5,600 | 6,400 | 7,400 | 8,520 | 9,785 | 11,260 | 12,955 | 61,920 |
| አማራ | 7,630 | 382 | 27 | 32.4 | 40.5 | 50.6 | 65.8 | 85.6 | 111.2 | 413.1 |
| ጋምቤላ | 5,693 | 285 | 20 | 24 | 30 | 40.5 | 52.6 | 71.1 | 96 | 314.4 |
| ቤ/ጉምዝ | 4,503 | 225 | 16 | 19.2 | 24 | 30 | 39 | 52.6 | 71.1 | 251.9 |
| ትግራይ | 160 | 8 | 0.5 | 0.7 | 0.8 | 1.1 | 1.4 | 2 | 3 | 9.5 |
| **ድምር** | **780,698** | **177,623** | **16,120.5** | **19,044.3** | **22,704.3** | **27,156.2** | **32,584.8** | **39,283.3** | **45,486.3** | **190,302.9** |

*) ከእናት ቡና በኦሮሚያ 25፣ በደ/ብ/ብ/ህ 20 እንዲሁም በአማራ፣ ጋምቤላና ቤ/ሻንጉል ጉምዝ 5% የሚሆነዉ በጣም ያረጀ ስለሆነ ተነቅሎ መተከል እንዳለበት ታሳቢ ተደርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 11: በተጎነደለና እናት ቡና ማሳ ውስጥ ስግሳጎ ተከላ***

(ሄ/ር)

| ክልል | የእናት ቡና መሬት (ሄ/ር) | ዓመታዊ ስግሳጎ ተከላ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| ኦሮሚያ | **482,882** | 70,875 | 65,815 | 58,500 | 49,646 | 42,490 | 37,770 | 30,392 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | **279,990** | 40,158 | 36925 | 32,115 | 30,704 | 28657 | 26152 | 23359 |
| አማራ | **7,630** | 1300 | 1250 | 1150 | 1050 | 950 | 850 | 800 |
| ጋምቤላ | **5,693** | 830 | 821 | 800 | 759.5 | 740.4 | 719 | 689 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | **4,503** | 657 | 650 | 628 | 619 | 601 | 567.4 | 529 |
| ትግራይ | **160** | 25 | 24 | 23 | 22 | 21 | 20 | 20 |
| **ድምር** | **780,858** | **115,851** | **107,492** | **95,224** | **84,809.5** | **75,469.4** | **68,089.4** | **57,801** |

*) በተጎነደለና እናት ቡና ማሳ ውስጥ በአማካኝ 500 የቡና ችግኝ በሄ/ር በስግሳጎ እንደሚተከል ይገመታል፡፡

**ሠንጠረዥ 12፡ በተመረጡ ዝርያዎች አዲስ ቡና ተከላ**

**(ሺህ ሄ/ር)**

| ክልል* | ተስማሚ መሬት (ፖቴንሻል) | ዓመት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ ዕቅድ | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| ኦሮሚያ | 9,998 | 1197 | 147 | 154 | 162 | 188 | 197 | 180 | 171 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 4,338 | 651 | 93 | 98 | 102 | 107 | 89 | 84 | 78 |
| አማራ | 6,552 | 66 | 0.9 | 1.1 | 3 | 6 | 11 | 22 | 22 |
| ጋምቤላ | 2,379 | 3 | 0.3 | 0.3 | 0.4 | 0.4 | 0.5 | 0.5 | 0.6 |
| ቤ/ል ጉምዝ | 210 | 5.2 | 0.1 | 0.2 | 0.3 | 0.4 | 0.6 | 1.2 | 2.4 |
| ትግራይ | 627 | 3 | 0.02 | 0.03 | 0.05 | 0.1 | 0.4 | 0.8 | 1. 6 |
| ድምር | **23,105** | **1925.2** | **241.32** | **253.63** | **267.75** | **301.9** | **298.5** | **288.5** | **281** |

* ካለዉ እምቅ አቅም በደ/ብ/ብ/ህ 15፣ በኦሮሚያ 12፣ በቤ/ጉምዝ 2.5፣ በአማራ 1፣ ቢጋምቤላ 0.125 ና በትግራይ 0.05% ለአርሶ አደሮች የቡና ልማት ይዉላል

**ሠንጠረዥ 13፡ በተከላ እና በጉንድል ቡና ማሳ ኮምፖስት፣ ጉዝጓዝና አፈርና ዉሃ ጥበቃ የሚደረጉለት መሬት**

**(ሄ/ር)**

| ክልል | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | 237,365 | 260,845 | 261,460 | 257,650 | 242570 | 214,670 | 195,392 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 191,984 | 160,325 | 155,515 | 146,224 | 134,442 | 121,412 | 114,314 |
| አማራ | 7,690 | 8,430 | 10,430 | 14,130 | 22,115 | 32,100 | 50,080 |
| ጋምቤላ | 5,515 | 6,555 | 7,665 | 8,560 | 8,899 | 10,605 | 15,375 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | 4,300 | 5,200 | 6,100 | 8,254 | 12,690 | 15,525 | 25,810 |
| ትግራይ | 115 | 180 | 210 | 260 | 360 | 560 | 840 |
| **ድምር** | 448,975 | 443,542 | 443,388 | 437,087 | 423,086 | 396,883 | 403,823 |

**ሠንጠረዥ 14፡ የቡና እንክብካቤ በሙሉ ፓኬጅ የሚተገብሩ ሞዴል አርሶአደሮች**

**(ቁጥር)**

| ክልል | ቡና አምራች ወረዳ ብዛት | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | 173 | 1,730 | 3,460 | 10,380 | 41,520 | 207,600 | 622,800 | 1,245,600 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 113 | 1,130 | 2,260 | 6,780 | 27,120 | 135,600 | 406,800 | 813,600 |
| አማራ | 25 | 500 | 1000 | 3,000 | 12,000 | 60,000 | 180,000 | 180,000 |
| ቤ/ጉምዝ | 3 | 60 | 120 | 360 | 1, 440 | 7200 | 21,600 | 43,200 |
| ጋምቤላ | 2 | 40 | 80 | 240 | 960 | 4,800 | 14,400 | 28,800 |
| ትግራይ | 2 | 20 | 40 | 120 | 480 | 2,400 | 7,200 | 14,400 |
| ድምር | **318** | 3,480 | 6,960 | 20,880 | 83,520 | 417,600 | 1,252,800 | 2,327,612 |

**ሠንጠረዥ 15፡ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያን በመጠቀም የመለማ ቡና***

**(ሄ/ር)**

| ክልል | ቡና አምራች ወረዳ ብዛት | ዓመት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | **2006** | **2007** | **2008** | **2009** | **2010** | **2011** | **2012** |
| ኦሮሚያ | 173 | 216.25 | 432.5 | 2,595 | 10,380 | 103,800 | 311,400 | 622,800 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 113 | 141.25 | 282.5 | 1,695 | 6,780 | 67,800 | 203,400 | 406,000 |
| አማራ | 25 | 31 | 62 | 375 | 1,500 | 15,000 | 25,000 | 30,000 |
| ቤ/ጉምዝ | 3 | 3.75 | 7.5 | 45 | 90 | 180 | 540 | 1,080 |
| ጋምቤላ | 2 | 2.5 | 5 | 30 | 240 | 440 | 360 | 720 |
| ትግራይ | 2 | 2.5 | 5 | 30 | 60 | 120 | 240 | 480 |
| **ድምር** | 318 | **397.25** | **794.5** | **4,770** | **19,050** | **187340** | **540.940** | **1,061,080** |

***)** በየወረዳዉ አስር ሞዴል አርሶአደሮች ካላቸዉ የቡና ይዞታ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ቢያንስ 0.125፣ በቀጣይ ሁለት ዓመታት ሩብ እንዲሁም በቀሪ ዓመታት ከቡና ማሳውበአማካይ እስከ ግማሽ ሄክታር ሰው ሰራሽ ማዳበሪያን በመጠቀም የቡና ምርቱን በማሳደግ ተሞክሮዉን ለሌሎች ያካፍላል በሚል ታሳቢ የተሰራ፡፡

### ሠንጠረዥ 16፡ የቡና ግንድ አድርቅና ሌሎች በሽታዎች ቁጥጥር*

**(ቡና እግር ቀጥር)**

| ክልል | በ2006 ምርት የሚሰጥ ቡና መሬት (ሄ/ር) | በበሽታ የተጠቃ ቡና እግር ብዛት | ዓመታዊ ግብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | **2007** | **2008** | **2009** | **2010** | **2011** | **2012** |
| ኦሮሚያ | **482,882** | 19,315,280 | 2,897,292 | 3,331,886 | 3,831,669 | 4,406,419 | 5,067,782 | 5,827,489 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | **279,990** | 11,199,600 | 1,679,940 | 1,931,931 | 2,221,721 | 2,554,979 | 2,938,226 | 3,378,960 |
| አማራ | **7,630** | 305,200 | 45,780 | 52,647 | 60,544 | 69,626 | 80,070 | 92,080 |
| ጋምቤላ | **5,693** | 227,720 | 34,158 | 39,282 | 45,174 | 51,950 | 59,743 | 68,704 |
| ቤ/ጉምዝ | **4,503** | 180,120 | 27,018 | 31,071 | 35,731 | 41,091 | 47,255 | 54,343 |
| ድምር | **780,698** | 31,227,920 | 4,684,188 | 5,386,817 | 6,194,839 | 7,124,065 | 8,193,076 | 9,421,576 |

***)** በአንድ ሄ/ር 2000 እግር ቡና በአማካይ እንደሚኖርና ከዚህ ዉስጥ 2% በበሽታ ሊጠቃ የሚችል መሆኑና በየዓመቱ 15%

እንደሚወገድ ታሳቢ ተደርጎ የተሰላ

### ሠንጠረዥ 17፡ ምርት የሚሰጥ የቡና መሬት*

**(ሄ/ር)**

| **ክልል2006** | | **2007** | **2008** | **2009** | **2010** | **2011** | **2012** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | **482,882** | 580,632 | 678,512 | 793,412 | 922,008 | 1,048,964 | 1,170,647 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | **279,990** | 348,390 | 417,390 | 493,990 | 578,070 | 663,625 | 665,081 |
| አማራ | **7,630** | 8,244 | 8,881 | 9,636 | 10,430 | 11,362.5 | 14,098.5 |
| ጋምቤላ | **5,693** | 5,742 | 5,821 | 6,000 | 6,219 | 6,391 | 6,587 |
| ቤ/ጉምዝ | **4,503** | 4,513 | 4,515 | 4,555 | 4,593 | 4,701 | 4,861 |
| ትግራይ | 160 | 162.2 | 168.8 | 181.9 | 199.5 | 226 | 270.3 |
| **ድምር** | 780,858 | 947,683.2 | 1,115,287.8 | 1,307,774.9 | 1,521,519.5 | 1,735,269.5 | 1,852,544.8 |

* በየዓመቱ የሚጎነደልና የሚነቀል እናት ቡና እንዲሁም ወደ ምርት የሚገባዉን ጉንድል፣ አዲስና ነቅሎ ተከላ ቡናን ከግምት

ውስጥ በማሳገባት የተሰላ

## ሠንጠረዥ 19፡ የሚጠበቅ የቡና ምርታማነት

(ኩ/ል በሄ/ር)

| ክልል | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | 7 | 7.4 | 8.2 | 9.1 | 10.1 | 11.2 | 12.3 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 7.3 | 8 | 8.9 | 9.9 | 11 | 12 | 12.8 |
| አማራ | 5 | 5.5 | 6.2 | 7.3 | 8.5 | 9.8 | 11.2 |
| ጋምቤላ | 6 | 6.3 | 6.8 | 7.4 | 8.3 | 9.4 | 10.5 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | 5.8 | 6.1 | 6.6 | 7.2 | 8 | 9 | 10 |
| ትግራይ | 7 | 7.5 | 8.3 | 9.3 | 10.4 | 11.6 | 13 |
| አማካይ | **7.1** | **7.6** | **8.4** | **9.4** | **10.4** | **11.5** | **12.5** |

## ሠንጠረዥ 17፡ የሚጠበቅ ቡና ምርት መጠን

(ሺህ ቶን)

| ክልል | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | 338 | 429. 7 | 556.4 | 722 | 931.2 | 1174.8 | 1439.9 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 204.4 | 278.7 | 371.5 | 489 | 635. 9 | 796.4 | 851. |
| አማራ | 3.81 | 4.5 | 5.5 | 7 | 8.9 | 11.1 | 15.5 |
| ጋምቤላ | 3.4 | 3.6 | 4 | 4.4 | 5.2 | 6 | 6.9 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | 2.6 | 2.8 | 3 | 3.3 | 3.7 | 4.2 | 4.9 |
| ትግራይ | 0.11 | 0.12 | 0.14 | 0.17 | 0.21 | 0.26 | 0.35 |
| **ድምር** | **552.32** | **719.4** | **940.54** | **1225.87** | **1585.1** | **1992.76** | **2318.6** |

### ሠንጠረዥ 20፡ የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች ዘር አቅርቦትና ስርጭት*

**(ኩ/ል)**

| ክልል | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | 1684 | 1766 | 1859 | 2136 | 2254 | 2127 | 2088 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 1067 | 1118 | 1159 | 1213 | 1046 | 1005 | 951 |
| አማራ | 12 | 14 | 33 | 63 | 113 | 223 | 223 |
| ጋምቤላ | 5 | 5 | 6 | 6 | 7 | 7.1 | 8.3 |
| ቤ/ል ጉምዝ | 2.5 | 3.5 | 4.5 | 5.6 | 8 | 7.5 | 26 |
| ትግራይ | 0.5 | 0.5 | 0.75 | 1.1 | 4.1 | 8.5 | 17 |
| ድምር | **2771** | **2907** | **3062.3** | **3424.7** | **3432.1** | **3378.1** | **3313.3** |

### ሠንጠረዥ 21፡ የተሻሻሉ የቡና ዝርያዎች ዘር ምርትና አቅርቦት

**(ኩ/ል)**

| የቡና ዘር ምንጭ | ዓመታዊ አቅርቦትና ስርጭት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **2006** | **2007** | **2008** | **2009** | **2010** | **2011** | **2012** |
| ምርምር ማዕከላት | 416 | 436 | 460 | 513.5 | 515 | 506 | 497 |
| ሰፋፊ እርሻዎች | 416 | 436 | 460 | 513.5 | 515 | 507 | 497 |
| በአርሶአደሮች | 1939 | 2035 | 2143 | 2398 | 2403 | 2365 | 2319 |
| **ድምር** | **2771** | **2907** | **3063** | **3425** | **3433** | **3379** | **3313** |

### ሠንጠረዥ 22፡ የተሻሻሉ የዲቃላ ቡናዎች ችግኝ ዝግጅት*

| ዝርዝር | በጀት ዓመት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **2006** | **2007** | **2008** | **2009** | **2010** | **2011** | **2012** |
| የሚዘጋጅ ችግኝ (ቁጥር) | - | - | 137,500 | 275,000 | 550,000 | 687,500 | 825,000 |
| ሊለማ የሚችል (ሄ/ር) | - | - | - | 50 | 100 | 200 | 250 |
| ተሳታፊ አርሶአደሮች | - | - | - | 200 | 400 | 800 | 1,000 |

* እያንዳንዱ ሞዴል አርሶአደር 0.25 ሄ/ር እንደሚያለማ የሚጠበቅ ሲሆን የዲቃላ ቡና ችግኝ ዝግጅት በጅማ ግ/ም/ማ/ እና ለዘር ምንጭነት በሚቋቋሙት ማዕከላት ይሆናል፡፡

### ሠንጠረዥ 23፡ በየደረጃዉ ላሉ ባለሙያዎች ስልጠና

(ቁጥር)

| ክልል | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | 1730 | 1990 | 2288 | 2631 | 2368 | 2013 | 1610 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 1130 | 1300 | 1495 | 1719 | 1547 | 1315 | 1052 |
| ጋምቤላ* | 50 | 58 | 66 | 76 | 87 | 100 | 115 |
| አማራ | 250 | 288 | 331 | 381 | 438 | 504 | 579 |
| ቤ/ ጉምዝ* | 60 | 69 | 80 | 92 | 107 | 123 | 142 |
| ትግራይ | 10 | 12 | 14 | 16 | 19 | 22 | 25 |
| ድምር | **3230** | **3717** | **4274** | **4915** | **4566** | **4077** | **3523** |

* በጋምቤላና ቤ/ጉምዝ ሥልጠናዎች ከልማት ሠራተኞች በተጨማሪ ግምባር ቀደም አርሶ አደሮችም ይሳተፋሉ፡፡

## 9.2. የቡና ምርት ዝግጅትና ጥራት ማሻሻያ መርሃ-ግብር

ለማዕከላዊ ገበያ የቀረበ የአቅርቦት ቡና የጥራት ይዘት ሲታይ እጅግ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ይህንን ለማሻሻል በስትራቴጂው ቁልፍ ተግባራቶች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ ለዚህም መሻሻል በ2005 ዓም ለኢትጵያ ምርት ገበያ የቀረበ የኤክስፖርት አቅርቦት ቡና መረጃ መነሻ በማድረግ ተወስዷል፡፡ በዚህም መሠረት በ2005 ዓ.ም ለማዕከላዊ ገበያ ከቀረበ ቡና 27.75% የታጠበ ቡና ሲሆን 72.25% ያህሉ ያልታጠበ ደረቅ ቅሽር ቡና ነው፡፡

በጥራት ይዘት አንፃር ለማዕከላዊ ገበያ ከቀረበው ያልታጠበ ቅሽር ቡና 1% ያህል ብቻ የልዩ ቡና ዝግጅት (Specialty coffee) በመሆኑ ይህንን በስትራቴጀው የተቀመጡ ቁልፍ ተባራትን ትኩረት ሰጥቶ በመተግበር በ 201**2** ዓ.ም ወደ 50% ለማሳደግና የዝቅተኛ ጥራት ይዘት ያለውን አቅርቦት ቡና ድርሻ ከ40% ወደ 15% ዝቅ ለማድረግ ግብ ተይዟል፡፡ በአንፃሩ የተሻለ ዝግጅትና ጥራት ይዘት ያለውን የታጠበ ልዩ ቡና በዋናነት በስትራቴጂው ትኩረት የተሰጣቸውን በታጠበ ቡና ኢንደስትሪ የምንጠቀምባቸውን ቴክኖሎጂዎች ማሻሻልና በምርት ዝግጅት ወቅት የሚከሰቱትን ችግሮች ለይቶ በመስራትና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬሽን አይነት ታሳቢዎችን በመተግበር ለማዕከላዊ ገበያ የሚቀርበውን ልዩ ቡና አሁን ካለበት 10% ወደ 85% ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 24፡ ለማዕከላዊ ገበያ የሚቀርብ የኤክስፖርት አቅርቦት ቡና ተደራሽ ግብ**

(መቶኛ)

| የቡና ዝግጅት | የጥራትደረጃ | በጀት ዓመት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መነሻ | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |

| ዓይነት | | (2005) | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የታጠበ | ልዩ ቡና (Specialty coffee) | 11 | 15 | 19 | 23 | 28 | 32 | 35 | 40 |
| | መካከለኛደረጃ (High commercial | 87 | 85 | 81 | 77 | 72 | 68 | 65 | 60 |
| | ዝቅተኛ | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ያልታጠበ | ልዩ ቡና (Specialty coffee) | 1 | 4 | 8 | 13 | 18 | 24 | 26 | 30 |
| | መካከለኛ ደረጃ (High commercial) | 53 | 52 | 50 | 47 | 44 | 41 | 40 | 40 |
| | ዝቅተኛ ደረጃ (Low commercial) | 46 | 44 | 42 | 40 | 38 | 35 | 34 | 30 |

### ሠንጠረዥ 25፡ ለማዕከላዊ ገበያ አቅርቦት ቡና መጠን

(ሺህ ቶን)

| ክልል | በጀት ዓመት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **2006** | **2007** | **2008** | **2009** | **2010** | **2011** | **2012** |
| ኦሮሚያ | 294 | 374 | 484 | 628 | 810 | 1022 | 1253 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 175 | 242 | 323 | 425 | 553 | 693 | 740 |
| ጋምቤላ | 2 | 2 | 3 | 3.5 | 4.5 | 6 | 8 |
| አማራ | 3 | 3 | 3 | 3.5 | 4 | 4 | 5.5 |
| ቤኒሻንጉል ጉምዝ | 1.5 | 1.5 | 2 | 2 | 2 | 2.5 | 3 |
| **ድምር** | **475.5** | **622.5** | **815** | **1062** | **1373.5** | **1727.5** | **2009.5** |